አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት


# በአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ኢአፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች


በ

**ድንቄሳ ዴሬሳ**


ሰኔ፣ 1996 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| Belay Tefera<br>ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# በአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ኢአፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

ድንቂሳ ዴሬሳ

ሰኔ፣ 1996 ዓ.ም

# በአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ኢአፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ንጽጽርና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር (TeAm)
ኤም.ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ድንቄሳ ዴሬሳ

ሰኔ፣ 1996 ዓ.ም

ይህ የጥናት ሥራ መታሰቢያነቱ ትምህርቴን በመከታተል ላይ እያለሁ ከዚህ አለም በሞት ለተለየችኝ እናቴ አዳነች ይነሱና በናቅፋ በረሃ ያሞራ ሲሳይ ለሆነው ለታላቅ ወንድሜ ጌታቸው ዴሬሳ ይሁንልኝ።

# ምስጋና

አንድ ጎበዝ አትክልተኛ ጥሩ ተክል መርጦ ተንከባክቦ ለፍሬ እንደሚያበቃ ሁሉ፣ ከርዕስ መረጣው አንስቶ የስራ ሂደቱን በቅርበት በመከታተል፣ በማረቅና በማዳበር ለዚህ እንዲበቃ ላስቻሉ አማካሪዬ ረዳት ፕሮፌሰር አለም እሸቱ እጅግ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የእርስዎ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ባይኖር ኖሮ ይህ ስራ ለዚህ ደረጃ ባልበቃ ነበር።

የትምህርት ዕድሉን ሳገኝ ደስታዬ ደስታችሁ የሆነና እስከመጨረሻው ድረስ ስታበረታቱኝ ለነበራችሁ መምህሮቼ፣ የልብ ጓደኞቼ፣ ጎረቤቶቼና ወዳጆቼ ሁሉ ትልቅ አክብሮት አለኝ። ከሞራል ባሻገር በሙያችሁ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ፣ በሃሳብና በማቴሪያል ከጐኔ ላልተለያችሁኝ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። በተለይ ለሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ ቤተመፃሕፍት፣ ለስርአተ ትምህርት ቤተመፃሕፍትና የቋንቋ ፓናል አባላት ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

ዘወትር እኔን ደስ ለማሰኘት ስትማስኑና ከእኔ ጋር ሁለት አመት ሙሉ ጭንቅ ጥብብ ስትሉ ክፋና ደግ የተፈራረቀባችሁ ውድዋ ባለቤቴ አበበች መኮንንና ልጆቼ ትዕግስትና ፍቅር እንኳን ደስ አላችሁ! ከልብ ኮርቼባችኋለሁ።

በእውነት ለትየባ የማይጋብዝና አስቸጋሪ የሆነውን ሙጭርጭር ዕሑፌን ተቋቁመሽ ቀን ዕረፍትሽን ሰውተሽ፣ ለሊት እንቅልፍሽን አጥተሽ ይህን ልቅም ያለ ሥራ ለሠራሽልኝ ለወይዘሪት ምስራቅ ጉልትነህ ያለኝ ምስጋና ወደር የለውም።

# አህፅሮተ-ጥናት (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት በቋንቋው ትምህርት ላይ የመሰናዶ ተማሪዎች ያመጡት የአመለካከት ለውጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነበር:: ከዚህም ባሻገር ለውጥ ካለ የለውጡ መንስኤዎች ሊቀረፉ የሚችሉበትን የመፍትሄ ሃሳብ ለመጠቆም ነበር:: ይህንኑን ለመተግበር የሚያስችሉ አራት መሠረታዊ ጥያቄዎች ከተነደፉ በኋላ ጥናቱን ለማካሄድ ናሙናዎች ተወስደዋል:: በዚሁ መሠረት ለቋንቋው አፊፊት ለሆኑት ሁለት የአዲስ አበባ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች እና ለቋንቋው ኢአፊፊት ለሆኑት ደግሞ በምስራቅ ሸዋ ዞን ስር ከሚገኙት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች መካከል ሶስት ተወስደዋል::

አራት መቶ የመሰናዶ ተማሪዎችንና አሥር የመሰናዶ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላት፣ ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለተማሪ ወላጆች ቃለ መጠይቅ በማድረግና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: በተለያየ መንገድ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተመዝግበው ከተጠናቀሩ በኋላ የእያንዳንዳቸው ውጤት በተናጠል ከአፊፊት እና ከኢአፊፊት ተማሪዎች አንፃር ተተንትነዋል:: ከዚያም በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እርስ በርስ በንጽጽር መልክ ለማየት ተሞክሯል::

እነዚህ ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ የተገኘው ውጤት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ የአመለካከት ለውጥ እንዳመጡ ያሳያል:: ይህ የአመለካከት ለውጥ ደግሞ ለቋንቋው አፊፊት በሆኑትም ሆነ በኢአፊፊቶች ላይ ተንፀባርቋል:: በዚህም ምክንያት የቋንቋው ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናዎች ውስጥ አለመካተት ተማሪዎቹ ትምህርቱን ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱት እንዳደረጋቸው ለመገንዘብ ተችሏል:: ከዚህም ባሻገር የተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያን ያህል ቦታ አለመስጠት ቋንቋውን በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የሞራል ውድቀት በማድረሱ ግድየለሽ እንዲሆኑ በር የከፈተ ይመስላል:: እንዲሁም ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና አለመሰጠት፣ የመምህራን ስሜት መጎዳት፣ ስለቋንቋው የሚነገሩ የተሳሳቱ አባባሎችና ሌሎች ተላውጦዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከትን እንዲያዳብሩ እንዳደረጋቸው ለመገመት ተችሏል::

በመጨረሻም በተመዘገበት ውጤት ማየት እንደሚቻለው በቋንቋው ትምህርት ላይ አፍራሽ የሆኑ ሁኔታዎች እያጠሉበት ያሉ ይመስላሉ:: አጥኚው ከዚሁ በመነሳት ለችግሩ መፍትሄ ይሆናሉ ብሎ ያሰፈራቸው አስተያየቶች ተቀምጠዋል::

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና ........ i

አህፅሮተ-ጥናት ........ ii

## ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4
1.4. የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.5. የጥናቱ ውስንነት ........ 5
1.6. ስያሜ ቃላት ........ 6
1.7. የአዲስ አበባ መስተዳድርና የምስራቅ ሸዋ ዞን አጭር ቅኝት ........ 7

## ምዕራፍ ሁለት:- ክለሳ ድርሳን

2.1. የመሰናዶ መርሃ ግብር ምንነትና የመሰናዶ ተማሪዎች ማንነት ........ 9
2.2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዳራ ........ 10
2.2.1. የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት ........ 10
2.2.2. አማርኛ እንደ ማስተማሪያ ቋንቋ ........ 10
2.3. ስነልቦና በስነ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና ........ 11
2.4. አመለካከት ምንድን ነው? ........ 13
2.4.1. አመለካከት ለምን ይጠናል? ........ 14
2.4.2. የአመለካከት ምንጮች ........ 15
2.4.3. ለአመለካከት መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች ........ 16
2.4.4. አመለካከት እንዴት ይለካል? ........ 18
2.4.4.1. በአመለካከት አለካክ ዙሪያ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች ........ 18
2.4.4.2. የአመለካከት መለኪያ ዘዴዎች ........ 19
2.4.5. አመለካከት 2ኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ........ 21
2.5. ተማሪዎች በሚማሩት የቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚገፋፉ ሁኔታዎች ........ 22
2.6. በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን አመለካከት አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች ........ 25

## ምዕራፍ ሶስት፡- የጥናቱ ዘዴ

3.1. ናሙና ........................................................................................................27

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ....................................................................30

3.3. የመረጃ አተናተን ስልቶች ..............................................................................33

3.4. የመረጃዎች ስሌታዊ አሰራር ...........................................................................34

## ምዕራፍ አራት፡- ውጤቶችና ትንታኔያቸው

4.1. የጽሁፍ መጠይቅ መላሽ ተማሪዎች አጠቃላይ ዳራ .........................................35

4.2. ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...............................39

4.3. ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...............................76

4.4. በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ...................................................86

4.5. በቃለ መጠይቅ ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከተማሪ ወላጆች የተገኙት መረጃዎች ንጽጽር ..................................................................................................91

## ምዕራፍ አምስት፡- አጠቃላይ ግኝትና የመፍትሄ ሃሳብ

5.1. ግኝት .............................................................................................................94

5.2. የመፍትሄ ሃሳብ .............................................................................................96

ዋቢ ጽሁፎች ..........................................................................................................99

አባሪዎች

አባሪ «ሀ» የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ..........................................................103
አባሪ «ለ» የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ..........................................................108
አባሪ «ሐ» ለተማሪዎች በቃለ መጠይቅ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎች ..........................111
አባሪ «መ» ለመምህራን በቃለ መጠይቅ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎች ..........................112
አባሪ «ሠ» ለተማሪ ወላጆች በቃለ መጠይቅ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎች ......................113
አባሪ «ረ» «ወደ ከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ አለመካተቱ የሚያሳድረው ተፅዕኖ» በሚለው ተላውጦ ስር የተመዘገበ ዝርዝር ውጤት ......114
አባሪ «ሰ» «የተማሪው ግላዊ አመለካከት» በሚለው ተላውጦ ስር ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገቡት ውጤቶች ..........................................................115
አባሪ «ሸ» «የአማርኛ ቋንቋን መማር ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንፃር» በሚል ተላውጦ ስር ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገበው ውጤት ዝርዝር ..............116
አባሪ «ቀ» «ወላጆች፣ እኩዮች፣ ኅብረተሰብና የመገናኛ ብዙሃን አመለካከት» በሚል ተላውጦ ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች የተገኘው ውጤት ዝርዝር ...........117
አባሪ «በ» «ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት/ኢአፈፊት ከመሆን አንፃር» ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተገኙት ዝርዝር መልሶች ..................................................118
አባሪ «ተ» «የመማሪያ መፃህፍት ይዘትና አቀራረብ» በሚል ተላውጦ ስር ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገቡ ውጤቶች ..............................................119
አባሪ «ቸ» «ለአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከተሰጠው ዝቅተኛ ደረጃ አንፃር» ከሚል ተላውጦ ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች የተመዘገቡ ውጤቶች:: ..................................120

# የሠንጠረዥ ማውጫ


| ተ.ቁ | ይዘት | ገጽ |
|---|---|---|
| ሠንጠረዥ አንድ | በናሙናነት የተወሰዱ ት/ቤቶች ስምና የሚገኙበት መስተዳድር | 28 |
| ሠንጠረዥ ሁለት | በናሙናነት ስለተወሰዱ ተማሪዎች አጠቃላይ ዳራ | 29 |
| ሠንጠረዥ ሶስት | በናሙናነት ስለተወሰዱ መምህራን አጠቃላይ ዳራ | 30 |
| ሠንጠረዥ አራት | የተማሪዎች የፆታ ስብጥር | 35 |
| ሠንጠረዥ አምስት | የዕድሜ ሁኔታ | 35 |
| ሠንጠረዥ ስድስት | የቤተሰብ የቋንቋ አጠቃቀም | 36 |
| ሠንጠረዥ ሰባት | የቤተሰብን የትምህርት ደረጃ | 37 |
| ሠንጠረዥ ስምንት | የቤተሰብ የስራ ሁኔታ | 38 |
| ሠንጠረዥ ዘጠኝ | አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብሩ የሚችሉ ተላውጦዎች | 45 |
| ሠንጠረዥ አስር | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የደረጃ ስብጥር | 47 |
| ሠንጠረዥ አስራ አንድ | የአፈፊቶች ለ5.1 ጥያቂ ምላሽ የሚያመለክት ነው | 48 |
| ሠንጠረዥ አስራ ሁለት | ኢአፈፊቶች ለ5.3 ጥያቂ የሰጡት ዝርዝር ምላሽ | 49 |
| ሠንጠረዥ አስራ ሶስት | ከተማሪዎች የተሰጡ አዎንታዊ አስተያየቶች | 73 |
| ሠንጠረዥ አስራ አራት | ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲጠሉት አድርገናል ብለው ያስቀመጡአቸው ምክንያቶች | 75 |
| ሠንጠረዥ አስራ አምስት | መምህራን በደረጃ ያስቀመጡአቸው ተላውጦዎች | 82 |
| ሠንጠረዥ አስራ ስድስት | የመምህራን አስተያየቶች | 83 |
| ሠንጠረዥ አስራ ሰባት | የመምህራን ምላሾች | 84 |
| ሠንጠረዥ አስራ ስምንት | የመምህራን ምላሾች | 85 |

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the Study)

የመማር ማስተማሩ ሂደት ያለ እንቅፋት እንዲካሄድና አጥጋቢ ውጤት እንዲመዘገብ ተማሪዎች ለሚማሩአቸው ትምህርቶች ያላቸው አመለካከት ወሳኝ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ። ተማሪዎች ለሚማሩአቸው ትምህርቶች ጥሩ አመለካከት ካላቸው በትምህርታቸው ውጤታማ መሆን እንደሚችሉና በአንፃሩ ደግሞ አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ግን ውጤታቸው ዝቅ ከማለቱ ባሻገር በመማር ማስተማሩ ላይ እንቅፋት እንደሚሆኑ ብዙ ጥናቶች አረጋግጠዋል (Neale, et al 1970), Vargas (1972), Medhaine (1986), Littlewood (1992), Aggarwal (1998)፣ ታሪኩ (1988 ዓ.ም))። እንዲሁም አመለካከት እንደፍላጎትና ኀሺ ሁሉ በተማሪዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ባህርይ (Behaviour) ላይ ተፅዕኖ እንዳለው የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ (Fishbein (1967), Cushman and Mephee (1980), Kuppuswamy (1984), Skinner, C.E (1989), Celce-Murcia (1991) እና Cronbach (1963))።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ፖሊሲ ጥናት ጥራዝ አንድ (1981) እንዳስቀመጠው ዘመናዊ ት/ቤት በአገራችን ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ1901 ዓ.ም ነው። ከዚሁ ከዘመናዊ ት/ቤት መከፈት ጋር እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሰጠት የጀመረው የአማርኛ ቋንቋ እስከዛሬ ድረስ በብዙ እርከኖች ውስጥ አልፎ እናገኛለን። ለምሳሌ በ1ኛ እና በ2ኛ ደረጃዎች እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመሰጠት፣ የ1ኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋ በመሆን፣ በ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የአማርኛ ቋንቋ ውጤት እንደወሳኝ (Compulsory) በመወሰድ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። ነገር ግን በ1986 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የወጣውና በአሁኑ ወቅት እየተተገበረ ያለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ደግሞ ለአማርኛ ቋንቋ የሚከተለውን ደረጃ (Status) ሰጥቶት እናገኛለን።

- ቋንቋው እንደ አንድ የትምህርት አይነት የሚሰጥበትን የክፍል ደረጃ በአፈፊት ክልሎችና በኢአፈፊት ክልሎች ለያይቷል።
- የ1ኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋነቱን በመረጡት ክልሎች እንዲወሰን አድርጓል።
- የአማርኛ ቋንቋ የብሔራዊ ፈተና ውጤት በአማራጭነት እንዲያዝ አድርጓል።
- በመሰናዶ ክፍሎች በተለይ በኢአፈፊት ክልሎች በአማራጭነት እንዲሰጥ አድርጓል።
- የመሰናዶ ተማሪዎች ወደከፍተኛ ተቋማት ለመግባት በሚሰጣቸው የመግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ አልተካተተም።

በዚሁ ፖሊሲ መሠረት የአዲስ አበባ መስተዳድር የአማርኛ ቋንቋን ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት አይነት ከማስተማሩ ባሻገር ከ1-6 ላሉት ክፍሎች እንደማስተማሪያ ቋንቋ እየተገለገለበት ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመስተዳድሩ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ ባንፃሩ የኦሮሚያ ክልል የሥራና የአንደኛ ደረጃ (ከ1-8) የማስተማሪያ ቋንቋ ኦሮምኛ ነው፡፡ አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መስጠት የሚጀምረው ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ መሰናዶ ላይ ተማሪዎች ከኦሮምኛና ከአማርኛ አንዱን ብቻ መርጠው ይማራሉ፡፡

በሁለቱ መስተዳድሮች መካከል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ልዩነት እንዳለ ሆኖ፣ ተማሪዎች ከመሰናዶ በኋላ ወደ ከፍተኛ ተቋማት መግቢያ በሚሰጠው ፈተና ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አልተካተተም፡፡ ይህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በፈተናው ውስጥ አለመካተት በተማሪዎች አመለካከት ላይ ያሳደረው ለውጥ ይኖር ይሆን? ለውጡ ካለስ አሉታዊነቱን/አዎንታዊነቱን ይመለከታል? የሚሉት ነጥቦች የዚህ ጥናት አቅራቢ ግንባር ቀደም ጥያቄና የጥናቱ መነሻ ሆነዋል፡፡

የዚህ ጥናት ባለቤት ከላይ የተጠቀቆሙትን እውነታዎች በመያዝ እስከዛሬ ድረስ የተሰሩትን ሥራዎች ለመፈተሽ ጥረት አድርጓል፡፡ የ1986 ዓ.ም የትምህርት ፖሊሲ መተግበር ከጀመረ ወዲህ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት አስመልክቶ ከተደረጉት ጥናቶች መካከል ታሪኩ ፋንታዬ (1988)፣ አበበ ሺፈራው (1990) እና ዳንኤል መኮንን (1992) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ አቶ ታሪኩ "የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት" በሚል ርዕስ ጥናት አካሄደዋል፡፡ አጥኚው ትኩረት ያደረጉት በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሆኖ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚማሩት ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

አበበ ሺፈራው በ1990 በኮተቤ የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ "አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት" በሚል የሰበታ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ታላሚ በማድረግ ጥናታቸውን አካሂደው ነበር፡፡ እንዲሁም ዳንኤል መኮንን በ1992 ዓ.ም በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ኢላማው በሆሳዕና ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሁለት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሆኖ "በሀዲይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በሆሳዕና ከተማ የሚገኙ የሁለት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት" በሚል የተሰራ ስራ ነው፡፡ እነዚህን ሶስት ስራዎች ስመረምር፡-

1. ጥናቶቹ የተመሰረቱት አዲስ በወጣው የትምህርት ፖሊሲና ስልጠና መሠረት በተዘጋጁት መጻሕፍትና መርሃ ግብር ላይ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል በነበሩት መጻሕፍትና መርሀ ግብር ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመሰናዶ ተማሪዎች ለከፍተኛ ተቋማት ለመግቢያ ፈተናነት እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች ለምሳሌ እንደ እንግሊዝኛና እንደሂሳብ ሳይካተት ከቀረ ወዲህ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት የሚገልጽ ጥናት የለም። ስለሆነም የዚህ ጥናት ባለቤት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደከፍተኛ ተቋማት መግቢያነት በሚሰጠው የመግቢያ ፈተና ውስጥ ሳይካተት በመቅረቱ ምክንያት፡-

1.1.1. ተማሪዎች ለቋንቋው ባላቸው አመለካከት ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ይኖር ይሆን?

1.1.2. ይህ ሁኔታ ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት በሆኑትና አፈፊት ባልሆኑት የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ልዩነት ያሳይ ይሆን?

1.1.3. የቋንቋው ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግበያ ፈተና ላይ አለመሰጠቱ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተፅዕኖ አለ?

1.1.4. የቋንቋው ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ላይ አለመሰጠቱ ለቋንቋው ይሰጥ የነበረውን ቦታ (Status) ቀንሶ ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎች በአጥኚው አእምሮ ዘወትር ይመላለሱ ስለነበር፣ ለጥናቱ እንደአነሳሽ ምክንያት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

## 1.2. የጥናቱ አላማ (Objectives of the Study)

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ አመለካከት (Attitude) በመማር ማስተማር ሂደትና ውጤት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ገፅታዎችን ማሳየትና በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎችን (Variables) ማመልከት ነው። ከዚህ አጠቃላይ ግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ዝርዝር አላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

1.2.1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመሰናዶ ተማሪዎች ወደከፍተኛ ተቋሞች ለመግቢያ በሚሰጠው ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ተማሪው ለቋንቋው ባለው አመለካከት ላይ ለውጥ አስከትሎ እንደሆነ ማረጋገጥ።

1.2.2. ይህ በተራ ቁጥር "1" ሥር የተጠቀሰው ሐሳብ ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት እና ኢአፈፊት በሆኑት ተማሪዎች መካከል ልዩነት ያሳይ እንደሆነ ማረጋገጥ።

1.2.3. የቋንቋው ትምህርት ለከፍተኛ ተቋሞች የመግቢያ ፈተና ላይ አለመሰጠቱ፡ የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የፈጠረባቸው ስሜት ካለና ይህ ስሜት በተማሪዎቹ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ካለ ማረጋገጥ።

1.2.4. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ተላውጦዎችን ለይቶ ማሳየት፡- ለምሳሌ ያህል የወላጆች፣ ስለ ቋንቋው የሚነገሩ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች፣ የመማሪያ መጻሕፍት፣ ወዘተ ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study)

አመለካከት እራሱን ብቻ የሚገልጽ የስነልቦና አካል ሳይሆን ከሌሎች የስነልቦና ዘርፎች ለምሳሌ ከባህሪ፣ ከፍላጎት፣ ከተነሳሽነት፣ ከስኬትና ከመሳሰሉት ጋር ተያያዥነት ያለው ዕንሰ ሐሳብ ነው። እነዚህ ዘርፎች እርስ በርስ የተሰናሰሉና የተመረኳኮዙ በመሆናቸው አመለካከትን ማጥናት ስለሌሎች ማውሳትን የሚያጠቃልል በመሆኑ የጥናቱን ውጤት ዘርፈ ብዙ ያደርገዋል። በሌላ መልኩ በ1986 ዓ.ም የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት የመሰናዶ መርሀግብር መተግበር ከጀመረ ገና ሶስተኛ ዓመቱን መያዙ ነው። ስለዚህ በመሰናዶ ተማሪዎች ላይ የሚደረገው ጥናት ወቅታዊ ነው። ከጅምሩ የመርሀ ግብሩን ጠንካራና ደካማ ጐን በጥናት ማረጋገጥ ለፖሊሲው አተገባበር የበኩሉን ድርሻ ሊያበረክት ስለሚችል ጥናቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ስለሆነም፡-

1.3.1. ቋንቋውን አስመልክቶ የወጣው ፖሊሲ በተማሪዎች እና በመምህራን ዘንድ ያገኘውን ምላሽ (Response) ጠቋሚ ነው።

1.3.2. የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከት አስመልክቶ የመጀመሪያ ጥናት ስለሆነ ለወደፊት በስፋት ለሚሰሩ ሥራዎች መነሻ ሊሆን ይችላል።

1.3.3. የመሰናዶ ተማሪዎች ሆነው ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑትም ሆነ ኢአፈፊቶች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ለመገመት ፍንጭ ሰጪ ሊሆን ይችላል።

1.3.4. በትምህርት ፖሊሲው መሠረት ለቋንቋ ገምጋሚዎች አጋዥ መረጃ እንደሚሆን ይገመታል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን (Delimitation of the Study)

ጥናቱ በአዲስ አበባ መስተዳድርና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ሥር ያሉትን የመሰናዶ ተማሪዎች በሙሉ አላጠቃለለም። ኦሮሚያ ውስጥ ካሉት 14 ዞኖች መካከል በኢላማ የናሙና (Purposive sampling) የአመራረጥ ዘዴ የተመረጠው የምስራቅ ሸዋ ዞን ነው። ስለዚህ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት በአዲስ አበባና በምስራቅ ሸዋ ዞን ሥር የሚገኙ የመንግስት የመሰናዶ ት/ቤቶች ብቻ ናቸው። ከአዲስ አበባ እና ከምስራቅ ሸዋ ትምህርት ቢሮዎች በተገኘው መረጃ መሠረት በአዲስ አበባ 10፣ በምስራቅ ሸዋ 10 በድምሩ 20 የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል ከአዲስ አበባ መስተዳድር ሁለት፣ ከምስራቅ ሸዋ ሶስት በድምሩ አምስት የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ተካትቷል።

በሌላ መልኩ ጥናቱ በአዲስ አበባ መስተዳድር ሥር የሚገኙትን የአማርኛ ቋንቋ አፈፊቶችንና በምስራቅ ሸዋ ሥር የሚገኙትን ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት የሚያነጻጽር ነው። ስለሆነም ከአዲስ አበባ በጥናት ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ብቻ ሲሆኑ፣ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ደግሞ ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት የሆኑ ተማሪዎች ብቻ ተካትቷል።

## 1.5. የጥናቱ ውስንነት (Limitation)

የጥናቱ ወሰን መንግስታዊ በሆኑ ት/ቤቶች ላይ ሆኖ፣ ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ የአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎችና ለቋንቋው ኢአፈፊት የሆኑ የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች ብቻ ኢላማ እንዳደረገ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ነገር ግን ለሁለቱም አይነት ተማሪዎች የናሙና አወሳሰዱ ከአንድ መስተዳደር ስር ካሉት ት/ቤቶች መሆን የሚገባ ቢሆንም፣ ከአዲስ አበባ በቂ የኢአፈፊት ቁጥር ማግኘቱ በማጠራጠሩ የምስራቅ ሸዋ ዞን ተተኪ ሆኗል።

ከሁለቱ የአዲስ አበባ የመሰናዶ ት/ቤቶች ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት ከሆኑት የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ሁለት መቶዎቹ በነሲብ ናሙና የተወሰዱ ናቸው። ለቋንቋው ኢአፈፊት የሆኑ የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች ግን የተወሰዱት በፈቃደኝነት ነው። እንደ ት/ቤቶቹ አመራረጥ ሁሉ የተማሪዎቹ አወሳሰድም ከአዲስ አበባው ይለያል። ይህ የሆነበት ምክንያት፡-

1ኛ በየት/ቤቶቹ የኢአፈፊት ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በነሲብ ናሙና ለመውሰድ አላስቻለም።

2ኛ ካሉትም መካከል ፈቃደኛ የሆኑትን ብቻ መርጦ መውሰድ የግድ የሆነበት ምክንያት፣ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ኦሮሚያ ክልል ውስጥ ባሉት ት/ቤቶች አካባቢ ያለመረጋጋት ሁኔታ ስለነበረ፣ ጥናቱ እንዳይደናቀፍና በሥራው ላይ ሌላ ችግር እንዳያስከትል ታስቦ ነው፡፡

በእርግጥ በፈቃደኝነት በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ለቋንቋው ኢአፈፊት መሆናቸው ከየግል ማህደራቸው የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ይልቅ የአማርኛ ቋንቋን መርጠው መግባታቸው በቋንቋው ላይ ያላቸውን አመለካከት ይበልጥ አዎንታዊ ሊያደርግ መቻሉ በጥናቱ ላይ የሚገነባረቁ ውስንነቶች ናቸው፡፡

## 1.6. ስያሜ ቃላት

| | |
|---|---|
| ልቅ አጠያየቅ | Open form |
| መሰናዶ | Preparatory |
| ማህበራዊ | Social |
| ማስተዋወቅ | Advertising |
| ምላሽ | Response |
| ስሜታዊ | Affective |
| ስሜት | Feeling |
| ስነአእምሮ | Psychology |
| ስነትምህርት | Education |
| ቀመር | Formula |
| በደረጃ ማስቀመጥ | Ranking |
| ባህሪያዊ | Behavioural |
| ተላውጦች | Variables |
| ተስተምህሮ | Learning |
| ገሺ | Motivation |
| አሉታዊ አመለካካት | Negative attitude |
| አላባዊያን | Elements |
| አመለካከት | Attitude |
| አማካይ ነጥብ | Mean |
| አስተምህሮ | Teaching |
| አዕምሮታዊ | Cognitive |

| | |
|---|---|
| አዎንታዊ አመለካከት | Positive attitude |
| አግባቢ ተግባቦት | Persuasive communication |
| አፈ.ፈ.ት | First Language |
| ኢ.አፈ.ፈ.ት | Second language |
| ከፊል-ሥርዓታዊ | Semi-structured |
| ከፊል-ወሰን | Semi-closed |
| ከፍተኛ ተቋም | Higher commission |
| ወሰን | Delimitation |
| ወሳኝ | Compulsory |
| ውስን አጠያየቅ | Closed form |
| ውስጣዊ ንሺ. | Integrative motivation |
| ውጤት፣ ስኬት | Achievement |
| የመግቢያ ፈተና | Entrance Examination |
| የዓላማ ናሙና | Purposive Sampling |
| ደረጃ፣ ቦታ | Status |
| ግለሰባዊ | Individual |
| ፍላጎት | Interest |

## 1.7. የአዲስ አበባ መስተዳድርና የምስራቅ ሸዋ ዞን አጭር ቅኝት

ከመስተዳድሩና ከት/ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ የራሱ መስተዳድር ያለው ሆኖ በከንቲባ የሚተዳደር ነው:: አዲስ አበባ የፌደራሉ መንግስት ዋና ከተማ ከመሆኑ ባሻገር የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት፣ ልዩ ልዩ አለምአቀፋዊ ድርጅቶችና፣ የተለያዩ አገሮች ኤምባሲዎች የሚገኙበት ከተማ ነው:: መስተዳድሩ በ10 ክፍለ ከተሞችና በ203 ቀበሌዎች ይከፈላል:: በ1996 ዓ.ም እስታትስቲካዊ መረጃ መሠረት አዲስ አበባ ወደ 3 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርበት ከተማ ነው:: በትምህርት ተቋማት በኩል በከተማው ውስጥ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ሥራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅና በርከት ያሉ የግል ኮሌጆች ይገኛሉ:: ከዚህም በተጨማሪ 10 የመሰናዶ ት/ቤቶች፣ 10 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤቶች፣ 20 የመንግስትና 47 የግል 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በድምሩ 67 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አሉ:: እንዲሁም 20 የመንግስት፣

68 የሕዝብና 177 የግል በድምሩ 265 የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሲገኙ፣ ወደ 316 የሚሆኑ አፀደ ሕፃናት አሉ።

የአዲስ አበባ መስተዳድር የሥራና የትምህርት ቋንቋ አማርኛ ሲሆን፣ ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው። የአማርኛ ቋንቋ ግን እንደ አንድ የትምህርት አይነት ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ይሰጣል።

ከምስራቅ ሸዋ ዞን ት/ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት የምስራቅ ሸዋ ዞን በኦሮሚያ ውስጥ ከሚገኙት 14 ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን፣ በውስጡ አንድ ልዩ ዞንና 12 ወረዳዎችን ያቀፈ ሆኖ ዋና ከተማው ዝዋይ ነው። የዞኑ የሕዝብ ብዛት ወደ 2,120,000 ይገመታል። ልዩ ዞኑ አዳማ (ናዝሬት) ከተማ ሲሆን፣ የክልሉም የልዩ ዞኑም ዋና ከተማ ነው። በከተማው ክልል የናዝሬት ቴክኒክ ኮሌጅ፣ የአዳማ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅና የተለያዩ የግል ኮሌጆች ይገኛሉ። በምስራቅ ሸዋ ዞን ስር 10 የመሰናዶ ት/ቤቶች 7 የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ት/ቤቶች፣ 17 የመንግስት፣ 10 የግል በድምሩ 27 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና 244 ያህል የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይገኛሉ።

የክልሉ (የዞኑ) የሥራና የትምህርት ቋንቋ ኦሮምኛ ነው። የኦሮምኛ ቋንቋ ትምህርት እስከ 10ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት አይነት ከመሰጠቱ ባሻገር በመሰናዶ ክፍሎች ከአማርኛ ጋር በአማራጭነት ይሰጣል። ለኦሮምኛ ቋንቋ ኢአፈፊት ለሆኑ ተማሪዎች አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል። ትምህርታቸውን በኦሮምኛ ለሚከታተሉ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መማር የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል ጀምሮ ሲሆን፣ አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋቸው ለሆኑት ግን ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ስር ለመዳሰስ የተሞከሩት ይዘቶችና አደረጃጀታቸው የሚከተለውን ይመስላል:: መጀመሪያ ላይ የመሰናዶ መርሀ ግብር ምንነት ገና ብዙም ያልተለመደ በመሆኑ ስለመርሀ ግብሩና ስለተማሪዎች ማንነት ባጭሩ ይጠቁማል:: በመቀጠል ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በመሆኑ ስለቋንቋው ዳራ መጠነኛ ዳሰሳ ያደርጋል:: ክለሳ ድርሳኑ በቀጥታ ወደ አመለካከት ከመግባቱ በፊት ስነአዕምሮ በስነትምህርት ውስጥ ስላለው ሚና ግንዛቤ ያስጨብጣል:: ከዚያም ከአመለካከት ምንነት አንስቶ፣ ለምን እንደሚጠና፣ የአመለካከት ምንጮች ምን ምን እንደሆኑና አመለካከት እንዴት እንደሚለካ ይጠቁመናል:: ከዚህም በተጨማሪ አመለካከት 2ኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚናና ተዛማጅ ሥራቸውን ያስቃኘናል::

### 2.1. የመሰናዶ መርሀ ግብር ምንነትና የመሰናዶ ተማሪዎች ማንነት

በ1986 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት በወጣው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ. መሠረት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች የሚከተሉት እርከኖች አሏቸው:: አንደኛ ደረጃ ከ1-8 ያሉትን ክፍሎች ያቀፈ ሆኖ በሁለት ሳይክል ይከፈላል፡ ከ1-4 ያሉት ክፍሎች በሳይክል አንድ ስር ሲጠቃለሉ ከ5-8 ያሉት ደግሞ ሳይክል ሁለት ስር ይጠቃለላሉ:: የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ከ9-12 ያሉትን ክፍሎች የያዘ ሆኖ 9 እና 10 ሳይክል አንድ፣ 11 እና 12 ሳይክል ሁለት ናቸው:: በዚህ የትምህርት እርከን መሠረት በ2ኛ ደረጃ በ2ኛ ሳይክል ላይ የሚሰጡት ትምህርቶች ተማሪዎችን ለከፍተኛ ተቋማት የሚያዘጋጁ የትምህርት ደረጃዎች ናቸው:: እነዚህ የትምህርት ደረጃዎች በሌላ አነጋገር የመሰናዶ መርሀ ግብር በመባል የሚታወቁ የትምህርት እርከኖች ናቸው::

ተማሪዎች የ2ኛ ደረጃ 1ኛ ሳይክልን እንደጨረሱ ወደሚቀጥለው ሳይክል ለመሸጋገር አገር አቀፍ የብሔራዊ ፈተና ይወስዳሉ:: በዚህ ብሔራዊ ፈተና፣ ወደ መሰናዶ የሚያስገባውን ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ የ2ኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል ትምህርት ለመከታተል ዕድል ያገኛሉ:: በእነዚህ በተጠቀሱት ሂደት ውስጥ አልፈው የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት ተማሪዎች የመሰናዶ (Preparatory) ተማሪዎች በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ ተማሪዎች የመሰናዶውን ትምህርት ለሁለት ዓመታት ከተከታተሉ በኋላ ወደከፍተኛ ተቋም የሚያስገባውን የመግቢያ ፈተና ይወስዳሉ:: ፈተናውን ያለፉት ተማሪዎች በየተቋማቱ ይደለደላሉ:: እነዚህ ተማሪዎች ቀደም ሲል በከፍተኛ

ተቋማት ይሰጥ የነበረውን የጀማሪ መርሀ ግብር ሳይማሩ በቀጥታ ወደመረጡት ክፍለ ትምህርት የሚገቡ ናቸው።

## 2.2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዳራ

### 2.2.1. የአማርኛ ቋንቋ እንደትምህርት አይነት

Punkhurst (1976) እና የኢሕዲሪ የትምህርት ፖሊሲ ጥናት ጥራዝ አንድ (1981) እንዳሰፈሩት ዘመናዊ ት/ቤት በአገራችን ተከፍቶ ሥራ የጀመረው እ.ኤ.አ. ከ1901 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ሰነዱ እንደሚያስረዳው የማስተማሪያ ቋንቋው ፈረንሳይኛ ሆኖ፣እንግሊዝኛ ፣ጣሊያንኛ፣ አማርኛ፣ አረብኛ ... እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጡ ነበር። በዚህ መሠረት ከዘመናዊ ትምህርት ጋር እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሰጠት የጀመረው የአማርኛ ቋንቋ የ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መተግበር እስከጀመረበት 1987 ዓ.ም ድረስ በመላ አገሪቱ ውስጥ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች ትምህርቱ ይሰጥ እንደነበረ ለማረጋገጥ ተችሏል። የ1986 ዓ.ም የትምህርት ፖሊሲ መተግበር ከጀመረ ወዲህ ያለው ሁኔታ ግን ከበፊቱ ይለያል። ቋንቋው እንደትምህርት አይነት የሚሰጥበት የትምህርት ደረጃ ከክልል ክልል ይለያያል። በአማራ ክልል፣ በአዲስ አበባ መስተዳድር፣ በድሬዳዋ ካውንስልና በቤንሻንጉል ክልል አማርኛ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል። እንዲሁም በሌሎች ክልሎች ለክልሉ ቋንቋ ኢአፈፊት ለሆኑትና የማስተማሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑ ተማሪዎች ቋንቋው በትምህርት አይነት ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ይሰጣል። ነገር ግን ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት ለሆኑት ክልሎች ከኦሮሚያ በስተቀር ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ይሰጣል። በመሰናዶ ክፍሎችም በአማራጭነት ይሰጣል። ቀደም ሲል በምስራቅ ሸዋ ዞን ቅኝት ስር እንደተጠቆመው በኦሮሚያ የአማርኛ ቋንቋ መሰጠት የሚጀመረው ከአምስተኛ ክፍል ነው።

### 2.2.2. አማርኛ እንደማስተማሪያ ቋንቋ

የ1981 ዓ.ም የትምህርት ፖሊሲ ጥናት ጥራዝ አንድ፣ ሙሉ እመቤት (1989) እና ኃይሉ (1995) እንደገለፁት ከ1901 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ የዘመናዊ ትምህርት የማስተማሪያ ቋንቋ ፈረንሳይኛ ነበር። ይኸውም በወቅቱ ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራት የሚያመላክት ነው። የኢጣሊያ ወራሪዎች ከአገራችን ከተባረሩ በኋላ ግን ሁኔታዎች ተለውጠው እናገኛለን። ወራሪዎችን ከአገራችን ለማባረር የኢትዮጵያ መንግስት ከእንግሊዝ መንግስት ጋር በፈጠረው ወዳጅነት መንስኤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፈረንሳይኛን እንዲተካ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1953 ዓ.ም በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች እንግሊዝኛ የማስተማሪያ ቋንቋ ነበር። በተለይ ትምህርት ሚኒስቴር ጥራዝ አንድ (1981) እንደሚያብራራው ከ1954 ዓ.ም እስከ 1956 ዓ.ም ግን ከ1ኛ-

3ኛ ክፍል ባሉት ደረጃዎች አማርኛ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ እንደነበረ ይገልፃል፡፡ በሌላ መልኩ በ1936 ዓ.ም የትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ባወጣው ድንጋጌ መሰረት ሚሲዮናውያን ሚኒስቴሩ በሚሰጣቸው ፈቃድና መመሪያ መሰረት ትምህርትን በአማርኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ተደርጓል፡፡

የማስተማሪያ ቋንቋን አስመልክቶ ሌላ የምናገኘው መረጃ በ1956ዓ.ም በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር የወጣውና እንደ ስርአተ ትምህርት ይቆጠር የነበረው ደንብ ነው፡፡ በዚህ ደንብ (ስርአተ ትምህርት) መሰረት አማርኛ ከ1-6 ላሉት ክፍሎች የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን፣ ከ7 ክፍል ጀምሮ ግን እንግሊዝኛ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ይህ የወጣው ደንብ የ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መተግበር እስከጀመረበት 1987 ዓ.ም ድረስ ሥራ ላይ ውሎ ነበር፡፡

ከአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ በኋላ ግን ሁኔታዎች ተለውጠው እናገኛለን፡፡ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ (1994) በሚል የትምህርት ሚኒስቴር መጽሔት ላይ እንደሰፈረው አማርኛ እንደማስተማሪያ ቋንቋ የሚያገለግለው በተወሰኑ ክልሎችና መስተዳድሮች ብቻ ነው፡፡ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ እስከ ስድስተኛ ክፍል፣ በአማራና በቤኒሻንጉል ክልሎች ለ1ኛ ደረጃ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በሐረሪና በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ለክልል ቋንቋ ኢአፈፊት ለሆኑት ተማሪዎች የ1ኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሁሉ ክስተቶች በቋንቋው ትምህርት ላይ የሚያስከትሉት ስነአዕምሮ ጫና ይኖር ይሆን? ይህንን ሁኔታ በቀጥታ በቋንቋው ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የአመለካከት ለውጥ ከማየታችን በፊት፣ ስነአዕምሮ በስነ ትምህርት ውስጥ ያለው ድርሻ በአጭሩ መመልከቱ ይመረጣል፡፡

## 2.3. ስነአዕምሮ በስነትምህርት (Education) ውስጥ ያለው ሚና

ስነአዕምሮ በስነትምህርት ውስጥ ወደሚጫወተው ድርሻ ለመግባት ስነአዕምሮ (Psychology)፣ የስነትምህርት (Education) እና የተስተምህሮ (Learning) ምንነት በቅድሚያ ማየቱ ይመረጣል፡፡

"Psychology" የሚለው ቃል ከሁለት የግሪክ ቃላት ማለት "Psyche" እና "Logos" ከሚሉት እንደተገኘና ፍቺውም Psyche-mind(soul), logos-study (line of teaching) ሆኖ የአዕምሮ ጥናት (Study of the mind) እንደነበረ Malim and Birch (1998) ያስረዳሉ፡፡ ስነልቦና ቀደም ሲል የፍልስፍና ትምህርት ዘርፍ አካል እንደነበረና በኋላ ላይ ከጀርመናዊው Wilhelm Wundt የ1879 የስነአዕምሮአዊ የላቦራቶሪ ሙከራ በኋላ እንደ አንድ ትምህርት (Discipline) እንደተቆጠረ (Chauhan (1996) ,Malim and Birch (1998), Aggarwal (1998))

ይጠቀሙናል፡፡ከዚህ መረዳት የምንችለው ስነአዕምሮአዊ እንደ አንድ ሳይንሳዊ ዲሲፕሊን መታወቅ የጀመረበት ዘመን ቅርብ መሆኑን ነው፡፡

Chauhan (1996) የስነትምህርት ምንነትን ሲገልጹ፡- ስነትምህርት በሰፊው ሲታይ አንድ ዜጋ ተፈላጊውን ልማድ፣ ክሂልና አመለካከት እንዲጨብጥ የማድረጊያ መንገድ ነው፡፡ በጠባቡ ሲታይ ደግሞ በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ (ት/ቤት ማለት ነው) የልጆች ባህሪ በሚፈለገው መልክ የሚቀረጽበት ወይም የሚጎለብትበት ሁኔታ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ Aggarwal (1998)ም በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡ በጥቅሉ ስነትምህርት መሠረታዊ እውቀት የሚያስጨብጥ፣ አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ የሚጥር፣ ከማህበረሰባዊ የሕይወት ዳራ (ገጠመኝ) ጋር የሚያስተዋውቅ ... መስክ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መንገድ Russell በSkinner (1989) ስነትምህርትን ሲገልጹ የስነትምህርት ተግባር የነበረው አሉታዊ አመለካከት የሚለወጥበትና አዲስ አዎንታዊ አስተሳሰብ በተማሪው ውስጥ እንዲፈጠር የማድረግ ሂደት ነው ይሉናል፡፡

ተስተምህር የባህሪ ለውጥ ነው፤ ስለዚህ የመምህሩ ተግባር የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው በማለት Vargas (1972) ደግሞ ምንነቱን ይገልፃሉ፡፡ Kuppuswamy (1984) ተስተምህር አንድ ነገር (ሰው) ከሁኔታዎች ጋር በሚያደርገው ተራክቦ የሚለመደው አዲስ ባህሪ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ግለሰቡን ከቀድሞ የተሻለ አስተሳሰብ እንዲኖረው ወይም ልቆ እንዲገኝ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ስለዚህም ተስተምህሮ የአዲስ አስተሳሰብ፣ የአዲስ እውቀት ማግኛ ትልም እንደሆነ ይቆጥሩታል፡፡

ስነአዕምሮ፣ የስነትምህርትና የተስተምህሮ ምንነትን አስመልክቶ መጠነኛ ግንዛቤ ከያዝን ስነአዕምሮ በተለይም የስነትምህርት ስነአዕምሮ (Educational Psychology) በክፍል ውስጥ በሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ባጭር ባጭሩ እንደሚከተለው ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

ስነአዕምሮ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ድርሻ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወሳኝም ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊጨበጥ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ በተሳካ ሁኔታ ከግብ ለማድረስ መምህሩ ከስነአዕምሮ አንፃር ተማሪውን ለይቶ ሊያውቀው ይገባል በማለት Aggarwal (1998) ያስቀመጣቸው ነጥቦች አሉ፡፡

- የተማሪውን ታሪካዊ ዳራ መመርመር፣
- የትምህርት አቀባበላቸው ምን ይመስላል? ሰብዕናቸውስ (Personality)?
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ያላቸው ማህበራዊ ግንኙነት፣
- በክህሎታቸው ላይ እየታየ ያለው ለውጥ፣
- የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን እንዴት አልፎአቸዋል?

የሚሉት ነጥቦች በተለያዩ መንገድ (ዘዴዎች) መታየት እንዳለባቸው ያሳስባሉ፡፡ ከዚህ ሌላ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ንሺ. ወዘተ የስነአዕምሮ አላባውያን (Elements) በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው Russell in Skinner (1989), Cunningsworth (1984), Kuppuswamy (1984), Neale, et al (1970) በሚገባ ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ. ካንግዎርዝ ንሺ.ን በሚመለከት አንድ አባባል አላቸው፡፡ "ከፍተኛ ንሺ. ያለው ተማሪ በጥሩ ሁኔታ ባይማርም ንሺ. ሳይኖረው በጥሩ ሁኔታ ከተማረው ተማሪ የተሻለ መስራት ይችላል (1984:59)" በማለት ንሺ. ለተማሪው ውጤት ማማር ያለውን የላቀ ድርሻ ይገልፃሉ፡፡ Kuppuswamy በበኩላቸው የስነአዕምሮ እና የስነትምህርትን ግንኙነት አስመልክተው "ስነአዕምሮ ለስነትምህርት ፊዚክስና ኬሚስትሪ ለእንጂነርንግ፣ ኬሚስትሪና ባዮሎጂ ለሕክምና ትምህርት የሚሆኑትን ያህል ማለት ነው" (1984:3) በማለት እንጂነርንግ ያለፊዚክስና ኬሚስትሪ እውቀት እንደማይሞከር ሁሉ ካለአዕምሮ ትምህርት የማይታሰብ እንደሆነ ያስገነዝቡናል፡፡ እኒሁ ተመራማሪ ስነአዕምሮ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ውጤትን ለመገምገም እንደሚረዳ፣ የስነትምህርት ስነአዕምሮ አላማ የተሻለ አስተምህሮ እና ተስተምህሮ ሊያሰፍን ከሚችለው መርህ አተገባበር አኳያ፣ እንዲሁም በቅድመ ትምህርትም ሆነ በትምህርት ላይ በልጆች መካከል ልዩነቶች (Individual Differences) ግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ያስገነዝቡናል፡፡

ለማጠቃለል ያህል የትምህርት ትልቁ ግብ በማንኛውም መልኩ አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ከስነአዕምሮ አንፃር እያንዳንዱ ተማሪ ምን ነበር? ምን እንዲሆን ይፈለጋል? እንዴትስ ሊተገበር ይችላል?... ወዘተ የስነአዕምሮ ጥያቄዎች በሂደት ምላሽ ካላገኙ የታለመው ግብ ላይመታ ነው፡፡

## 2.4. አመለካከት (Attitude) ምንድን ነው?

Allport፣በFishbein (1967) እና Roger and Houghton (1995) ስለአመለካከት ሲገልጹ ከቃሉ ስያሜ ጀምሮ ቁርጥ ያለ ፍቺ ለመስጠት እንደብዙዎች የስነአዕምሮ አባባሎች አስቸጋሪ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ የቃሉ አመጣጥ "Aptus" ወይም "Aptitudo" ከሚለው የላቲን ቃል እንደሆነና ፍቺው "Fitness" ወይም "Adaptedness" ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ቅድመ ችሎታ (Aptitude) እና አካላዊ ብቃት (Posture Fitness) ይወስደናል፡፡ ይሁን እንጂ የስነ-አዕምሮ ሰዎች ቃሉን ከዝንባሌ፣ ዝግጁነት ወዘተ አንፃር ይገለገሉበት እንደነበር ያብራራሉ፡፡

ስለቃሉ አመጣጥና አጠቃቀም መጠነኛ ግንዛቤ ከያዝን እስቲ አንዳንድ ምሁራን ለአመለካከት የሰጡትን ፍቺ (Definition) እንመልከት፡፡

አመለካከት ነገሮችን ምን ያህል እንደምንወዳቸው ወይም እንደምንጠላቸው የሚጠቁም ነው (Morgan, et al, 1986:382)፡፡

አመለካከት ውስብስብና መላምታዊ ሆኖ በውስጡ ግምገማዊ እሳቤን ያዘለ ነው (Anastasi, 1976:543) ።

Lambert and Lambert (1964), Rokeach in International Encyclopedia of Social Science (1968), Gagne (1977) እና Malim and Birch (1998) አመለካከት የተደራጀና ተከታታይነት ያለው ሰዎችን፣ ቡድኖችን፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን ባጠቃላይ በአካባቢው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ አዕምሮታዊ፣ ስሜታዊና ባህርያዊ ክስተት እንደሆነ ይገልፃሉ።

ከነዚህ ፍቺዎች መገንዘብ እንደሚቻለው አመለካከት አዕምሮአዊና ስሜታዊ (Mental and Neural) ዝንባሌ በመሆኑ ረቂቅ ነው። ረቂቅ በመሆኑም በቀጥታ የማይታይና ለመለካት አስቸጋሪ የሆነ ነገር ነው። ከዚህ በተነሳ አመለካከት ስለአንድ ነገር ወይም ሁኔታ ካለን ግንዛቤ ወይም መረጃ በመነሳት የምንይዘው ግምገማዊ አስተሳሰብ ነው።

አመለካከት አብሮን የሚወለድ ነገር ሳይሆን በዕድገት ሂደት የምናዳብረው ጉዳይ እንደሆነ Fishbein (1967), Kuppuswamy (1984), Roger and Houghton (1995) እና Aggarwal (1998) ያረጋግጡልናል። አመለካከት ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን ወዘተ የመውደድ/የመጥላት፣ የመደገፍ/አለመደገፍ፣ የመቅረብ/የመራቅ...ዝንባሌ፣ ስሜት፣ ወይም እርምጃ ነው። እነዚህ ባህርያት ደግሞ በውስጣችን ሊጠነሰሱ የሚችሉ እራሳችንንና አካባቢያችንን ለይተን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ይነሱና በሂደት የምናዳብራቸው ነገሮች ይሆናሉ።

## 2.4.1. አመለካከት ለምን ይጠናል?

Jahoda and Warren (1966) Allport (1935)ን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት በአመለካከት ላይ የሚደረገው ጥናት ለማህበራዊ ስነአዕምሮ ግንባታ የመጀመሪያው መሠረተ ድንጋይ እንደሆነ ይገልፃሉ። ማህበራዊ ስነአዕምሮ በስነትምህርትና በሌሎች መስኮች ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አንፃር አመለካከት ደግሞ ለዚህ ግዙፍ መስክ የመሠረት ድንጋይ ነው። በመሆኑም ምንነቱን፣ ጠቀሜታውን፣ መንስኤዎቹን ወዘተ በጥናት መለየት የበለጠ አስፈላጊነቱን ያጎላዋል የሚል እምነት ያሳድራል።

Neale, et al (1970) ለአመለካከት ቦታ የሚሰጠው ተማሪው ለትምህርት ካለው ንሺ (Motivation) እና በትምህርቱ ከሚያስመዘግበው ውጤት (Achievement) ጋር የጠበቀ ትስስሮሽ ስላለው ነው ይሉናል። ተማሪው አዎንታዊ አመለካከት ካለው ለትምህርቱ ንሺ ይኖረዋል፤ ጥሩ ንሺ ያለው ተማሪ ደግሞ ውጤታማ የማይሆንበት ምክንያት የለም (Gardner, 1968)። አመለካከትን አስፈላጊ ከሚያደርጉት ነጥቦች አንዱ ባህሪን (Behavior) አቅጣጫ የሚያስይዝ በመሆኑ ነው (Morgan, et.al. 1986)። ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረው አመለካከት በግልጽ የሚታይ ወይም በቀጥታ የሚለካ ባለመሆኑ፣ በባህርይ

አማካይነት ይንፀባረቃል፡፡ ስለዚህ በአንድ ግለሰብ ውስጥ ያለው በጎም ሆነ በጎ ያልሆነ አመለካከት ግለሰቡ ለሚያንፀባርቃቸው ባህርያት እርሾ ይሆኑታል፡፡ እንዲሁም Kundu and Tutoo (1988:520) የአመለካከትን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ "ለምናደርገው ነገር ትክክለኛ አመለካከት ከሌለን ሊኖረን የሚችለው ብቃት ውጤት ያን ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የግማሽ ልብ ሥራ ስለሆነ ነው" በማለት አመለካከት ምን ያህል በሚኖረን ብቃትና በምናስመዘግበው ውጤት ላይ ጫና መፍጠር እንደሚችል ያስረዱናል፡፡

አንድን የተስተምህሮ መርሀ ግብር ከግብ ለማድረስ በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ አመለካከት፣ ባህሪ፣ ፍላጎት፣ ንሺ፣ ስኬት ወዘተ የስነልቦና አላባውያን እርስ በርስ የተመረኳኮዙና የተሰናሰሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ አመለካከት ከቀሩት ጋር ያለውን ተያያዥነት አስመልክተው Morgan, et.al. (1986) እና Fernaldand Fernald (1999) አመለካከት ቀድሞ በመምጣት ባህሪ እንዲከሰት እንደሚያደርግ ይገልፁታል፡፡ ከዚህም ባሻገር እንደፍላጎት ሁሉ አመለካከት የግለሰብን ባህሪ ወደ ዝንባሌው እንደሚወስደው ይጠቁሙናል፡፡ Kuppuswamy (1984) እንዲሁ አመለካከት በግለሰብ ባህሪ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል በግልጽ ያስቀምጣሉ፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ Kuppuswamy ንሺ በስነ ትምህርት ውስጥ ድርሻው የላቀ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ይኸውም በተማሪው ዘንድ የማጥናትና የሌሎች እንቅስቃሴዎችን ፍላጎት የማስረጽና የማነሳሳት ሚና እንደሚጫወት ነው የሚገልጹልን፡፡ በሌላ በኩልም Spolsky (1969) አመለካከት በ2ኛ ቋንቋ ተስተምህሮ ውስጥ የተማሪውን የስኬት ደረጃ ከሚገልጹት ፊርጆች አንዱ እንደሆነ ይጠቁሙናል፡፡ እንዲሁም ንሺ በተለይ ውስጣዊ ንሺ (Integrative motivation) ለተማሪው ስኬት ትልቅ ድርሻ እንዳለው Gardner (1968) በሰፊው ያብራራሉ፡፡ Littlewood (1992)ም በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ፡፡ ከነዚህ መንደርደሪያ ሃሳቦች በመነሳት አመለካከት፣ ባህሪ፣ ፍላጎት፣ ንሺና ስኬት በተስተምህሮ ሂደት ውስጥ እርስበርስ የተቆላለፉ የእያንዳንዱ ሁኔታ በሌላው ውስጥ የሚንፀባረቅ፣ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ውጤቱ የሁሉም ድምር ውጤት እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ስለሆነም አመለካከት ከሌሎች የስነአዕምሮ አላባውያን (Elements) ጋር ካለው ቁርኝት አንፃር መጠናቱ ስለሌሎች አላባዊያን ለማወቅ አጋዥ በመሆኑ ዛሬ በትኩረት የሚጠና መስክ በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

## 2.4.2. የአመለካከት ምንጮች

ደረጃቸው ይለያይ እንጂ ለአመለካከት በውስጣችን መፈጠር መነሻ የሚሆን ብዙ ነገሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በተለይ እስከ ወጣትነት ዕድሜ (Adolescent Age) ላሉት ወላጆች፣ ባህል፣የእድሜ እኩዮች፣ ቀጥተኛ ተጋልጦ (Direct experience)፣ መምህራንና አይቶ መኮረጅ

(Observation and Imitation) ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Sills in International Encyclopedia of Social Science (1968), Atkinson, et al (1987), Roger and Hougton (1995), Malim and Birch (1998))::

ወላጆች ልጆቻቸው ከተወለዱበት ዕድሜ አንስቶ እራሳቸውን እስከሚችሉበት ድረስ ለአነጋገራቸው ፣ ለፍቅርና ጥላቻቸው፣ ለእምነታቸው፣ ለአለባበሳቸው ወዘተ ምንጮች ብቻ ሳይሆኑ ሞዴሎች ናቸው:: የህብረተሰቡ ማህበራዊ አኗኗር፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ እምነት፣ የበዓላት አከባበር፣ የሚከተሉአቸው ስነሥርዓቶች፣ ታሪክ፣... ለእያንዳንዳችን አስተሳሰብ ስሜቶችና ክንውኖች ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ:: ወጣቶች ዕድሜያቸው እየጨመረ በሔደ ቁጥር የዕድሜ እኩዮች (Peer groups) የሚያሳድሩባቸው ተፅዕኖዎች ቀላል አይሆኑም":: አለባበስን፣ አነጋገርን፣ መጥላትንና መውደድን ዝንባሌን ወዘተን ከብጤዎች መኮረጅ የተለመዱና የወጣት ባህርያት ናቸው:: ለመዝናናትም ሆነ የፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያረካቸው ከእኩዮቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር መሆን ነው:: ይህም አብሮነት ደግሞ የፍላጐት፤ የእምነት፤ የአመለካከት ወዘተ መጋራትን እንደሚያስከትል መገንዘብ እንችላለን:: መምህራንም ከዕውቀት አባትነት ባሻገር ተማሪዎች ጥሩ ስነምግባር እንዲኖራቸው፤ አገር ወዳድ፤ ተፈጥሮን አድናቂ ወዘተ መሆን ይችሉ ዘንድ በባሕሪይ ቀረፃ ረገድም ለተማሪዎቻቸው አርአያና ተምሳሌት ናቸው:: በአጠቃላይ ከቤተሰብ አንስቶ አካባቢ፤ ሕብረተሰብ፤ የእምነት ቦታ፤ ትምህርት ቤት፤ ጓደኛ የየእለት ገጠመኞች ለአመለካከታችን ምንጮች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል::

## 2.4.3. ለአመለካከት መለወጥ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች

Roger and Houghton (1995) አንድ የሚሉን ነገር አላቸው:: አመለካከት አንዴ በውስጣችን ከዳበረ ወይም ስር ከሰደደ ለውጥን የመቋቋም ሃይል ይኖረዋል:: ይሁን እንጂ የአንዳንድ ሁኔታዎች ግፊት ለውጡን እንድንቀበል የሚያደርግበት አጋጣሚ አለ:: እነሮጀርም ቢሆኑ አመለካከት አይለወጥም አይሉም፤ ነገር ግን አንድ ነገር እንድናጤን አድርገውናል:: ይኸውም በአንዳንድ ነገር ላይ ያለን አመለካከት በቀላሉ ሊለወጥ አለመቻሉ ነው:: በግለሰብ ደረጃም ቢሆን ለአመለካከት ለውጥ እራስን የማዘጋጀትና አለማዘጋጀት ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ጠቋሚ የሆኑ ሐሳቦች ናቸው:: በተጨማሪ Sherif et.al. (1965), Sills in International Encyclopedia of Social Science (1968), Morgan, et.al. (1986) አመለካከት ሊለወጥ እንደሚችል ጥናታቸው ያስረዳናል:: Russel in Skinner (1989) በበኩላቸው ከልምድ እንደታየው አመለካከት እንደሚሻሻል የተረጋገጠ ነው ይላሉ:: በነዚህ ምሁራን አተያይ አመለካከት ከከፍተኛ አዎንታዊነት ወደአሉታዊነት፣ ከከፍተኛ አሉታዊነት ወደ አዎንታዊነት ሊለወጥ መቻሉን በግልጽ አስፍረዋል::

አመለካከት ሊለወጥ እንደሚችል የጋራ ግንዛቤ ከያዝን፣ ለለውጡ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ሁሉ ግን ከነበረን አመለካከት ጋር እንድንቆይ የሚያደርጉንም ተጠቃሽ ምክንያቶች አሉ:: Morgan (1961) አመለካከታችንን ከለውጥ እንድናቅብ የሚያደርጉንን ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ያስቀምጣሉ:: እነዚህም:-

1. የአተረጓጎም ምርጫ (Selective interpretation):- ስለ አንድ ነገር አሮጌና አዲስ አስተሳሰብ ይኖርና እነዚህ እራሳቸውን ከለውጥ ያቀቡ ክፍሎች አሮጌውን አስተሳሰብ ወይም እምነት የሚመርጡበት ሁኔታ ነው:: ለምሳሌ መሬት በፀሐይ ዙሪያ ትዞራለች የሚለውን ሳይንሳዊ መንገድ አለመቀበልና ፀሐይ በመሬት ዙሪያ ትዞራለች በሚለው ማመን::
2. አመለካከታችንን ወይም እምነታችንን ሊለውጡ የሚችሉ መረጃዎችን አለማስተናገድ::
3. ማህበራዊ ጫና:- ግለሰቡ ያ ነገር ትክክል አለመሆኑን እያወቀ ወይም እየተገነዘበ ከማህበራዊ ኑሮ ጋር ላለመጋጨት የቀድሞውን እምነት (አመለካከት) የሚያንፀባርቅበት ሁኔታ አለ::

እነዚህ ሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ግለሰብ፣ ቡድን፣ ፓርቲ፣ ጐሣ፣ የሕብረተሰብ ክፍል ወዘተ አመለካከታቸውን ይዘው እንዲቆዩ በምክንያትነት የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው:: እነዚህ ሐሳቦች እንዳሉ ሆነው አንድ ሰው፣ ቡድን፣ ፓርቲ፣ ጐሣ፣ የሕብረተሰብ ክፍል ወዘተ ቀደም ሲል የነበራቸውን አመለካከት (ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ ወይም ከአዎንታዊ ወደ አሉታዊ) ሊያስለውጡ የሚችሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ ጥናቶች ያረጋግጡልናል:: Morgan (1961, 1986), Smith in International Encyclopedia of Social Science (1968), Roger and Houghton (1995) ተጠቃሾች ናቸው::: አመለካከታችንን ሊያስለውጡን ይችላሉ ተብለው በነዚህ የስነአዕምሮ ምሁራን የተጠቀሱ ሁኔታዎች አሉ:: እነርሱም ስነትምህርት (Education)፣ ቅስቀሳ (Propoganda)፣ማስተዋወቂያ (Advertising)፣ አዳዲስ መረጃዎች፣ የርስበርስ ግንኙነት፣ የቡድን አባላት ስብጥር፣ የተለዩ ሁኔታዎች (Particular situations)፣ እና የመልዕክት ምንጭ (the source)፣ መልዕክቱ (the message)፣ የመልዕክቱ ተቀባይ (the receiver) ናቸው:: ከእነዚህ ሌላ አመለካከት ሊለወጥ የሚችልባቸው መንገዶች ብለው Ropger and Houghton (1995) የዘረዘሩአቸው ነገሮች አሉ:: እነዚህም ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ ማየት መቻል፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ ምሁራን፣ የስነልቦና ሰዎች፣ አግባቢ ተግባቦት (Persuasive communication)፣ የመልዕክቱ ባህሪ፣ የተደራሲያን ባህሪ፣ የንግግሩ ባለቤት፣ መልዕክቱ የተላለፈበት አውድ፣ የግል ግንዛቤ ንድፈ-ሐሳብ (Self-perception theory) ፣ የውሳኔ ንድፈ ሐሳብ (Judgment theory) እና አገልግሎታዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional theory) ያካትታል::

ለማጠቃለል ያህል የአመለካከት አንዱ ባህሪው መለወጥ መቻሉ ነው። ነገር ግን ቀደም ሲል ለማየት እንደተሞከረው አመለካከታችን ሊያስለውጡን የሚችሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ ሁሉ፣ የነበረንን አመለካከት ይዘን እንድንቆይ የሚያደርጉን ሁኔታዎችም እንዳሉ መታወቅ ይኖርበታል።

## 2.4.4. አመለካከት እንዴት ይለካል?

በግልፅ የማይታይና በቀጥታ ሊጨን ባለመቻሉ ምክንያት አመለካከትን መለካት አስቸጋሪ እንደሆነ የሚጠቅሱ ጥናቶች አሉ። ከነዚህም መካከል Vargas (1972), Lewy (1977), Malim and Birch (1998) ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ምሁራንና ሌሎችም አመለካከትን መለካት ቀላል አለመሆኑን ይጥቀሱ እንጂ አመለካከትን መለካት ጨርሶ አይቻልም አላሉም። መለካቱ አስቸጋሪ ነው የሚለው ዕንስ ሐሳብ እንዳለ ሆኖ ግን አመለካከት መለካት እንደሚችልና መለካት መቻሉ ደግሞ አንዱ ባህሪው እንደሆነ የሚያረጋግጡልንን ሥራዎች መጥቀስ ይቻላል። Kiesler, et al (1969), Thurnstone (1928) በመጥቀስ ፣ Morgan (1961, 1986) , Kerlinger (1988) አመለካከት ሊለካ እንደሚችልና እንዴት እንደሚለካ በጥናት ከዳሰሷቸው ምሁራን ስር ይመደባሉ።

አመለካከት መለካት መቻሉ ላይ አንድ የጋራ ግንዛቤ ከያዝን ትኩረታችን በሁለት ነጥቦች ዙሪያ ይሆናል።

### 2.4.4.1. በአመለካከት አለካክ ዙሪያ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች

አመለካከት የግንዛቤ (Cognition, percetion) እና የስሜት (Feeling) ጉዳይ በመሆኑ በቀጥታ ሊታይ የሚችል ነገር አይደለም። በዚህም ነጥብ ላይ Anastasi (1976) እና Malim and Birch (1998) አመለካከት በቀጥታ የሚታይ ነገር ባለመሆኑ የሚለየው ወይም የሚለካው ግለሰቡ ከሚያሳየው ባሕሪ በመነሳት ነው ይላሉ። ይህ ደግሞ ከባድና አወዛጋቢ እንደሆነ ከነምክንያቱ ያስቀምጣሉ። በግለሰቡ ላይ የሚንፀባረቀው ባሕሪ እውነተኛውን አመለካከቱን የማይገልጽና የማስመሰል ሊሆን ይችላል። ድርጊቱና (Reaction) ውስጣዊ እምነቱ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚለውና የሚያደርገው፣ በአደባባይ የሚንፀባረቀውና በግል የሚያንፀባርቀው ወይም በተለያዩ ሁኔታዎች (አውዶች) የሚያንፀባርቀው የተለያዩ አመለካከቶች ሁኔታውን አስቸጋሪና አወዛጋቢ ያደርጉታል። ይህንን አወዛጋቢ ሁኔታ አስመልክቶ Thurnstone በFishbein (1967) የሚሉን ነገር አላቸው። የአመለካከት ቃላዊ መግለጫ ሐሳብ (Opinion) ነው። እኛ የምንለካው ይህንን ሐሳብ ነው። ነገር ግን ግለሰቡ ውስጣዊ ስሜቱ የማይገልፀውን ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል። ስለዚህ ከሚሰነዝረው ሐሳብ ይሻላል ተብሎ የሚገመተውን የግለሰቡ ድርጊት (Action) ነው። ይህን ካሉን በኋላ እሱም ቢሆን

የውሸት (የማስመሰል) መሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። ከእርሳቸው አባባል መገንዘብ እንደሚቻለው አወዛጋቢው ነገር የሚሰነዘረው ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በድርጊት የታየውም ነገር ሊያወዛግብ እንደሚችል ነው።

እነዚህ የተዘረዘሩት አስተያየቶች ሁሉ አመለካከት ሊለካ አይችልም ወደሚለው ድምዳሜ ሊወስዱን አይችሉም። እንዲያውም ሊገጥሙን የሚችሉትን እንቅፋቶች ከወዲሁ አውቀን ጥንቃቄ እንድንወስድ ያደርጉናል። በዚህም ወደ ትክክለኛው ልኬት የሚያቀርበውን የአለካክ ዘዴ እንድንመርጥ ያደርገናል። በመረጃዎች አወሳሰድ ላይ ይበልጥ ጥንቃቄ እንድንወስድና የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እንድንተገብር ይገፋፉናል። የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች ከተለያየ አቅጣጫ እንድናመዛዝን ወዘተ ማሳሰቢያ ናቸው። ስለዚህ የሚገጥሙንን ችግሮች ለመቅረፍ አንዱ መፍትሔ የመረጃ ምንጮቻችንን ማስፋት ነው። ይኸውም በጽሑፍ መጠየቅ ብቻ ሳንተማመን በቃለ መጠይቅ ማጠናከር፤ ከዚህም ባሻገር በተለያየ አውድ የሚንፀባረቁትን ባህርያት (ድርጊቶች) በምልከታ ማመዛዘን አስፈላጊ ይሆናል። ከዚህም ሌላ የተሻለ የመለኪያ ዘዴ ከተገኘ መጠቀም ሌላኛው መፍትሔ መንገድ ነው። እስከዛሬ ድረስ ሥራ ላይ የዋሉት የአመለካከት መለኪያ ዘዴዎች ብዙ ቢሆኑም አንዱ ከሌላኛው የተሻለ ወደትክክለኛው (እውነተኛ) ነገር የሚያቀርብ እንደሆነ በምሁራን ይጠቀሳሉ።

## 2.4.4.2. የአመለካከት መለኪያ ዘዴዎች

በ"2.4.4.1" ስር የተነሱት ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው የተለያዩ የማህበራዊ ስነልቦና ተመራማሪዎች አመለካከትን ለመለካት ያመቻል፤ የበለጠ ትክክለኛ መረጃ ያስጨብጣል ብለው የሚከተሉአቸው ዘዴዎች ብዙ ናቸው። Thurnstone scale, Likert Scale, Semantic difference (Bogardus Scale) ተጠቃሾች ናቸው። ሁሉም ዘዴዎች ደግሞ መሠረት የሚያደርጉት የተጠኚውን ሐሳብ (Opinion) እና የሚያንፀባርቃቸውን ባህርያት ነው።

Kiesler, et al (1969) Cook and Selltiz (1964) ጠቅሰው እንዳስፈሩት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ነጥቦች በመነሳት የአንድን ግለሰብ (ቡድን) አመለካከት መለካት እንደሚቻል ይጠቁሙናል።

1. የግለሰቡን (የቡድን) ዘገባ ወይም ሐሳብ
2. የእውናዊው አውድ በመመልከት
3. ከተጠኚው አባባል ወይም አተረጓጎም
4. ከተጠኚው ብቃት
5. ተጠኚው ለጉዳዩ ከሚሰጠው አካላዊ ምላሽ

Morgan (1961) Kiesler, et al (1969), Anastasi (1976), Kerlinger (1988), Roger and Houghton (1995), Best and Kahun (1998), Malim and Birch (1998) እና ሌሎች የአመለካከት

መለኪያ ዘዴዎችን በጥናታቸው ውስጥ ካካተቱት ተመራማሪዎች መካከል ናቸው:: በሁሉም ምሁራን ሥራዎች ውስጥ የጋራ የሆኑት ግን ሁለት ዘዴዎች ብቻ ናቸው:: እነሱም Thurnstone Scale እና Likert Scale ናቸው:: እነዚህ ሁለት ዘዴዎች በብዙዎች ሥራ በመዳሰሳቸውና ከሌሎች ይበልጥ እየተተገበሩ ያሉ በመሆናቸው ስለባህርያቸውና አተገባበራቸው በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን::

Thurnstone scale, equal - appearing interval, Psychphyoical Model በመባል የሚታወቅ ነው:: እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ምንጮች እንደሚጠቁሙት Thurnstone and Chave በ1929 ያስተዋወቁት ዘዴ ሆኖ አተገባበሩ እንደሚከተለው ነው::

- ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርከት ያሉ አረፍተ ነገሮች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ይዘረዘራሉ::እነዚህን የተዘረዘሩትን አረፍተ ነገሮች ዳኞች እንዲደለድሉ ይደረጋል:: ከደለደሉት በኋላ ሁሉም በሚስማሙበት ሣጥን ውስጥ የመስማማት ምልክት ያደርጋሉ፤ ካልተስማሙበት ግን አረፍተ ነገሩ ይወጣል::
- በየእስኬሎቹ መካከል ያለው ዋጋ እኩል ነው::
- እያንዳንዱ እስኬል የራሱ ዋጋ አለው::
- ዝቅተኛ የእስኬል ዋጋ ካለው የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት አለው::
- አተገባበሩ በጣም አድካሚ ነው::

Likert scale, summated rating scales ከሚባሉት የሚመደብ ሆኖ Likert በሚባለው ተመራማሪ በ1932 ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን አብይ መለያው:-

- ለመላሾች በሚስማማ መልኩ አማራጮቹን ሰፋ አድርጎ (ብዙውን ጊዜ አምስት ናቸው) በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ ለመወሰን አልችልም፣ አልስማማም፣ ፍፁም አልስማማም የሚሉትን አማራጮች ከሐሳቡ ጋር ያቀርባል::
- የአንድ ሰው አመለካከት ደረጃ (መጠን) ለመወሰን ተደምሮ አማካይ ይወጣለታል:: አማራጮቹ የሚከተሉት ዋጋ አላቸው::

| ሀ/ <u>በአዎንታዊ ምላሽ</u> | | ለ/ <u>በአሉታዊ ምላሽ</u> | |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ = | 5 | በጣም እስማማለሁ = | 1 |
| እስማማለሁ = | 4 | እስማማለሁ = | 2 |
| መወሰን አልችልም = | 3 | መወሰን አልችልም = | 3 |
| አልስማማም = | 2 | አልስማማም = | 4 |
| ፍፁም አልስማማም = | 1 | ፍፁም አልስማማም = | 5 |

- ለማዘጋጀት ቀላል ነው::
- እንደ Kerlinger (1988) አባባል ለባህሪ ምርምር (Behavior research) ይህ ዘዴ በጣም ጠቃሚ የሆነ ዘዴ ነው፡ ለማዘጋጀት ጊዜ የማይወስድ፣ ቀላል አቀራረብ ያለው፣ ውጤቱ ግን ከ Thurnstone ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዘዴ ነው::

## 2.4.5. አመለካከት 2ኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ሚና

እንደሌሎች የስነአዕምሮ ዘርፎች አመለካከትም ለየትኛውም የትምህርት አይነት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው (Cronbach, 1963):: ቋንቋውን ለመማር ጥሩ ግንዛቤና ስሜት ከሌለን በአጠቃላይ ለትምህርታዊ ሂደቱ መልካም ፍላጎት አናሳይም:: ፍላጎቱ ከሌለ ደግሞ ንቪ አይኖርም:: ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ ከሌለ በጥሞና (Attention) ትምህርቱን ስለማንከታተል ውጤታማነታችን ጥያቄ ሥር ይወድቃል:: Celce-Murcia (1991) እና Stewart (1968) በበኩላቸው ተማሪው ለታላሚው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች (Activities) ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ይገልጻሉ:: ይህ ማለት ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ካለው እንደቋንቋው ባለቤቶች ለመናገር ይጣጣራል፤ በድፍረት ይናገራል (አያፍርበትም)፤ ለመቃረም ዝግጁ ነው፣ ከተናጋሪዎቹ ጋር ለመገናኘት ፍላጎት ያሳያል ወዘተ:: በተቃራኒው በቋንቋውና በቋንቋው ተናጋሪዎች ላይ አሉታዊ አመለካከትን አዳብሮ ከሆነ ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት አያሳይም ወይም ደስተኛ አይደለም:: ቋንቋውን ለመለማመድ ሙከራ አለማድረግ፤ ከቋንቋው ተናጋሪዎች እራሱን የማግለልና የመሳሰሉት ባህርያት ይታዩበታል:: Day and Bamford (1998) በበኩላቸው 2ኛ ቋንቋን (የውጭ ቋንቋን) መማር ሌሎች ትምህርቶችን ከመማር በጣም የተለየ ነው:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት ቋንቋን መማር ካለው የተለየ ባህሪ የተነሳ ነው:: የምንማረው የቋንቋውን ክሂሎችና ዕውቀቶች ብቻ ሳይሆን የሌላውን ሕዝብ ባህል ጭምር ነው:: የራሳችን መለያ ከሆነ ከቋንቋችንና ከባህላችን ጎን ለጎን የሌላውን ቋንቋ፣ባህል መማሩ ምን ያህል አመለካከታችንን እንደሚፈታተን መገንዘብ አያዳግተንም::

በአፍ መፍቻ ቋንቋና በ2ኛ ቋንቋ ተስተምህሮ መካከል የብቃት ልዩነትን የሚያስከትሉ አራት ነገሮችን Spolsky (1969) ይጠቀሳሉ:: እነዚህም የማስተማር ስነዘዴ፣ ዕድሜ፣ ቅድመ ችሎታ (Aptitude) እና አመለካከት ናቸው:: Spolsky ይህን ከጠቀሱ በኋላ በአንድ የቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የበርካታ ሰዎች አመለካከት የየራሱ አስተዋጽኦ አለው በማለት ይጠቅሳሉ:: እነዚህም የተማሪው፣ የመምህሩ፣ የተማሪው ወላጆች፣ የተማሪው ጓደኞችና የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች የመሳሰሉት ናቸው:: ከነዚህ ሁሉ ግን ትልቁን ሚና የሚጫወተው ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት ነው:: ይህ አባባል ከCelce-Murcia (1991)፣ከGardner in Oller and Richards(1975) ሃሳብ ጋር አብሮ

የሚሄድ ነው። ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ከሌለው ለትምህርቱ ጉጉት ስለማይኖረው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። Spolsky(1969) ቀደም ሲል ካነሱአቸው ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ካለው አመለካከት በተጨማሪ Spolsky (1990) ቋንቋውን የሚማርበትም አውድ በአመለካከቱ ላይ የበኩሉን ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያስገነዝቡናል። ቋንቋውን የሚማርበት አውድ ሲል ለምን እንደሚማረው፣ ክፍለ ጊዜው፣ ትምህርቱ በመርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ መቅረቡ፣ ሙያውን ባልተካኑ መምህራን ትምህርት መስጠቱ፣ በፈቃደኝነት ወይም በግዳጅ የትምህርቱ የመስጠቱ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። በተጨማሪም ቋንቋው በሕብረተሰቡ ማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚነገር፣ የሚያገለግል ከሆነ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ተቋዳሽ ለመሆን በቋንቋው ላይ በጎ አመለካከትን በመያዝ በጥሩ መንፈስ ትምህርቱን ተማሪው የሚከታተልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

ሐሳቦቹን ስናጠቃልል አመለካከት የትኛውንም የትምህርት አይነት ለመማር አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ቋንቋን ስንማር ከሌሎች የትምህርት አይነቶች የተለየ የሚያደርጉት ባህርያት አሉት። ይህ የቋንቋ የተለየ ባህሪ ደግሞ አመለካከት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና ከሌሎች የትምህርት አይነቶች የበለጠ አስፈላጊና ወሳኝ ያደርገዋል። ስለዚህ አመለካከት በቋንቋው ትምህርት ውስጥ በተለይ በ2ኛ ቋንቋ ተስተምህሮ ወቅት በጣም ትኩረት የሚሰጥበት ስነ-አዕምሮ ጉዳይ መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።

## 2.5. ተማሪዎች በሚማሩት የቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ የሚገፉፉ ሁኔታዎች

ለአመለካከት መፈጠር መነሻ የሚሆኑ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ አመለካከታችን ሊያስለውጡን የሚችሉ በርካት ያሉ ሁኔታዎች ወይም ክስተቶች እንዳሉ ቀደም ሲል ተመልክተናል። እነዚህ የሚፈጠሩ ወይም የሚለወጡ ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ እንደዚሁም ከአሉታዊነት ወደ አዎንታዊነት ወይም ወደ ተቃራኒው መሆን እንደሚችልም ዳስሰናል። በጎ አመለካከትን ማዳበርና እንዲጎለብትም ጥረት ማድረግ የመማር ማስተማሩ ትልቁ ግብ እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም። ነገር ግን የተተለመው ዕቅዳችን ከዳር እንዳይደርስ ለአሉታዊ አመለካከት መፈጠር መንስኤ የሚሆኑ ሁኔታዎች በተስተምህሮ ሂደት ውስጥ ይገጥሙናል። ለነዚህ አሉታዊ አመለካከቶች መዳበር መንስኤ የሆኑ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ ደግሞ ለችግሩ መፍትሔ ለመሻትም ስለሚረዳ ተማሪው በአንድ የትምህርት አይነት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብር የሚያደርጉትን ዋና ዋና ነጥቦች ለይቶ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለ።

ተማሪዎች በሚማሩአቸው የትምህርት አይነቶች ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉአቸው ብዙ ሁኔታዎች እንዳሉ የስነልቡና ምሁራን ያስረዳሉ። ከነዚህ ምሁራን መካከል Hurlock (1996), Harmer (1983), Spolsky (1969) እና

Morgan (1961) ተጠቃሾ ናቸው። Hurolck (1996) በተለይ በተማሪዎች አመለካከት ላይ አሉታዊ ድባብ የሚፈጥሩ ሰባት ነገሮችን በዝርዝር አስፍረው እናገኛለን። እኛም በቀዳሚነት የዘረዘሩአቸውን ነጥቦች የምንመለከት ይሆናል።

1) የእኩዮች አመለካከት (Peer attitude):- በወጣትነት ዕድሜ ተማሪዎች ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የበለጠ በብጤዎቻቸው ፍላጎት እንደሚመሩ ከHurlock በተጨማሪ Harmer (1983) ያስገነዝቡናል። ከወላጆችም የበለጠ በእኩዮች ሐሳብና ምርጫ የመመራት ሁኔታ ስላለ ጓደኞቻቸው በክፍለ ጊዜው የሚረብሹ፣ የቤት ሥራ የማይሰሩ፣ የማያጠኑ ወዘተ ከሆነ የእኩዮቻቸውን ዝንባሌ፣ ስሜትና አድራጎት ሊጋሩ ይችላሉ።

2) የወላጆች አመለካከት (Parental attitude):- ይህን ነጥብ በሁለት መንገድ ነው ለማየት የሞከሩት። ወላጅ ስለትምህርት ያለው ግንዛቤ:-

ሀ/ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ትምህርት የሕልውና መሠረተ ድንጋይ ነው።

ለ/ የአገሪቱ ሕግ ስለሚያስገድዳቸው ብቻ ልጆችን ለይስሙላ ወደ ት/ቤት መላክ።

የመጀመሪያው ነጥብ አዎንታዊ አመለካከትን የሚያጎለብት ሲሆን፣ ሁለተኛው ነጥብ ግን የወላጅ ለትምህርት ያን ያህል ቦታ አለመስጠት ወደ ልጆቻቸው ይጋባል። የወላጆችን ተፅዕኖ አስመልክቶ ብዙ የተሰሩ ሥራዎችን እናገኛለን። Gardner በOller and Richard (1975) እና Lamber and Klineberg (1967) ጠቅሰው ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ እንደሚከተለው ያብራራሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ላይ የነቃ ተሳትፎ (Active role) ወይም የደከመ ተሳትፎ (Passive role) ሊጫወቱ ይችላሉ። የነቃ ተሳትፎ ስንል ልጆቻቸው ቋንቋውን እንዲማሩ ያበረታታሉ፣ ብቃታቸውን በቅርበት ይከታተላሉ (ይቆጣጠራሉ)፣ የቤት ሥራ መስራታቸውን፣ ማጥናታቸውን ወዘተ ያያሉ። የደከመ ተሳትፎ ስንል ግን ስለቋንቋውና ስለቋንቋው ተናጋሪዎች መጥፎ መጥፎ ነገር፣ መጥፎ ታሪክ ለልጆቻቸው ማጫወት ያዘወትራሉ፤ጥላቻቸውን ወደልጆቻቸው ያሰርፃሉ። ስለሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ጎሣዎች ሁኔታ በልጆች ውስጥ በማስረጹ በኩል የወላጅ ሚና በጣም ከፍተኛ ነው፤ ለዚህም ነው "የልጅ አመለካከታዊ አውድ የቤቱን ይመስላል" የሚባለው በማለት የወላጅን ተፅዕኖ በሚገባ ያስጨብጡናል።

Spolsky (1969) በበኩላቸው ወላጆች የውጭውን (2ኛውን ቋንቋ) ብዙውን ጊዜ ቤት አካባቢ የሚገለገሉ ከሆነ ልጆቻቸውም በዚያ ቋንቋ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ ይሉናል። ይህን ሐሳብ በተቃራኒው ስንወስደው ደግሞ ወላጆች በጥላቻም ይሁን በሌላ ቋንቋውን ቤት አካባቢ የማይገለገሉ ከሆነ ልጆቻቸውም ለቋንቋው ዝቅተኛ ግምት በመስጠት ትምህርቱን በአግባቡ ላይከታተሉ ይችላሉ። ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በወላጆችና በልጆቻቸው መካከል ከፍተኛ የአመለካከት ግንኙነት አለ (Morgan, 1961)።

በምሁራኑ ገለፃና በገጠመኝም እንደሚታወቀው የወላጆች አሉታዊ አባባሎች፣ ወጉች፣ ጥቆማዎች ወዘተ በልጆቻቸው አመለካከት ላይ አሉታዊ ጫናን መፍጠሩ የማይቀር ነው።

3) ውጤት (Grades):- ተማሪው ለምሳሌ በዚያ በቋንቋ ትምህርቱ ጥሩ ውጤት ካስመዘገበ የሚበረታታ ሲሆን፣ በየጊዜው ዝቅተኛ ውጤት የሚያገኝ ከሆነ ግን ጥላቻን እያዳበረ ይመጣል።

4) የትምህርቱ (የኮርሱ) ጠቀሜታ ወይም ተጨባጭ ፋይዳ (The relevance or practical value of various courses):- እንግሊዝኛንና አማርኛን ጎን ለጎን አስቀምጠን ከጠቀሜታቸው አንፃር ብንመለከት እንግሊዝኛ፣ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ተቋማት የማስተማሪያ ቋንቋ፣ ለለምአቀፋዊ ቋንቋ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ ወዘተ በሚሉት ሰበቦች የእንግሊዝኛን ሚዛን ከፍ፣ የአማርኛን ዝቅ እንደሚያደርጉት የተደረጉት ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

5) ለመምህራን፣ ለት/ቤቱ አስተዳደር፣ ለትምህርት ፖሊሲው ካላቸው አመለካከት (Attitudes toward teachers, administrators, and academic and disciplinary policies) በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪው ለመምህሩ በጎ አመለካከት ከሌለው ለትምህርቱም ያለው አመለካከት እንደሚቀንስ Harmer (1983) ያረጋግጡልናል። የት/ቤቱ ደንቦች ለምሳሌ ስለአለባበስ፣ የዲሲኘሊን ሁኔታ፣ የዝውውር ፖሊሲ (Promotion policy) ወዘተ ከተማሪው ፍላጎት አቅም ወይም ችሎታ ጋር የማይሄድ ከሆነ ከመምህሩ ጀምሮ አስተዳደሩን፣ ደንቦቹን በአጠቃላይ ስለሚጠላቸው ትምህርቱንም እየጠላው ይሄዳል።

6) በተጓዳኝ ትምህርቶች ውጤታማ መሆን/አለመሆን (Success in extracurricular activities) አንድ የቋንቋ ተማሪ ለምሳሌ በስነጽሑፍ ክበብ፣ በድራማ ክበብ፣ በጋዜጠኝነት ወዘተ ውጤታማ ወይም ታዋቂ እየሆነ ሲሄድ የቋንቋውንም ትምህርት እየወደደ ሊመጣ ይችላል። ነገር ግን በነዚህ ክበባት አካባቢ ምንም ፍላጎቱንም ሆነ ቦታ ከሌለው ትምህርቱንም ችላ ችላ እያለው ከዚያም አልፎ ተርፎ አሉታዊ አመለካከት እያሳደረ ሊሄድ ይችላል።

7) በክፍል ተማሪዎች መካከል ያለው ማህበራዊ ተቀባይነት (Degree of social acceptance among class-mates) በክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎች ከፊሎቹ የቋንቋው አፈፊት ወይም አፈፊትም ባይሆኑ በሁኔታዎች መመቻቸት የተነሳ የቋንቋው ጥሩ ተናጋሪ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ለቋንቋው ኢአፈፊት ወይም የቋንቋው ባለቤትም ሆነው ቀበልኛ ተናጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህን ወቅት በተማሪዎች መካከል ብሽሽቅ ወይም ሌላም ፀያፍ ንግግር ካለ እነዚያ ተማሪዎች ከደረሰባቸው የማህበራዊ ቀውስ የተነሳ በቋንቋው ትምህርት ላይ በጎ ያልሆነ አመለካከት እያዳበሩ ይመጣሉ።

እነዚህ በHurlock (1996) አሉታዊ አመለካከትን ለማስረጽ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ተብለው የተዘረዘሩት ሲሆኑ ብዙዎች ምሁራን የሚጋሩአቸው ነጥቦች ናቸው። Spolsky (1969) ከማንኛውም ነጥብ በላይ በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያድል የሚያደርገት ተማሪው ለቋንቋውና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት ነው ይላሉ። የቋንቋውን ባለቤቶች የሚጠላቸው፣ የማይፈልጋቸው ከሆነ ቋንቋቸውንም ይጠላዋል፤ ቋንቋውን ከጠላው ደግሞ ትምህርቱንም ይጠላዋል። Morgan(1961) አሉታዊ አመለካከትን በተማሪው ጭንቅላት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ከሚቀርጹት ነገሮች ዋንኞቹ ቋንቋውንና የቋንቋውን ታሪክ አስመልክተው በድራማ ወይም በጭውውት መልክ የሚቀርቡት ነገሮች ናቸው በማለት ይገልፃሉ።

እስካሁን የተጠቋቆሙትን ነጥቦች እንኳን ብንመለከት የተፅዕኖው ደረጃ ይለያይ እንጂ ብዙ ሁኔታዎች በተማሪው የቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከትን የሚያሳድሩ መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

## 2.6. በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን አመለካከት አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች

ብርሃኑ ገብረማርያም በ1976 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ "ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት (Attitude) በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች" ላይ የቀረበ ቴሲስ እናገኛለን።

ጥናቱ በመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ ሆኖ ተማሪዎች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ላይ ያላቸውን አመለካከት በንጽጽር መልክ ቢመለከትም ዋና ትኩረቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ነው። የጥናቱ ውጤትም ሲታይ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ እንግሊዝኛን እንደሚመርጡ፣ ከሴቶች ይልቅ ወንዶች አማርኛን እንደሚመርጡና የአማርኛ ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን እንደማይፈልጉ የሚሉት ዋና ዋና ግኝቶቹ ናቸው።

ታሪኩ ፋንታዬ በ1988 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ተቋም አማርኛን በማስተማር ትምህርት (TeAm) ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ "የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከትን (Attitude)" ለማወቅ የተካሄደ ጥናት ነው። የታሪኩ ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ዘንድ አማርኛ ቋንቋና የቋንቋው ትምህርት ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው? ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተላውጦዎችን መፈተሽ ነው።

የጥናቱም ግኝት የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ወላጆችና የተማሪ እኩዮች ለአማርኛ ቋንቋና ለቋንቋው ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ነው፡፡

አበበ ሺፈራው በኮተቤ የመምህራን ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኢዱኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ "አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት (Attitude) በሰበታ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" ላይ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ አንዱ ነው፡፡ የአበበ ዋና አላማ "አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የሰበታ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት የላቸውም" የሚለውን መፈተሽ ነበር፡፡ ግኝቱ እንደሚያስረዳው ተተኳሪ ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ለቋንቋው ትምህርት፣ ለቋንቋው ተናጋሪ ወዘተ ጥሩ አመለካከት የላቸውም፡፡

ዳንኤል መኮንን በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኢዱኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ "በሀዲይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በሆሣዕና ከተማ የሚገኙ የሁለት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት" የቀረበ ጽሑፍ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ አፋቸውን በሀዲይኛ ቋንቋ የፈቱ የሆሣዕና ከተማ ውስጥ የሚገኙ የዋቸሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የየካቲት 25/67 አንደኛና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ነው፡፡ የጥናቱ ግኝት እንደሚያስረዳው በታላሚ ት/ቤቶቹ ውስጥ ያሉትና አፋቸውን በሀዲይኛ የፈቱ ተማሪዎች ለቋንቋው፣ ለቋንቋው ትምህርት፣ ለቋንቋው ተናጋሪ ወዘተ አዎንታዊ አመለካከት እንዳለቸው ነው፡፡

የእኔ ሥራ ከእነዚህ ተዛማጅ ሥራዎች ጋር የሚጋራቸው ነጥቦች ያሉ ቢሆንም፣ የሚለይባቸው ነጥቦች ግን ይበረክታሉ፡፡ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት መፈተሹ ላይ የጋራ ስንሆን፣ ታላሚ በሆኑት ተማሪዎችና በዋናነት ይዘን በተነሳንባቸው ጥያቄዎች እንለያያለን፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሆኑት ለአማርኛ ቋንቋ አፈፈት ኢአፈፈት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ሲሆኑ፣ ጥናቱ በዋናነት ሊመልስ የተነሳው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደ ከፍተኛ ትምህርት በሚያስገባው የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ያስከተለ ለውጥ ካለ መፈተሽ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ

### 3.1. ናሙና

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ አፈፊት እና በምስራቅ ሸዋ ዞን ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት የሚያነፃፅር ነው፡፡ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ጥናቱ የሚመለከተውን ማንኛውንም ሰው ወይም ነገር ሁሉ በመረጃ ሰጪነት መጠቀም ብዙውን ጊዜ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ አማራጩ ከጠቅላላው ጥናቱ ከሚመለከታቸው ሰዎች መካከል ጥቂቶቹን መርጦ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አሠራር ደግሞ ናሙና በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት ይህን ጥናት ለማካሄድ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ ናሙናዎች ተወስደዋል፡፡

### 3.1.1. ትምህርት ቤቶች

በአዲስ አበባ መስተዳድር ሥር 10፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን 10 በድምሩ 20 የመንግስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው በዚህ በሃያዎቹ ትምህርት ቤቶች ላይ ለመሥራት ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከሰው ሃይል አንፃር ከአጥኚው አቅም በላይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ከሁለቱም መስተዳድሮች ናሙናዎች ተወስደዋል፡፡ ይኸውም ከአዲስ አበባ መስተዳድር ሁለት፣ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ሶስት በድምሩ አምስት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ለናሙናነት ተመርጠዋል፡፡ የአዲስ አበባዎቹ ትምህርት ቤቶች ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ሁሉም ወካይ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመረጋገጡ ዳግማዊ ምኒልክ እና መድሐኒዓለም በዕጣ ተመርጠዋል፡፡ በምሥራቅ ሸዋ ዞን ስር የሚገኙት ትምህርት ቤቶች ግን ከጥናቱ ዓላማ አንፃር እንደ አዲስ አበባዎቹ ሁሉም እኩል የወካይነት ሚና መጫወት እንደማይችሉ አጥኚው ስላረጋገጠ በዒላማ የናሙና ዘዴ (Purposive sampling) ሶስቱን መርጧል፡፡

እንደሚታወቀው ምሥራቅ ሸዋ ዞን በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ሥር ከሚገኙት ዞኖች አንዱ ነው፡፡ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያሉት የመሰናዶ ተማሪዎች ደግሞ ከኦሮምኛና ከአማርኛ አንዱን መርጠው ይማራሉ፡፡ አጥኚው በሥራ ሂደቱ የተገነዘበው አንድ መሠረታዊ ነገር አለ፡፡ የኦሮምኛ ቋንቋ ለብዙዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በመሆኑና ለሥራ ዕድልም ትምህርቱን ስለሚፈልጉት በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች አማርኛ የሚመርጡ ተማሪዎች ቁጥር አንሶ አግኝቷል፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሳት የጥናቱ ባለቤት ብዙ የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚገኙባቸውን ትምህርት ቤቶች ለመምረጥ ተገድዷል፡፡ በዚህ መሰረት ሐዋስ

ናዝሬት የሚገኘው የቀድሞው አጼ ገላዴዎስ ትምህርት ቤት፣ ከደብረ ዘይት ቢሾፍቱ የመሰናዶ ትምህርት ቤትና ዝዋይ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ ሠንጠረዥ አንድም እነዚህን በጥናቱ ውስጥ የታቀፉትን ትምህርት ቤቶች ስምና የሚገኙበትን መስተዳድር ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ አንድ:- በናሙናነት የተወሰዱ ትምህርት ቤቶች ስምና የሚገኙበት መሥተዳድር

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የሚገኙበት መሥተዳድር |
|---|---|---|
| 1 | ዳግማዊ ምኒልክ | አዲስ አበባ |
| 2 | መድሀኒዓለም | አዲስ አበባ |
| 3 | ሐዋስ | ምስራቅ ሸዋ |
| 4 | ቡሾፍቱ | ምስራቅ ሸዋ |
| 5 | ዝዋይ | ምስራቅ ሸዋ |

## 3.1.2. ተማሪዎች

### 3.1.2.1. የአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎች

በ1996 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በዳግማዊ ምኒልክ እና በመድሀኒአለም ትምህርት ቤቶች ከ 11 እና 12 ( $PP_1$ እና $PP_2$) ከሚማሩት3042 የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ወንድና ሴትን ያካተተ ሆኖ ከሳይንስና ከአርት በጠቅላላ 200 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል፡፡ ስክሽኖቹም ሆኑ ተማሪዎቹ (የአፍ መፍቻቸውን አማርኛ የሆኑት) የተመረጡት በነሲብ የናሙና ዘዴ ነው፡፡

### 3.1.2.2. የምሥራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች

ዞኑ በመሰናዶ ደረጃ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በብዛት መርጠው የሚማሩበት ዞን ነው ተብሎ ስለሚገመት ሊመረጥ ችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት በትምህርት ዘመኑ በሶስቱ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መርጠው በመማር ላይ የሚገኙት 2476 የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ከሁለቱም ፆታ፣ ከ11 እና ከ12፣ ከሳይንስና አርት በአጠቃላይ 200 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት 200 ተማሪዎች እንደ አዲስ አበባዎቹ በነሲብ የናሙና ዘዴ ተመርጠው አይደለም፡፡ በነዚህ በሐዋስ፣ ቡሾፍቱና ዝዋይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በብዛት የሚከታተሉት የአማርኛ ቋንቋ አፊፊት የሆኑ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም ከየክፍሎቹ ወይም ከሴክሽኖቹ ለቋንቋው ኢአፊፊት የሆኑትን ተማሪዎች በመጠየቅና ፈቃደኛ ሆነው ሲገኙ ብቻ በማስሞላት የተሰበሰበ መረጃ ነው፡፡

በአጠቃላይ በተማሪዎች እንዲሞሉ የተበተኑ 400 የጽሑፍ መጠይቆች ሙሉ በሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡ ነገር ግን የአንዲት ተማሪ ወረቀት ገጽ 4 ስለሚጎለው በአንዳንዱ

እስታትስቲካዊ መረጃዎች ላይ በ399 ተሰርቶ እናገኛለን:: ሠንጠረዥ ሁለት መጠይቁን በመሙላት የተሳተፉትን ተማሪዎች ሁኔታ ይገልጽልናል::

ሠንጠረዥ ሁለት:- በናሙናነት የተወሰዱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤትና ከክፍል ደረጃ አንፃር የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የት/ቤቱ ስም | 11ኛ ክፍል | | 12ኛ ክፍል | | ጠቅላላ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | ዳግማዊ ምኒልክ | 30 | 20 | 25 | 25 | 55 | 45 | 100 |
| 2 | መድህኒዓለም | 24 | 21 | 42 | 13 | 66 | 34 | 100 |
| 3 | ሐዋስ | 29 | 8 | 32 | 21 | 61 | 29 | 90 |
| 4 | ቡሾፍቱ | 22 | 12 | 18 | 13 | 40 | 25 | 65 |
| 5 | ዝዋይ | 25 | 12 | 7 | 1 | 32 | 13 | 45 |
| | የአምስቱ ት/ቤት | | | | | 254 | 146 | 400 |

## 3.1.3. መምህራን

በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ናቸው:: ምክንያቱም ከጥናቱ ርዕስ መገንዘብ እንደሚቻለው "የመሰናዶ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው አመለካከት" ስለሚል ጠቃሚ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉት ለክፍሎቹ የተዘጋጁትን የትምህርት መሳሪያዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ይሆናሉ የሚል እምነት ስላለ ነው::

በእነዚህ በናሙናነት የተወሰዱ አምስት ትምህርት ቤቶች የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር 11 ነው:: አሥሩቹ የጽሑፍ መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል:: የዝዋይ የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር የነበሩት በወቅቱ ለሥርክሾፕ ወደሌላ አካባቢ ሄደው ስለነበሩ ለማግኘት አልተቻለም::

ሠንጠረዥ ሶስት የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት የተሳተፉት መምህራን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ ይሰጠናል::

ሠንጠረዥ ሶስት:- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉትን መምህራን ዝርዝር ግላዊ መረጃ የሚያመለክት

| ፆታ | | | የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ | | | በኢት/ቋ/ስነጽሁፍ የመጀመሪያ ድግሪ | | | በአማርኛ ቋንቋ | | | አሁን አማርኛን እየተማሩ ያሉት | | | | የአገልግሎት ዘመን | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ሴ | ድ | የሆነ | ያልሆነ | ድምር | ያላቸው | የሌላቸው | ድምር | በፍላጎት የሰለጠኑ | ያለፍላጎት የሰለጠኑ | ድምር | በፍላጎት | ያለፍላጎት | ያልገለፁ | ድምር | 22 - 25 | 26-29 | ከ30 በላይ | ድምር |
| 7 | 3 | 10 | 7 | 3 | 10 | 10 | - | 10 | 4 | 6 | 10 | 3 | 5 | 2 | 10 | 5 | 3 | 2 | 10 |

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናት ለማካሄድ አስተማማኝ መረጃዎችን መሰብሰብ አስፈላጊ ነው። እንደ አለም (1992፣ 43) አገላለጽ "አንድ ጥናታዊ ዘገባ ተወጥኖ፣ አስተማማኝ ወደ ሆነ ድምዳሜ መድረስ እንዲችል ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ መረጃዎችን ማሰባሰብ ያሻል።" ከመረጃዎቹ ወቅታዊነትና አስተማማኝነት ባሻገር ለጥናቱ ተስማሚ የሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መምረጡን አጥኝው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ የሚጠቀሱ የምሁራን ሥራዎች አሉ። Kiesler, et al (1969), Dubin and Olshtain (1986), Spolsky (1990) እና አለም (1992) የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች በርካታ ቢሆኑም የጽሑፍ መጠይቅ፤ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ የሚዘወተሩና አስተማማኝ ስልቶች እንደሆኑም ተጠቅሰው እናገኛለን። አጥኚውም በእነዚህ እውነታዎች ላይ በመንተራስ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶቹን፣ የመረጃ ምንጮቹንና ቦታዎችን ወስኗል። በዚሁ መሠረት ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን፣ አጋዥ የመረጃ መጋቢዎቹ ቃለመጠይቅ እና ምልከታ ናቸው። መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት በናሙናነት ከተያዙት አምስት የመሰናዶ ት/ቤቶች ነው። የጥናቱ ዒላማና (target) የመረጃዎቹም ዋና ምንጮች እነዚህ የመሰናዶ ተማሪዎች ናቸው። የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ወላጆች አጋዥ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

### 3.2.1. የጽሑፍ መጠይቆች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ የተዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቆች ሁለት ናቸው። አንደኛው በናሙናነት በተወሰዱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ባሉት የመሰናዶ ተማሪዎች የሚሞላ ነው። ሌላኛው በእነዚሁ በናሙናነት በተወሰዱ ት/ቤቶች የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን የሚሞላ ነው።

### 3.2.1.1. ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ

መጠይቁ ሁለት ክፍሎች አሉት:: የመጀመሪያው ክፍል ተማሪዎች ስለራሳቸውና ቤተሰባቸው የሚፈለግ መረጃ የሚሞሉበት ነው:: ሁለተኛው ክፍል ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥያቄዎች የሚቀርቡበት ነው:: ጥያቄዎቹ ውስን አጠያየቅ (Closed form) እና ልቅ አጠያየቅ (Open form) ያካተቱ ናቸው:: ውስን ጥያቄዎቹ በሶስት መልክ የቀረቡ ናቸው:: የመጀመሪያው በሊከርት እስኬል የመለኪያ ዘዴ፡- በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ አልስማማምና ፍጹም አልስማማም በማለት የሚመለሱ 30 ጥያቄዎችን ያካተተ ነው:: እነዚህ 30 ጥያቄዎች በውስጣቸው ሰባት የተለያዩ ጉዳዮችን (ጭብጦችን) የያዙ ናቸው::

1. ወደ ከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ አለመካተቱ የሚያሳድረው ተጽዕኖ
2. የተማሪው ግላዊ አመለካከት
3. የአማርኛ ቋንቋን መማር ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንፃር
4. የወላጅ፣ የእኩዮች፣ የህብረተሰብና የመገናኛ ብዙሃን አመለካከት
5. የቋንቋው አፈፊትና ኢአፈፊት መሆን የሚያሳድረው ተጽዕኖ
6. የመማሪያ መጽሐፍቱ ይዘትና አቀራረብ
7. ለአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከተሰጠው ዝቅተኛ ደረጃ አንጻር

ሌላው የውስን ጥያቄ አቀራረብ አሁን እየተተገበረ ካለው የቋንቋ የትምህርት ፖሊሲ፣ ቀድም ባሉት በእነታሪኩ (1988) ግኝቶችና በአገሪቷ ውስጥ በተጨባጭ እየተንጸባረቁ ያሉትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል ተብለው የተዘረዘሩትን ስምንት ተላውጦች (Variables) እንደ ችግሩ ክብደት በደረጃ ማስቀመጥ ነው:: ሦስተኛው አቀራረብ ከፊል ውስን (Semi closed ) ሲሆን ተማሪዎች በመሰናዶ ደረጃ የሚማሩአቸው የትምህርት ዓይነቶች በጣም ከሚወዱት በመጀመር በደረጃ የሚያስቀምጡበት አጠያየቅ ነው:: በመጨረሻም ሁለት ልቅ (open) የሆኑ ጥያቄዎች የቀረቡላቸው ሲሆን ነፃ ሆነው የየራሳቸውን አስተያየት በዚህ ሥር እንዲያሰፍሩ ተደርጓል::

አጥኚው ለናሙናነት በተመረጡ ት/ቤቶች በአካል በመገኘት ለተማሪዎቹ የጥናቱን ዓላማና አሠራር ካስረዳ በኋላ መጠይቁን የበተነላቸው ሲሆን፣ ከአምስቱም ትምህርት ቤት ለናሙናነት የተመረጡት 400 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቅጽ ሞልተው መልሰዋል::

### 3.2.1.2. ለመምህራን የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ

ለመምህራን የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ርዕስ ጋር በተያያዘ የመምህራንን ስሜት (Feeling) ለማወቅና ከተማሪዎቹ ምላሽ ጋር ለማገናዘብ ይረዳል ተብሎ የተዘጋጀ ነው:: እንደተማሪዎቹ መጠይቅ ሁሉ የመጀመሪያው ክፍል መምህራን ስለራሳቸው ሁኔታ

ምላሽ የሚሰጡበት ነው። በሁለተኛ ክፍል ሥር የቀረቡት መጠይቆች ውስንና ልቅ ጥያቄዎችን ያካተቱ ናቸው። በሊከርት እስኬል የአለካክ ስልት መሰረት፡- በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ አልስማማም እና ፍጹም አልስማማም በማለት የሚመለሱ 10 ጥያቄዎች ቀረበዋል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲዳብር ምክንያት ይሆናሉ ተብለው በአጥኚው የተዘረዘሩትን ስምንት ተላውጦች (Variables) እንደ ችግሩ ክብደት በደረጃ እንዲያስቀምጡ የሚጋብዙ ጥያቄዎችም ቀርበላቸዋል። እነዚህ ተላውጦዎች ለተማሪዎች ከተሰጡ ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው የሁለቱን ምላሽ ለማስተያየት (ለማነፃፀር) ተብሎ የተካተተ ክፍል ነው። በመጨረሻም መምህራን የየራሳቸውን አስተያየት የሚያሰፍሩበት ልቅ (Open) የሆኑ ሶስት ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል። በዚሁ መሠረት የጥናቱ ዓላማ ተገልጾላቸው መጠይቁን እንዲሞሉ የተሰጣቸው አስር መምህራን በሙሉ መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል።

## 3.2.2. ቃለ መጠይቅ

ከጽሑፍ መጠይቅ ቀጥሎ አጥኚው እንደ መረጃ ምንጭነት የተገለገለበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ይኸውም ከፊል ስርዓታዊ (Semi structured) በሆነ መልክ የተዘጋጁ ጥያቄዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ያላቸውን አመለካከትና ትምህርቱ ከከፍተኛ ትምህርት የመግቢያ ፈተና ውጭ መሆኑ ያሳደረባቸው ስሜት በግንባር ለመረዳት ቃለ መጠይቁ የተዘጋጀ ሲሆን ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች ወላጆች በማቅረብ ምላሻቸው በመቅረፀ ድምፅ ተቀድቶ ተተንትኗል።

### 3.2.2.1. የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ

ለተማሪዎች የተዘጋጁት ሰባት ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ አጥኚው ከአምስቱ ት/ቤቶች በነሲብ አንድ አንድ ተማሪ በመውሰድ ከ3 ሴት ተማሪዎችና ከ2 ወንድ ተማሪዎች ጋር ቃለመጠይቅ አድርጓል።

### 3.2.2.2. የመምህራን ቃለመጠይቅ

ከምኒልክ፣ ከመድሐኒዓለም፣ ከቡሻፍቱና ሐዋስ ት/ቤቶች የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ከአራቱ ጋር ቃለመጠይቅ ተካሂዷል። ለእያንዳንዳቸው አምስት ጥያቄዎችን ያህል በማቅረብ ከምላሻቸው ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመያዝ ተሞክሯል።

### 3.2.2.3. የተማሪ ወላጆች ቃለመጠይቅ

ከተማሪዎችና ከመምህራን በተጨማሪ ስለትምህርትና ስለመሰናዶ መርሀግብር ግንዛቤ ላላቸው ከሶስት የመሰናዶ ተማሪዎች ወላጆች ጋር ቃለመጠይቅ በማካሄድ አስተያየቶቻቸውን ለማሰባሰብ ተችሏል።

### 3.2.3. ምልከታ

አጥኚው ተማሪዎችና መምህራን በጽሑፍና በቃለመጠይቅ ከሰጡት ምላሾች ጋር በተገናዘበ መንገድ አዳዲስ መረጃዎችንም በክፍል ምልከታ ለማግኘት ሞክሯል። በዚሁ መሠረት በሶስት ትምህርት ቤቶች የሁለት የሁለት ክፍለ ጊዜ በአጠቃላይ የስድስት ክፍለ ጊዜ የክፍል ምልከታ ተደርጓል። በምልከታው ወቅት የአብዛኛው ትኩረት የተደረገባቸው ነገሮች የክፍለ ጊዜው መርሀግብር፣ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ባላቸው ተሳትፎና ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራን ያላቸውን ተነሳሽነት ላይ ነበር።

## 3.3. የመረጃዎች አተናተን ስልቶች

ከተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን የተሰበሰቡት መረጃዎች ሁለት አብይ ክፍሎች አሏቸው። የተማሪው መጠይቅ የመጀመሪያው ክፍል ስለራሱና ስለቤተሰቡ አጠቃላይ ዳራ የሚመለከት ክፍል ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት ለመመልከት የሚያስችሉና በተለያየ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። መምህራኑም እንደዚሁ የመጀመሪያው አጠቃላይ ዳራቸው የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ መምህራኑ የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች ለቋንቋ ያላቸውን አመለካከት የሚመለከቱ ጥያቄዎችን፣ መምህራኑ ለአስተምህሮው ያላቸውን ፍላጎት (ስሜት) የሚዳስሱ፣ እንደዚሁም በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት ሊፈጥሩ የሚችሉ ተላውጦች የሚዳኙበት ወዘተ ጥያቄዎች የቀረቡበት ክፍል ነው።

መረጃዎቹ እንደተሰበሰቡ በየት/ቤቶቹ ተለይተዋል። በየት/ቤቶቹ ከተለዩ በኋላ ለእያንዳንዱ ተማሪ ቅጽ መለያ ቁጥር ተሰጥቷል። መለያ ቁጥር ከተሰጣቸው በኋላ የእያንዳንዱ ተማሪ መልስ "ታሊ" ተደርጓል፤ አስተያየቶችና መልሶች በመልክ በመልካቸው አንድ ላይ ተደራጅተዋል። ታሊውና ድልደላው ከተጠናቀቀ በኋላ የእያንዳንዱ ጥያቄ አማራጭ መልሶች በምን ያህል አፌሴት እና ኢአፌሴት ተማሪዎች እንደተመረጡ ታውቆ ተመዝግቧል። ከዚያም ለእያንዳንዱ ጥያቄ አማራጭ መልሶች መቶኛ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ደግሞ አማካይ ነጥብ ለአፌሴቶች፣ ኢአፌሴቶች እና ለጠቅላላው ተሳታፊ ስሌት ተሰርቷል። የመምህራኑንም እንደዚሁ የመለያ ቁጥር በመስጠት፣ ታሊ በማድረግ የተሰጡትን አስተያየቶችና መልሶች በመልክ በመልካቸው የመመዝገቡ ሥራ ተከናውኗል። እንደዚሁም ለእያንዳንዱ ጥያቄ አማራጭ መልሶች በምን ያህል መምህራን እንደተመረጡ ተለይቷል። ለእያንዳንዱ ጥያቄም አማካይ ነጥብ ተሰልቶለታል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሂደቶች በሙሉ ከተከናወኑ በኋላ ከመቶኛ እና አማካይ ነጥቦች በተጨማሪ ይበልጥ ትክክለኛ ውጤት ለማግኘት ሲባል ተጨማሪ እስታትስቲካዊ ሥራዎች ተሰርተዋል። ይኸውም ከተሰበሰበው መረጃ አንፃር ተማሪዎቹ በቋንቋው ላይ

ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል፣ የአመለካከቱ አድማስ ደግሞ በአፈፈት እና በኢአፈፈት መካከል ልዩነት ያሳይ እንደሆነ፣ ይህ የቋንቋው ለተቋም መግቢያ ፈተና አለመስጠት ለቋንቋው ይሰጡት የነበረውን ደረጃ (Status) ቀንሶባቸው እንደሆነ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ተላውጦች እውነትም ተፅዕኖ አሳድሯል ወይ? የሚለውን ለማረጋገጥ የተመዘገበው ውጤት በ"t-test" ተለክቷል። ከዚህ በተጨማሪም እያንዳንዱ ጥያቄ ከተመዘገበው ውጤት አንፃር ተተንትኗል፣ አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ላይ መረጃዎቹ በሠንጠረዥ ላይ ተቀናብረው ቀርበዋል። በጽሑፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ የተማሪዎችና የመምህራን ምላሽ በንጽጽር መልክ ተተንትነዋል። በመጨረሻም ከጽሑፍ መጠይቆች፣ ከቃለመጠይቆች እና ከምልከታ የተገኙት መረጃዎች እየተጠቀሱ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

## 3.4 የመረጃዎች ስሌታዊ አሠራር

መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ አዎንታዊና አሉታዊ የሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ተለይተዋል። በእያንዳንዱ ጥያቄ ውስጥ፣ ስንት በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፡ ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ አልስማማም እና ፍፁም አልስማማም የሚሉ ምላሾች እንደተገኙ ተለይቶ ተመዝግቧል። የአዎንታዊና አሉታዊ ዐረፍተ ነገሮች ውጤት በሚከተለው ዋጋ መሠረት ተመዝግቧል።

### አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር

| | |
|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 5 |
| እስማማለሁ | 4 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 3 |
| አልስማማም | 2 |
| ፍፁም አልስማማም | 1 |

### አሉታዊ ዐረፍተነገሮች

| | |
|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 1 |
| እስማማለሁ | 2 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 3 |
| አልስማማም | 4 |
| ፍፁም አልስማማም | 5 |

ውጤቶቹ በዚህ መልክ ከተመዘገቡ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመላሾች ብዛት በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል።

መቶኛ የተሰላበት ቀመር = የመላሽ ብዛት ሲባዛ በመቶ ሲካፈል ለጠቅላላ መላሽ ብዛት።

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከመቶኛ በተጨማሪ የተገኘው ምላሽ በመላሾች ብዛት ተከፍሎ አማካይ ነጥብ ተቀምጦለታል። ይህንኑ በምሳሌ አስደግፈን እንመልከት።

የአማካይ ነጥብ ቀመር = የተገኘው ምላሽ ድምር ሲካፈል ለመላሾች ብዛት።

# ምዕራፍ አራት

## ውጤቶችና ትንታኔያቸው

## 4.1. የጽሑፍ መጠይቅ መላሽ ተማሪዎች አጠቃላይ ዳራ

### 4.1.1. ፆታ

በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለፀው በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች ከሁለት መስተዳድር የተወጣጡ ናቸው። ከአዲስ አበባ መስተዳድር ለአማርኛ ቋንቋ አፊፊት የሆኑ 200 የመሰናዶ ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከምስራቅ ሸዋ ዞን ኢአፊፊት የሆኑ 200 የመሰናዶ ተማሪዎች በድምሩ 400 ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። የእነዚህን የ400 ተማሪዎች የፆታ ተዋዕኦን ስንመለከት 254(63.5%) ወንዶች ሲሆኑ፣ ሴቶች ደግሞ 146 (36.5%) ናቸው። ለዝርዝሩ ሠንጠረዡን ይመልከቱ።

ሠንጠረዥ አራት፡- የተማሪዎችን የፆታ ስብጥር ይገልፃል።

| ፆታ | አፊፊት ተማሪዎች | % | ኢአፊፊት | % | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | 121 | 60.5 | 133 | 66.5 | 254 | 63.5 |
| ሴ | 79 | 39.5 | 67 | 33.5 | 146 | 36.5 |
| ድ | 200 | 100 | 200 | 100 | 400 | 100 |

### 4.1.2. ዕድሜ

ዝቅተኛው ዕድሜ 15፣ ከፍተኛው ደግሞ 25 ይሁን እንጂ የአብዛኛዎቹ ዕድሜ ከ17-19 ሆኖ እናገኛለን። ለአቀራረቡ እንዲያመች ሶስት ቦታ በመክፈል በሰንጠረዥ አምስት ላይ ዝርዝሩን ለማሳየት ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ አምስት፡- የዕድሜ ሁኔታን ይገልፃል

| ፆታ | 15-17 | % | 18-20 | % | ከ20 በላይ | % | ዕድሜያቸውን ያላስፈሩ | % | ጠቅላላ ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | 62 | 15.5 | 159 | 39.75 | 16 | 4.0 | 17 | 4.25 | 254 | 63.5 |
| ሴ | 60 | 15 | 79 | 19.75 | 5 | 1.25 | 2 | .5 | 146 | 36.5 |
| ድ | 122 | 30.5 | 238 | 59.25 | 21 | 5.25 | 19 | 4.75 | 400 | 100 |

### 4.1.3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ

የጥናቱ ርዕስ እንደሚያስረዳው የአማርኛ ቋንቋ አፊፊት እና ኢአፊፊት የሆኑ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ማነጻጸር ነው። በዚሁ መሠረት መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች መካከል 200 (50%) ለቋንቋው አፊፊት ሲሆኑ፣ 200 (50%) ደግሞ ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፊፊት የሆኑ ተማሪዎች ናቸው።

### 4.1.4. የቤተሰብ የቋንቋ አጠቃቀም

የተማሪ ቤተሰቦች ቤት ውስጥ በብዛት የሚግባቡት ወይም የሚገለገሉበትን ቋንቋ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ የተገኘው ውጤት በአፊፊት እና በኢአፊፊት ቤተሰብ በመክፈል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ስድስት፡- "ሀ" የአፊፊት ተማሪዎች ቤተሰብ

| አማርኛ | % | ሌላ ቋንቋ የሚገለገሉ | % | አማርኛን እና ሌላ ቋንቋ | % | ሳይገልፁ የቀሩ | % | ጠቅላላ ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 173 | 86.5 | 7 | 3.5 | 8 | 4 | 12 | 6 | 200 | 100 |

ሠንጠረዥ ስድስት "ለ" - የኢአፊፊት ተማሪዎች ቤተሰብ

| የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚገለገሉ | % | አማርኛ የሚገለገሉ | % | አማርኛ እና አፍ መፍቻ | % | ሳይገልፁ የቀሩ | % | ጠቅላላ ብዛት | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 74 | 37 | 95 | 47.5 | 13 | 6.5 | 18 | 9 | 200 | 100 |

ከሠንጠረዥ "ሀ" መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የአብዛኞዎቹ ተማሪዎች ቤተሰብ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ይሁን እንጂ፣ የሁሉም ቤተሰብ መግባቢያ ቋንቋ እንዳልሆነ እንገነዘባለን፡፡ ተማሪዎቹ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ይፍቱ እንጂ የአንዳንዶቹ ተማሪዎች ቤተሰብ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ በተነሳ የእያንዳንዱ ቤተሰብ የቤት ውስጥ ቋንቋ ትግርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ጉራጊኛ፣ ስልጥኛ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

በሰንጠረዥ "ለ" የአማርኛ ቋንቋ ተገልጋይ ቤተሰብ ቁጥር ወይም በመቶኛ መብለጡ ሊያስገርመን አይገባም፡፡ Gardner በOller and Richard (1975) Lamber and Klineborg (1967)'ን ጠቅሰው ቤተሰብ በታላሚው ቋንቋ እና ለቋንቋው ባለቤቶች አዎንታዊ አመለካከት ካላቸው ቋንቋውን አዘውትረው እንደሚገለገሉበት፣ ልጆቻቸው ቋንቋውን ሲማሩም ሆነ ቋንቋውን ሲግባቡ እንደሚያበረታቱአቸው ይጠቁሙናል፡፡ ይህ የቤተሰብ ሁኔታ ሊሆን ይችላል ተማሪዎቹ አማርኛን ከአፍ መፍቻቸው ይልቅ መርጠው እንዲማሩም የገፋፋቸው፡፡

### 4.1.5. የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ

የተማሪዎቹ ወላጆች የትምህርት ደረጃ ካልተማሩት እስከ ፒ.ኤች.ዲ. ደረጃ የሚሄድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአብዛኞዎቹ ተማሪዎች (የአፊፊቶቹም ተማሪዎች ሆነ የኢአፊፊቶቹ) የቤተሰብ የትምህርት ደረጃ ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ያልዘለለ ነው፡፡ በተለይ እናቶች የአፊፊቶቹ የ16.6%፣ የኢአፊፊቶች ደግሞ 23.5% ያልተማሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ቤተሰቡ ከትምህርት የ2ኛ ደረጃ አንጻር ስንመለከት ያልተማሩ 15.6%፣ መሠረተ ትምህርትና 1ኛ ደረጃ 27.6%፣ የ2ኛ ደረጃ 29.75%፣ ሠርተፊኬት 1.1%፣ ዲኘሎማ 9.5%፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 8%፣ ማስተርስ 0.75% እና ፒ.ኤች.ዲ. 0.25% ሲሆኑ፣ የቤተሰቦቻቸው የትምህርት ደረጃ ያልጠቀሱት 7.5% ናቸው፡፡ ዝርዝሩን ከሠንጠረዥ ሰባት ይመልከቱ፡፡

ሠንጠረዥ ሰባት፡- የቤተሰብን የትምህርት ደረጃ ያመለክታል

| | ያልተማሩ | % | መ/ት እና 1ኛ ደረጃ | % | 2ኛ ደረጃ | % | ሰርተፊኬት | % | ዲኘሎማ | % | የመጀመሪያ ዲግሪ | % | የማስተርስ ዲግሪ | % | ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ | % | ያልመለሱ | % | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአፈፌት ቤተሰብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| አባት | 17 | 8.5 | 30 | 15 | 64 | 32 | 1 | 0.5 | 32 | 16 | 34 | 17 | 5 | 2.5 | - | - | 18 | 9 | 200 | |
| እናት | 33 | 16.5 | 51 | 25.5 | 57 | 28.5 | 5 | 2.5 | 26 | 13 | 8 | 4 | - | - | - | - | 20 | 10 | 200 | |
| ድምር | 50 | 12.5 | 81 | 20.25 | 121 | 30.25 | 6 | 1.5 | 58 | 14.5 | 42 | 10.5 | 5 | 1.25 | - | - | 38 | 9.5 | 400 | |
| የኢአፈፌት ቤተሰብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| አባት | 28 | 14 | 66 | 33 | 60 | 30 | 1 | 0.5 | 14 | 7 | 18 | 9 | 1 | 0.5 | 1 | 0.5 | 11 | 5.5 | 200 | |
| እናት | 47 | 23.5 | 74 | 37 | 57 | 28.5 | 2 | 1 | 4 | 2 | 4 | 2 | - | - | 1 | 0.5 | 11 | 5.5 | 200 | |
| ድምር | 75 | 18.75 | 140 | 35 | 117 | 29.25 | 3 | 1.5 | 18 | 4.5 | 22 | 5.5 | 1 | .25 | 2 | 0.5 | 22 | 5.5 | 400 | |
| ጠቅላላ ድ | 125 | 15.6 | 221 | 27.6 | 238 | 29.75 | 9 | 1.1 | 76 | 9.5 | 64 | 8 | 6 | .75 | 2 | .25 | 60 | 7.5 | 800 | |

### 4.1.6. የቤተሰብ የሥራ ሁኔታ

የአፊፊት ሆነ የኢአፊፊት ተማሪዎች በአባት በኩል ከፍተኛውን መቶኛ (36.5፣32.5) የሸፈኑት በመንግስት ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው:: በአንፃሩ በእናቶች በኩል የተመለከትን እንደሆነ የአፊፊቶች 48% ፣ የኢአፊፊቶቹ 59.5% የቤት እመቤቶች ናቸው:: የተሟላ መረጃ ከሠንጠረዥ 8 ማግኘት እንችላለን::

**ሠንጠረዥ ስምንት:- የቤተሰብ የሥራ ሁኔታን ገላጭ ሠንጠረዥ**

| | ገበሬ | % | ነጋዴ | % | የመ. ሠራተኛ | % | የግል ሥራ | % | ሾፌር | % | ወታደር | % | ጡረተኛ | % | የቤት እመቤት | % | ያልጠየቁ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአፊፊት ቤተሰብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| አባት | 9 | 4.5 | 41 | 20.5 | 73 | 36.5 | 30 | 15 | 14 | 7 | 1 | 0.5 | 5 | 2.5 | - | - | 27 | 13.5 |
| እናት | - | | 19 | 9.5 | 48 | 24 | 6 | 3 | - | - | - | - | - | - | 96 | 48 | 31 | 15.5 |
| ድምር | 9 | 2.25 | 60 | 15 | 121 | 30.25 | 36 | 9 | 14 | 3.5 | 1 | 0.25 | 5 | 1.25 | 96 | 24 | 58 | 14.5 |
| የኢአፊፊት ቤተሰብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| አባት | 48 | 24 | 41 | 20.5 | 65 | 32.5 | 12 | 6 | 14 | 7 | 13 | 6.5 | - | - | - | - | 7 | 3.5 |
| እናት | - | - | 29 | 14.5 | 29 | 14.5 | 4 | 2 | - | - | 2 | 1 | 1 | 0.5 | 119 | 59.5 | 16 | 8 |
| ድምር | 48 | 12 | 70 | 17.5 | 94 | 23.5 | 16 | 4 | 14 | 3.5 | 15 | 75 | 1 | 0.25 | 119 | 29.75 | 23 | 5.75 |
| ጠቅላላ ድ | 57 | 7.1 | 130 | 16.25 | 215 | 26.9 | 52 | 6.5 | 28 | 3.5 | 16 | 2 | 6 | 0.75 | 215 | 26.9 | 81 | 10.1 |

## 4.2. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1. ወደ ከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ ባለመካተቱ የሚያሳድረው ተጽዕኖ

ይህ የመጀመሪያውና ዋነኛው ተላውጦ ነው:: በዚህ ሥር የቀረቡት ጥያቄዎች:-

ሀ/ በሊከርት እስኬል መሠረት የቀረቡ ሁለት አዎንታዊና ሁለት አሉታዊ በድምሩ አራት ጥያቄዎች ናቸው::

ለ/ በ"ሠ" ትዕዛዝ ሥር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ስምንት ተላውጦች ተዘርዝረዋል:: (አባሪ "ሀ"ን ይመልከቱ) ከስምንቱ ተላውጦዎች መካከል አንዱ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ" የሚል ነው:: የመጠይቁ ትዕዛዝ እነዚህን በምክንያትነት የተዘረዘሩትን ተላውጦች እንደችግሩ ክብደት በደረጃ ማስቀመጥ (Ranking) 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ. . . 8ኛ በማለት የችግሩን ደረጃ መጠቆም ነው:: የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ተቋም መግቢያ ውስጥ አለመካተቱ እንደ ችግር ምን ያህል በተማሪዎች ዘንድ ቦታ አግኝቷል? የሚለውን ለማሳወቅ ይረዳል ተብሎ የታሰበ ጥያቄ ነው::

ሐ/ በመሰናዶ ደረጃ የሚማሩአቸውን 10 የትምህርት ዓይነቶች በጣም ከሚወዱት በመጀመር የ1ኛ፣2ኛ፣. . . 8ኛ በደረጃ ማስቀመጥ ሆኖ ለመጨረሻዎቹ ሁለት ደረጃዎች (9 እና 10) ቦታ አልተደረገላቸው::

የዚህ ጥያቄ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ እየታወቀ በተማሪዎቹ ዘንድ ያለው የመወደድ ደረጃ የቱን ያህል ነው? የሚለውን ምላሽ ለማግኘት ነው::

በመቀጠል በ4.3.1. ላይ የሠፈረውን ተላውጦ አስመልክቶ በሶስት መልክ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡትን ምላሾችና የተገኘውን ውጤት እንመለከታለን::

ወደ ጥያቄዎቹ ዝርዝር ውስጥ ከመግባታችን በፊት በእያንዳንዱ ጥያቄ ውስጥ የሚደጋገሙ ቃላት አማራጭ አሰራር መጠቀሙ አስፈላጊ ነው:: በዚህ መሠረት:-

ሀ/ በማንኛውም የውጤት ትንተና ውስጥ የመጀመሪያው አሃዝ የአፈፌት ሲሆን፣ ሁለተኛው የኢአፈፌት ነው::

ለ/ አንዳንድ ቦታ አ፣ኢ፣ድ፣ የሚሉት:-

አ = አፈፌት ፣ ኢ = ኢአፈፌት ፣ ድ = ድምር ማለት ነው::

**1.1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ለቋንቋው እስጥ የነበረውን ቦታ ቀንሶብኛል::**

ጥያቄው አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ነው:: የተመዘገበው ምላሽ 194 እና 192 በድምሩ የ386 ተማሪዎች ነው:: ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት፣ በጣም እስማማለሁ 58 (30%) 67(35%) በድምሩ 125(32.4%)፣ እስማማለሁ 54(27.8%) 44(22.9%) በድምሩ 98(25.4%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 20(10.3%) 25(13%) በድምሩ 45 (11.7%)፣ አልስማማም 30(15.4%) 35(18.2%) በድምሩ 65(16.8%)፣ ፍጹም አልስማማም 32(16.5%) 21(10.9%) በድምሩ 53(13.7%) ሆኖ እናገኛለን:: አማካይ ነጥቦች ደግሞ 3.4፣3.5፣3.5 ናቸው::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 58 | 67 | 125 | 290 | 335 | 625 | 30.0 | 35 | 32.4 |
| እስማማለሁ | 54 | 44 | 98 | 216 | 176 | 392 | 27.8 | 22.9 | 25.4 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 20 | 25 | 45 | 60 | 75 | 135 | 10.3 | 13.0 | 11.7 |
| አልስማማም | 30 | 35 | 65 | 60 | 70 | 130 | 15.4 | 18.2 | 16.8 |
| ፍጹም አልስማማም | 32 | 21 | 53 | 32 | 21 | 53 | 16.5 | 10.9 | 13.7 |
| ድምር | 194 | 192 | 386 | 658 | 677 | 1335 | 100 | 100 | 100 |

ለ "1.1" ጥያቄ በተመዘገበው ውጤት መሠረት 57.8% አፈ.ፈ.ትና 57.9% ኢ.አፈ.ፈ.ት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ለቋንቋው ይሰጡት የነበረውን ቦታ (Status) እንደቀነሰባቸው ገልጸዋል:: በአንጻሩ 31.9% አፈ.ፈ.ትና 29.1% ኢ.አፈ.ፈ.ት ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጡትን ቦታ እንዳልቀነሱ ነው የገለጹት:: 10.3% አፈ.ፈ.ትና 13% ኢ.አፈ.ፈ.ት ተማሪዎች መወሰን አልቻሉም:: ከዚህ ውጤት ማጠቃለል የምንችለው ነገር ቢኖር፣ አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች ቋንቋው ለተቋምም መግቢያ ባለመሰጠቱ ይሰጡት የነበረውን ቦታ እንደቀነሰባቸው ነው:: እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር "ለቋንቋው የምንሰጠው ቦታ አልቀነሰም" ያሉትም አሃዝ ቀላል እንዳልሆነ ነው:: ነገር ግን ከሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ከተገኘው መረጃና በቃለመጠይቅና በምልከታ ለማረጋገጥ የተቻለው ቋንቋውን ይወዱታል፤ ነገር ግን ፈተና ስለሌለው ደግሞ ቦታ አይሰጡትም:: የአገራችንን ተማሪዎች ባህሪ በመጠኑ መለስ ብለን ስንመለከት፣ አንዱ የትምህርት ዓይነት ፈተና የለውም ተብሎ ይቀርና ሙከራ ወይም ፈተና አለ በተባለ ሰሞንና በሌላ ጊዜ ለትምህርቱ የሚሰጡት ትኩረት በጣም ይለያያል:: ለእውቀት ብሎ የመማሩ ነገር ብዙም የተለመደም አይምስልም:: ይህ ተማሪዎቹ ለቋንቋው ያላቸው ፍቅር ነው የያዛቸው እንጂ እርግፍ አድርገው ሊተውቱም ይችሉ ነበር::

በሌላ በኩል በአፈፌት ተማሪዎችም ሆነ በኢአፈፌት በኩል የተገኘው ውጤት በጣም የተቀራረበ ነው። ይህ ደግሞ በሁለቱም ወገን በቋንቋው ላይ ያላቸው አመለካከት ተቀራራቢ መሆኑን ያሳያል።

**1.2. የአማርኛ ቋንቋ በከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በቋንቋው ላይ ያለኝን አመለካከት አልለወጠም።**

ዐረፍተነገሩ አሉታዊ ዐረፍተነገር ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት 200 እና 197 በድምሩ 397 ተማሪዎች ናቸው። ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት በጣም እስማማለሁ 34(17%) 15(7.6%) በድምሩ 49(12.3%)፣ እስማማለሁ 29(14.5%) 47(23.9%) በድምሩ 76(19.1%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 12(6%) 25(12.7%) በድምሩ 37(9.4%)፣ አልስማማም 71(35.5%) 83(42.1%) በድምሩ 154(38.8%)፣ በፍጹም አልስማማም 54(27%) 27(13.7%) በድምሩ 81(20.4%) ሆኖ እናገኛለን። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.4፣ 3.3፣ 3.4 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 34 | 15 | 49 | 34 | 15 | 49 | 17 | 7.6 | 12.3 |
| እስማማለሁ | 29 | 47 | 76 | 58 | 94 | 152 | 14.5 | 23.9 | 19.1 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 12 | 25 | 37 | 36 | 75 | 111 | 6 | 12.7 | 9.4 |
| አልስማማም | 71 | 83 | 154 | 284 | 332 | 616 | 35.5 | 42.1 | 38.8 |
| ፍጹም አልስማማም | 54 | 27 | 81 | 270 | 135 | 405 | 27 | 13.7 | 20.4 |
| ድምር | 200 | 197 | 397 | 682 | 651 | 1333 | 100 | 100 | 100 |

በተገኘው ውጤት መሰረት 13.5% አፈፌት እና 31.5% ኢአፈፌት ተማሪዎች አማርኛ በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት በቋንቋው ላይ ምንም የአመለካከት ለውጥ እንዳላስከተለባቸው ገልጸዋል። በአንጻሩ ደግሞ 62.5% አፈፌት እና 55.8% ኢአፈፌት የመሰናዶ ተማሪዎች ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ በቋንቋው ላይ የአመለካከት ለውጥ እንዳስከተለባቸው ገልፀዋል። እንዲሁም መምህራን በተራ ቁጥር "1" (አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ) "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ ከመታወቁ በፊትና ከታወቀ በኋላ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ ተከስቷል" በሚለው ጥያቄ ከአሥሩ መምህራን መካከል ስምንቶቹ በሃሳቡ ተስማምተዋል። ከዚህ በተጨማሪ በተ.ቁ "2" (አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ) ላይ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተናነት መሰጠቱ አለመሰጠቱ

በተማሪዎች አመለካከት ላይ ያመጣው ለውጥ የለም" ለሚለው የተገኘውን መልስ ስንመለከት በሃሳቡ የተስማሙ ሁለት መምህራን ብቻ ሲሆኑ፣ ሃሳቡን የተቃወሙት ግን ስምንት ናቸው። ከነዚህ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው አብዛኞዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ባለመሰጠቱ ምክንያት በቋንቋው ላይ የነበራቸው አዎንታዊ አመለካከት ተቀይሯል። ታሪኩ ፋንታዬ (1988) የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንደነበራቸው በጥናታቸው አረጋግጠው ነበር። ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ ያ የነበረው አዎንታዊ አመለካከት እየተለወጠ መምጣቱን ይህ መረጃ ያመለክተናል።

### 1.3. ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ አማርኛን ባልማረው ደስታውን አልችልም።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተነገር ሲሆን፣ ከ199 እና ከ199 በድምሩ ከ398 ተማሪዎች የተገኘው ምላሽ በሚከተለው መልክ ተጠናቅሮ ቀርቧል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 15 | 13 | 28 | 15 | 13 | 28 | 7.5 | 6.6 | 7.0 |
| እስማማለሁ | 9 | 16 | 25 | 18 | 32 | 50 | 4.5 | 8.0 | 6.3 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 22 | 15 | 37 | 66 | 45 | 111 | 11.1 | 7.5 | 9.3 |
| አልስማማም | 48 | 38 | 86 | 192 | 152 | 344 | 24.1 | 19.1 | 21.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 105 | 117 | 222 | 525 | 585 | 1110 | 52.8 | 58.8 | 55.8 |
| ድምር | 199 | 199 | 398 | 816 | 827 | 1643 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥብ   አ = 4.1   ኢ. =4.2   ድ =4.1

76.9% አፈ.ፈትና 77.9% ኢ.አፈ.ፈት ተማሪዎች ሐሳቡን ሲቃወሙት፣ 12% አፈ.ፈትና 14.6% ኢ.አፈ.ፈት ሃሳቡን ደግፈውታል። ይህ የሚያመለክተን ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት መልካም አመለካከት እንዳላቸው ነው። ይህ መልካም አመለካከት ደግሞ በመግቢያ ፈተናው ቢታገዝ ምንኛ ጥሩ በሆነ ነበር!

1.4. ቋንቋውን ለተቋም መግቢያ ፈተናነት ቢሰጥ የትምህርት አቀባበሉን አዎንታዊ የማድረግ ሃይል አለው።

ጥያቄው አዎንታዊ ሲሆን ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች በጠቅላላው 396 ናቸው። ዝርዝር ውጤቱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 76 | 63 | 139 | 380 | 315 | 695 | 38.2 | 31.9 | 35.1 |
| እስማማለሁ | 46 | 47 | 93 | 184 | 188 | 372 | 23.1 | 23.9 | 23.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 35 | 40 | 75 | 105 | 120 | 225 | 17.6 | 20.3 | 18.9 |
| አልስማማም | 20 | 26 | 46 | 40 | 52 | 92 | 10.0 | 13.2 | 11.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 22 | 21 | 43 | 22 | 21 | 43 | 11.1 | 10.7 | 10.9 |
| ድምር | 199 | 197 | 396 | 731 | 696 | 1427 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች 3.7፣ 3.5፣ 3.6

ቋንቋው በተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ከተካተተ ለመማር ማስተማር ሂደት ስኬታማነት የበኩሉን ድርሻ እንዳለው የገለጹት 61.3% አፈ.ፈት እና 55.8% ኢ.አፈ.ፈት ተማሪዎች ናቸው። ሐሳቡን የተቃወሙት ደግሞ 21.1% አፈ.ፈት እና 23.9% ኢ.አፈ.ፈት ተማሪዎች ናቸው። መወሰን ያልቻሉት 18.9% ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ቋንቋው በመግቢያ ፈተናነት ቢሰጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ እንደሚያደርገው ያምኑበታል። ከዚህ ጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያለው ጥያቄ ለመምህራንም ቀርቦ ነበር። በዚሁ መሰረት በመምህራን መጠይቅ በተራ ቁጥር "5" (አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ) ላይ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ላይ ቢሰጥ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉት ያደርጋቸዋል" በሚል ተጠይቆ፣ የተሰጠው ምላሽ አስሩም መምህራን በጣም እስማማለሁ ብለው በመመለሳቸው አማካይ ነጥቡ 5.0 ሆኗል። ስለዚህ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን ለተቋም የመግቢያ ፈተናነት ቢሰጥ የመማር ማስተማሩን ሥራ በጥሩ መንፈስ ለማካሄድ እንደሚረዳ ያምኑበታል።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተዘረዘሩትን ተላውጠዎች ተማሪዎቹ እንደተፅዕኖው ክብደት በደረጃ አስቀምጠዋል። እያንዳንዱ ተላውጠ በምን ያህል ተማሪ፣ በምን ደረጃ እንደተቀመጠ ዝርዝር ውጤቱ በሰንጠረዥ መልክ ተቀምጧል። ስለዚህ ሁኔታውን በጥልቀት ለማወቅ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ ዘጠኝ ያለውን ጥንቅር ማየት ይመረጣል። ነገር ግን ስለምላሾቹ አለፍ አለፍ ብለን አንዳንዱን ሃሳቦች ብናነሳ ስለሁኔታው የበለጠ ግንዛቤ እንድንጨብጥ አጋዥ ይሆናል

የሚል እምነት አለ። ስለዚህ በመቀጠል እንደችግሩ ክብደት በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከ1-3 የተቀመጡትን ተላውጦች በመጠኑ ዘርዘር በማድረግ ለማየት ይሞከራል።

ከ392 መላሾች መካከል በ86 (21.9%) በአንደኛ ደረጃ የተመረጠው "አማርኛ ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ" የሚለው ተላውጦ ነው። የቋንቋው ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረ በ1.1፣ በ1.2 እና በ1.4 ላይ የተመዘገቡት ውጤቶች አሳይተውናል። በዚህ ተላውጦችን እንደችግራቸው ክብደት በደረጃ ማስቀመጡ ላይም የተንፀባረቀው ይኸው ነው። የቋንቋው ለፈተና አለመሰጠት ትኩረት እንዲነፈግ፣ ዝቅ ተደርጎ እንዲታይ ወዘተ ትልቁን ድርሻ ተጫውቷል ማለት ይቻላል።

ሌላው በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከትን ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብለው ከተዘረዘሩት ስምንት ተላውጦች መካከል በ1ኛ ደረጃ በ77 (19.8%)፣ በ2ኛ ደረጃ በ65(16.8%) እና በ3ኛ ደረጃ በ61(15.7%) ላይ ተማሪዎች ያስቀመጡት "ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛ ቋንቋ እንደ ጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበራከት" የሚለው ተላውጦ ነው። በመሰናዶ ደረጃ ያሉት ተማሪዎች ስለቋንቋ ምንነት፣ ባህርያት ወዘተ የተሻለ ግንዛቤ አላቸው ብለው ቢገመቱም በ"2.6" ላይ "አማርኛ ጨቋኝ በመሆኑ በእርሱ ላይ ጥሩ አመለካከት የለኝም" የሚለውን ሀሳብ የሚደግፉት 11% ናቸው። እንዲሁም በ"2.7" ላይ "ለቋንቋዎች እኩል አክብሮት አለኝ" የሚለውን ሀሳብ የሚቃወሙት 9.1% ያህል ተማሪዎች መኖራቸው ግራ ያጋባል። ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ደግሞ ከተማሪ ባሻገር በወላጅ፣ በኅብረተሰብ ዘንድና አልፎ አልፎም በመገናኛ ብዙሃን የሚከሰት ጉዳይ መሆኑ ደግሞ ነገሩን ያከብደዋል።

በሶስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው ተላውጦ ደግሞ "ለአብዛኛዎቹ ክልሎች ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና ለራሳቸው ቋንቋ ቅድሚያ መስጠታቸው" የሚለው ነው። በእርግጥ ይህ ተላውጦ የግንዛቤ ጉድለት ከሚለው ጋር ተቀራራቢነት አለው። ቋንቋ የመግባቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን ብዙ ቋንቋ ማወቅ ከተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል ጋር እንደሚያግባባ፣ እንደሚያስተሳስር፣ ብዙ የሥራ ዕድል ሊፈጥር እንደሚችል ወዘተን አብሮ ያለማየት ችግር እንዳለ ይጠቁማል። ከዚህ በተጨማሪ ነገሮችን አስፍቶ ካለመመልከት የተነሳ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛው ቋንቋ ላይ የሚፈጥረው ጫና ሊሆን ይችላል።

ከእነዚህ ተላውጦዎች በተጨማሪ ወላጆች፣ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ዝቅተኛ ቦታና በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚደረጉት ቅስቀሳዎች በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከትን ለመፍጠር የሚጫወቱት ሚና ቀላል እንዳልሆነ ነው።

| አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብሩ የሚችሉ ተላውጦዎች | የመላሾች ዓይነት | 1ኛ ደረጃ | % | 2ኛ ደረጃ | % | 3ኛ ደረጃ | % | 4ኛ ደረጃ | % | 5ኛ ደረጃ | % | 6ኛ ደረጃ | % | 7ኛ ደረጃ | % | 8ኛ ደረጃ | % | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት መፃሕፍት ይዘትና አቀራረብ ሳቢ አለመሆን | አፈ.ፈ.ት | 14 | 7.4 | 23 | 12.2 | 27 | 14.4 | 16 | 8.5 | 19 | 10.1 | 29 | 15.4 | 36 | 19.2 | 24 | 12.8 | 188 | 100 |
| | ኢ.አፈ.ፈ.ት | 11 | 5.6 | 14 | 7.1 | 5 | 2.6 | 16 | 8.2 | 30 | 15.3 | 45 | 23 | 45 | 23 | 30 | 15.3 | 196 | 100 |
| | ድምር | 25 | 6.5 | 37 | 9.6 | 32 | 8.3 | 32 | 8.3 | 49 | 12.8 | 74 | 19.3 | 81 | 21.1 | 54 | 14.1 | 384 | 100 |
| አማርኛ ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ | አ | 54 | 28.1 | 16 | 8.3 | 13 | 6.8 | 19 | 9.9 | 17 | 8.9 | 18 | 9.4 | 23 | 11.9 | 32 | 16.7 | 192 | 100 |
| | ኢ. | 32 | 16 | 13 | 6.5 | 28 | 14 | 41 | 20.5 | 23 | 11.5 | 23 | 11.5 | 20 | 10 | 20 | 10 | 200 | 100 |
| | ድ | 86 | 21.9 | 29 | 7.4 | 41 | 10.5 | 60 | 15.3 | 40 | 10.2 | 41 | 10.5 | 43 | 11 | 52 | 13.3 | 392 | 100 |
| ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛ ቋንቋ እንደጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበራከት | አ | 29 | 15.3 | 26 | 13.7 | 31 | 16.3 | 29 | 15.3 | 24 | 12.6 | 26 | 13.7 | 13 | 6.8 | 12 | 6.3 | 190 | 100 |
| | ኢ. | 48 | 24.2 | 39 | 19.7 | 30 | 15.6 | 23 | 16.6 | 11 | 5.6 | 15 | 7.6 | 13 | 6.6 | 19 | 9.6 | 198 | 100 |
| | ድ | 77 | 19.8 | 65 | 16.8 | 61 | 15.7 | 52 | 13.4 | 35 | 9.0 | 41 | 10.6 | 26 | 6.7 | 31 | 8.0 | 388 | 100 |
| የመምህራን ብቁ ሆኖ አለመገኘት | አ | 22 | 11.9 | 22 | 11.9 | 17 | 9.2 | 25 | 13.5 | 20 | 10.8 | 28 | 15.1 | 23 | 12.4 | 28 | 15.1 | 185 | 100 |
| | ኢ. | 15 | 7.9 | 17 | 8.9 | 16 | 8.4 | 19 | 10 | 25 | 13.2 | 27 | 14.2 | 35 | 16.8 | 39 | 20.5 | 190 | 100 |
| | ድ | 37 | 9.9 | 39 | 10.4 | 33 | 8.8 | 44 | 11.7 | 45 | 12 | 55 | 14.7 | 55 | 14.7 | 67 | 17.9 | 375 | 100 |
| ለአብዛኛዎቹ ክልሎች ቋንቋው የሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና ለራሳቸው ቋንቋ ቅድሚያ መስጠታቸው | አ | 24 | 12.8 | 46 | 24.6 | 37 | 19.8 | 20 | 10.7 | 21 | 11.2 | 22 | 11.8 | 12 | 6.4 | 5 | 2.8 | 187 | 100 |
| | ኢ. | 44 | 22.2 | 38 | 19.2 | 31 | 15.7 | 26 | 13.7 | 19 | 9.6 | 17 | 8.6 | 10 | 5.1 | 13 | 6.6 | 198 | 100 |
| | ድ | 68 | 17.7 | 84 | 21.8 | 68 | 17.7 | 46 | 11.9 | 40 | 10.4 | 39 | 10.1 | 22 | 5.7 | 18 | 4.7 | 385 | 100 |
| በብሔራዊ ፈተና የአማርኛ ውጤት አማራጭ ውስጥ መግባቱ | አ | 6 | 3.4 | 10 | 5.7 | 17 | 9.7 | 13 | 7.4 | 32 | 18.1 | 24 | 13.6 | 28 | 15.9 | 46 | 26.1 | 176 | 100 |
| | ኢ. | 9 | 4.5 | 15 | 7.5 | 17 | 8.5 | 24 | 12 | 40 | 20 | 38 | 19 | 28 | 14 | 29 | 14.5 | 200 | 100 |
| | ድ | 15 | 4.0 | 25 | 6.6 | 34 | 9.0 | 37 | 9.8 | 72 | 19.1 | 62 | 16.5 | 56 | 14.9 | 75 | 19.9 | 376 | 100 |
| በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚደረጉ ቅስቀሳዎች | አ | 13 | 7.3 | 30 | 16.9 | 22 | 12.4 | 19 | 10.7 | 27 | 15.2 | 22 | 12.4 | 29 | 16.3 | 16 | 9.0 | 178 | 100 |
| | ኢ. | 22 | 11.3 | 39 | 20 | 37 | 19.0 | 27 | 13.8 | 19 | 9.7 | 13 | 6.7 | 15 | 7.7 | 23 | 11.8 | 195 | 100 |
| | ድ | 35 | 9.4 | 69 | 18.5 | 59 | 15.8 | 46 | 12.3 | 46 | 12.3 | 35 | 9.4 | 44 | 11.8 | 39 | 11.5 | 373 | 100 |
| ወላጆች፣ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆን | አ | 31 | 16.1 | 21 | 10.9 | 31 | 61.1 | 33 | 17.1 | 21 | 10.9 | 18 | 9.3 | 16 | 8.3 | 22 | 14.4 | 193 | 100 |
| | ኢ. | 20 | 10.3 | 18 | 9.2 | 36 | 18.5 | 17 | 8.7 | 30 | 15.4 | 25 | 12.8 | 25 | 12.8 | 24 | 12.3 | 195 | 100 |
| | ድ | 51 | 13.1 | 39 | 10.1 | 67 | 17.3 | 50 | 12.9 | 51 | 13.1 | 43 | 11.1 | 41 | 10.6 | 46 | 11.9 | 388 | 100 |

በሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብሩ የሚችሉ ተላውጦዎችን ደረጃ ያሳያል፡፡

ትዕዛዝ "መ" ሥር (አባሪ "ሀ"ን ይመልከቱ) "አሁን የምትማሩዋቸውን የትምህርት ዓይነቶች በጣም ከምትወዱት በመጀመር 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ. . . እያላችሁ ሁሉንም በደረጃ አስቀምጡ" ለሚለው መጠይቅ ተማሪዎች ምርጫቸውን በደረጃ አስቀምጠዋል:: የሁሉንም የትምህርት ዓይነት ደረጃ ማየቱ ያን ያህል አስፈላጊ ላይሆን ስለሚችል የአማርኛና የእንግሊዝኛን ቋንቋዎችን ብቻ በመውሰድ ለማነጻጸር ይሞከራል:: ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ተማሪዎቹ የሚማሩዋቸው የትምህርት ዓይነቶች 10 ሲሆኑ፣ በመጠይቁ ላይ ቦታ የተደረገላቸው ወይም የተቀመጠላቸው እስከ 8ኛ ደረጃ ላሉት ብቻ ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ ተማሪ ከሚማራቸው የትምህርት ዓይነቶች ሁለቱን ከደረጃ ውጭ ያደርጋል ማለት ነው:: በዚህ መሠረት የአማርኛና እንግሊዝኛ የምላሽ ውጤት የሚከተለውን ይመስላል::

| የትምህርቱ ዓይነት | በ1ኛ ደረጃ | በ2ኛ ደረጃ | በ3ኛ ደረጃ | በ4ኛ ደረጃ | በ5ኛ ደረጃ | በ6ኛ ደረጃ | በ7ኛ ደረጃ | በ8ኛ ደረጃ | ደረጃ ያልሰጡት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማርኛ | 42<br>10.5% | 35<br>8.75% | 33<br>8.25% | 47<br>11.75% | 43<br>10.75% | 36<br>9% | 42<br>10.5% | 38<br>9.5% | 84<br>21% | 400<br>100% |
| እንግሊዝኛ | 64<br>16% | 62<br>15.5% | 50<br>12.5% | 55<br>13.75% | 65<br>16.25% | 32<br>8% | 21<br>5.25% | 14<br>3.5% | 37<br>9.25% | 400<br>100% |

አማርኛ በ1ኛ፣ በ2ኛ እና በ3ኛ ደረጃ በ42(10.5%)፣ 35(8.75%)፣33(8.25%) ሲመረጥ፣ ደረጃ ያልሰጡ ደግሞ 84 (21%) ናቸው:: ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው አሃዝ ወይም ደረጃ ውስጥ ያላስገቡ ተማሪዎች ናቸው:: በአንጻሩ እንግሊዝኛን ስንመለከት ፐርሰንት ደረጃ ውስጥ ያላስገቡ ተማሪዎች ናቸው:: በአንጻሩ እንግሊዝኛን ስንመለከት 64(16%)፣(15.5%) 50(12.5%) ሲሆን፣ ደረጃ ያልሰጡት ደግሞ 37(9.25%) ብቻ ናቸው:: Hurlock (1996) እንደሚያስገነዝቡን በአንድ የትምህርት ዓይነት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ብለው የዘረዘሩአቸውን ሰባት ነጥቦች በክለሳ ድርሳን ውስጥ ማየታችን ይታወሳል:: ከነዚያ ነጥቦች መካከል የቋንቋውን ወይም የትምህርቱን ተፈላጊነትና የትምህርቱን ለማለፍ ሆነ ለመውደቅ የሚጫወተው ድርሻ እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይችላል:: የእንግሊዘኛ ቋንቋ በብሔራዊ ፈተና ወሳኝ ትምህርት (Compulsory subject) ነው፤ በክፍል ፈተናም ቢሆን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጤት ወሳኝ ነው:: ለከፍተኛ ተቋምም በመግቢያ ፈተናነት የሚሰጥ ብቸኛ ቋንቋ ነው፤ ያውም ወሳኝ ሚና ያለው:: ከዚህ በተጨማሪ ኀብረተሰቡ የተማሪውን ወላጅ ጨምሮ በቋንቋው ያመልካል:: በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል ተማሪው ከአማርኛ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ቦታ ሊሰጥ የቻለው::

ሠንጠረዥ አሥር፡- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የደረጃ ስብጥር የሚያሳይ

| የመላሾች ዓይነት | በ1ኛ ደረጃ | % | በ2ኛ ደረጃ | % | በ3ኛ ደረጃ | % | በ4ኛ ደረጃ | % | በ5ኛ ደረጃ | % | በ6ኛ ደረጃ | % | በ7ኛ ደረጃ | % | በ8ኛ ደረጃ | % | ደረጃ ያልሰጡ | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አፌ.ፈ.ት | 18 | 9 | 13 | 6.5 | 13 | 6.5 | 22 | 11 | 23 | 11.5 | 23 | 11.5 | 25 | 12.5 | 28 | 14 | 35 | 17.5 |
| ኢ.አፌ.ፈ.ት | 24 | 12 | 22 | 11 | 20 | 10 | 25 | 12.5 | 20 | 10 | 13 | 6.5 | 17 | 8.5 | 10 | 5 | 49 | 24.5 |
| ድምር | 42 | 10.5 | 35 | 8.75 | 33 | 8.25 | 47 | 11.75 | 43 | 10.75 | 36 | 9.0 | 42 | 10.5 | 38 | 9.5 | 84 | 21.0 |

## 4.2.2. ለአማርኛ ቋንቋ አፌፈት/ኢአፌፈት ከመሆን አንፃር

የዚህ ጥናት መሠረታዊ ነጥብ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በመሰናዶ ተማሪዎች ላይ የአመለካከት ለውጥ አምጥቶ ይሆን?" የሚል እንደሆነ ይታወሳል፡፡

የጥናቱ ርዕስ ራሱ እንደሚጠቁመን የተማሪዎቹ አመለካከት የሚለካው በሁለት መንገድ ነው፡፡ ይኸውም ይህ የአመለካከት ለውጥ መኖር/አለመኖር ለቋንቋው አፌፈት/ ኢአፌፈት በሆኑት መካከል ተመሳሳይነት ይኖረው ይሆን ወይስ ልዩነት ያሳያል? የሚለው ነጥብ መፈተሽ አለበት፡፡ አንዱ ወገን በመቅረቱ ሲያዝን ሌላው ወገን የሚደሰት ይሆናል ወይም ሁለቱም በመቅረቱ አዛኝ ወይም ተደሳች? የሚለው ነጥብ ተለይቶ መታወቅ አለበት፡፡

ቀደም ሲል በ4.3.1. ሥር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ያመጣውን ለውጥ ለመመርመር የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ተመልክተናል፤ ውጤቱንም አይተናል፡፡ የአመለካከት ለውጥ እንዳለ፣ ለቋንቋው ይሰጡ የነበሩትን ግምት እንደቀነሰባቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ ቋንቋው በተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ ቢካተት በመማር ማስተማር ላይ አዎንታዊ ለውጥ ሊያስከትል እንደሚችል ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ ያስረዳናል፡፡ እነዚህ 4.3.1 ሥር የተጠየቁት ጥያቄዎች ለሁለቱም ዓይነት ተማሪዎች ጥቅል ናቸው፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ጥቅል ጥያቄዎች በተጨማሪ ስለመግቢያ ፈተናው የሁለቱንም ወገን አቋም በግልጽ ለማወቅ 4.3.2 ለአማርኛ ቋንቋ አፌፈትና ኢአፌፈት መሆን በሚለው ተላውጦ ሥር አራት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄ 5.1 በአፌፈቶች ብቻ የሚመለስ ሲሆን፣ ጥያቄ 5.3 ደግሞ በኢአፌፈቶች ብቻ ይመለሳል፡፡ የተቀሩት ጥያቄ 5.2 እና 5.4 ግን በሁለቱም የሚመለሱ ናቸው፡፡

### 5.1. አማርኛ አፌን የፈታሁበት ቋንቋ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ቢሰጥ ደስ ይለኛል፡፡

ዐረፍተነገሩ አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ በአፌፈቶች ብቻ የሚሞላ ጥያቄ ነው፡፡ የተመዘገበውን ውጤት ስንመለከት 37.7% በጣም እስማማለሁ ሲሉ፣ 16.6% ደግሞ ፍጹም

አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥቷል። በጥቅሉ ሃሣቡን የተቃወሙት 27.7% ሲሆን፣ ድጋፋቸውን የገለጹት ደግሞ 58.8% ናቸው። መወሰን ያልቻሉት 13.6% ይሆናሉ። አማካይ ነጥቡ 3.5 ነው። ይህ ውጤት የሚያሳየን አብዛኞዎቹ ቋንቋው ለተቋም መግቢያ ፈተናነት መሰጠቱን እንደሚፈልጉት ነው። ለበለጠ ግንዛቤ ሠንጠረዥ አሥራ አንድን ይመልከቱ።

ሠንጠረዥ አሥራ አንድ፡- የአፈፊቶች ለ5.1 ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚያመለክት ነው።

| ፆታ | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍጹም አልስማማም | % | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 42 | 21.1 | 27 | 13.6 | 14 | 7.1 | 14 | 7.1 | 23 | 11.6 | 120 | 60.3 |
| ሴት | 33 | 16.6 | 15 | 7.5 | 13 | 6.5 | 8 | 4.0 | 10 | 5.0 | 79 | 39.7 |
| ድምር | 75 | 37.7 | 42 | 21.1 | 27 | 13.6 | 22 | 11.1 | 33 | 16.6 | 199 | 100 |

አማካይ ነጥብ 3.5

5.3. አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ አስደስቶኛል።

ጥያቄው አሉታዊ ዓረፍተ ነገር ሲሆን፣ በኢአፈፊቶች ብቻ የሚሞላ ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሻቸውን የሰጡ ወንድ 128 ሴት 66 በድምሩ 194 ተማሪዎች ናቸው። ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት በጣም እስማማለሁ 27(14%)፣ እስማማለሁ 28 (14.4%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 37(19%)፣ አልስማማም 33(17%)፣ ፍጹም አልስማማም 69(35.6%) የሚል ተመዝግቧል። በዚሁ መሠረት ፈተናው አለመሰጠቱን የደገፉት 28.4% ተማሪዎች ሲሆኑ፣ አለመሰጠቱን የተቃወሙት ደግሞ 52.6% ናቸው። መወሰን ያልቻሉት 19% ናቸው። ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛው ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት የሆኑ ተማሪዎችም ቢሆኑ፣ በተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲካተት ይፈልጋሉ። ስለዚህ በዚህ ነጥብ ላይ አፈፊት ሆኑ ኢአፈፊት የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወደከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ እንዲካተት ይፈልጋሉ።

በኢአፈፊት ምላሽ ላይ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት ሠንጠረዥ አስራ ሁለትን ይመልከቱ።

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡- ኢ.አፊ.ፊ.ቶች ለ5.3 ጥያቄ የሰጡትን ዝርዝር ምላሽ የሚያሳይ

| ፆታ | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍጹም አልስማማም | % | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 12 | 6.2 | 14 | 7.2 | 28 | 14.4 | 24 | 12.4 | 50 | 25.8 | 128 | 66 |
| ሴት | 15 | 7.7 | 14 | 7.2 | 9 | 4.6 | 9 | 4.6 | 19 | 10.0 | 66 | 34 |
| ድምር | 27 | 14.0 | 28 | 14.4 | 37 | 19.0 | 33 | 17.00 | 69 | 35.6 | 194 | 100 |

አማካይ ነጥብ 2.5

5.2. ከአማርኛ የበለጠ የምወደው ቋንቋ አለኝ።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተነገር ነው። ይህ ጥያቄ በይበልጥ የኢ.አፊ.ፊ.ት ተማሪዎችን ፍላጎት ለማጤን የሚረዳ ቢሆንም፣ አፊ.ፊ.ቶችንም ይመለከታል። ምክንያቱም እነ መድኅኒ (1986) እና ብርሃኑ (1976) የአዲስ አበባ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ይልቅ ለእንግሊዝኛ ፍቅር እንዳላቸው በጥናታቸው አረጋግጠውልን ነበርና ነው። ለዚህ ነው በሁለቱም ወገን ተማሪዎች እንዲሞላ የተፈለገው።

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሰጡት 194 እና 194 በድምሩ 388 ተማሪዎች ናቸው። የተገኘው ውጤት በጣም እስማማለሁ 34(17.5%) 47(24.2%) በድምሩ 81(20.9)፣ እስማማለሁ 35(18%) 41(21.1%) በድምሩ 75(19.6%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 49(25.3%) 36(18.6%) በድምሩ 85(22%)፣ አልስማማም 33(17%) 37(19.1%) በድምሩ 70(18%)፣ ፍጹም አልስማማም 43(22.2%) 33(17%) በድምሩ 76(19.6%) ነው። ሃሣቡን የደገፉት አፊ.ፊ.ቶች 35.5%፣ ኢ.አፊ.ፊ.ቶች 45.3% ሲሆኑ፣ የተቃወሙት ደግሞ አፊ.ፊ.ቶች 39.2%፣ ኢ.አፊ.ፊ.ቶች 36.1% ናቸው። ለመወሰን ያስቸግረኛል ያሉት አፊ.ፊ.ቶች 25.3%፣ ኢ.አፊ.ፊ.ቶች ደግሞ 18.6% ነው። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.1፣2.8፣3.0 ናቸው።

ውጤቱ ሲጠቃለል ቀጥሎ ያለውን ይመስላል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 34 | 47 | 81 | 34 | 47 | 81 | 17.5 | 24.2 | 20.9 |
| እስማማለሁ | 35 | 41 | 76 | 70 | 82 | 152 | 18 | 21.1 | 19.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 49 | 36 | 85 | 147 | 108 | 255 | 25.3 | 18.6 | 22 |
| አልስማማም | 33 | 37 | 70 | 132 | 148 | 280 | 17 | 19.1 | 18 |
| ፍጹም አልስማማም | 43 | 33 | 76 | 215 | 165 | 380 | 22.2 | 17 | 19.6 |
| ድምር | 194 | 194 | 388 | 598 | 550 | 1148 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ 3.1፣2.8፣3.0 ናቸው።

በቅድሚያ ለመወሰን ያስቸግረኛል ያሉትን በመቶኛ ብንመለከት፣ በተለይ የአፊፊቶች ቀላል ቁጥር አይደለም። ሐሳቡን የደገፉት አፊፊቶችም 35.5% ናቸው። ይህ የሚጠቁመን መድሃኔ (1986) እና ብርሃኑ (1976) ያሉትን ሃሣብ በከፊልም ቢሆን እንድንጋራ ያደርገናል። የአፊፊቶች አማካይ ነጥብ 3.1 በመሆኑና ሃሣቡን የተቃወሙት ቁጥር ከደገፉት ስለሚበልጥ የአብዛኛዎቹ ሃሳብ ባይሆንም ጥቂት የማይባሉ ግን እንግሊዘኛን አስበልጠው እንደሚወዱ እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ኢአፊፊት ተማሪዎችን ስንመለከት ደግሞ 45.3% የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከአማርኛ አስበልጠው የሚወዱ ቢሆኑም፣ 36.1% ግን ከአፍ መፍቻቸው አስበልጠው አማርኛን እንደሚወዱ አረጋግጠውልናል።

5.4. የአማርኛ ቋንቋን ከየትኞቹም ቋንቋዎች አስበልጬ እወዳለሁ።

ዐረፍተ ነገሩ አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ነው። ጥያቄው ከ"5.2" ጥያቄ ጋር ተቀራራቢነት አለው። በተለይ ለቋንቋው አፊፊት የሆኑ ተማሪዎች ለቋንቋው ምን ያህል ፍቅር እንዳላቸው ለመለካት ያስችላል የሚል እምነት አለ። ለኢአፊፊቶችም ቢሆን፣ ለ "5.2" ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ ጋር ለማገናዘብ አጋዥ መረጃ ይሰጣል።

የተመዘገበው ውጤት በሚከተለው መልክ ቀርቧል

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 33 | 27 | 60 | 165 | 135 | 300 | 16.9 | 14.1 | 15.5 |
| እስማማለሁ | 48 | 47 | 95 | 192 | 188 | 380 | 24.6 | 24.6 | 24.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 45 | 50 | 95 | 135 | 150 | 285 | 23.1 | 26.2 | 24.6 |
| አልስማማም | 40 | 36 | 76 | 80 | 72 | 152 | 20.5 | 18.9 | 19.7 |
| ፍጹም አልስማማም | 29 | 31 | 60 | 29 | 31 | 60 | 14.9 | 16.2 | 15.5 |
| ድምር | 195 | 191 | 386 | 601 | 576 | 1177 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች 3.1፣ 3.0፣ 3.0 ናቸው።

ለአፊፊት ተማሪዎች ከተመዘገበው ውጤት ብንጀምር በ«5.4» ላይ የተመዘገበው አማካይ ነጥብ 3.1 ነው። ለዚህ ጥያቄ አማካይ ነጥብ እና በ«5.2» ላይ የተመዘገበው አማካይ ነጥብ እና በ«5.2» ላይ የተመዘገበው እስማማለሁ ብለው መልስ የሰጡት 24.6% ሲሆኑ፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል ያሉት ደግሞ 23.1% ናቸው። ይህ የሚያስገነዝበን የቋንቋው ለተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ተደማምሮ ልባቸው ወደ እንግሊዝኛው እየሸፈተ እንደሚገኝ ያሳያል። ኢአፊፊቶች ዘንድ ከፍተኛው አሃዝ 24.6% የተመዘገበው ለመወሰን ያስቸግረኛል በሚለው ሲሆን፣ አማካይ ነጥቡም 3.0 ነው። ከዚህ ማጠቃለል የምንችለው ኢአፊፊት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ከአፍ መፍቻቸው ቋንቋ እኩል እንደሚወዱት የዚህ ጥናት ውጤት ያሳየናል። አበበ (1990)

አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን አይወዱም ብለው ካጠቃለሉት ሃሣብ ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ይቃረናል ማለት ነው።

### 4.2.3. የተማሪው ግላዊ አመለካከት

Celce-Murcia (1991) ተማሪው ለታላሚው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለው አመለካከት በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ይገልፃሉ። ይህ ማለት ተማሪው ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት ካለው ቋንቋውን ለመማር ፍላጐት ያሳያል፣ ንሺ ይኖረዋል፤ ፍላጎቱና ንሺው ካለ ደግሞ ውጤታማ መሆን ይችላል። ተማሪው በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ካለው ትምህርቱን እንደማይጠላው ታሪኩ (1988) እንዲሁም Neale et al (1970) ያስረዱናል። ከዚህም በተጨማሪ ለቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ በጎ አመለካከት ይኖረዋል። ባንፃሩ ግን አሉታዊ አመለካከት ካለው የዚህ ተቃራኒ ሁኔታ ይከሰታል ማለት ነው። Spolsky (1969) Gardner (1968) ፣ Littlewood (1992) ይህንኑ ሃሣብ ይጋራሉ።

ከእነዚህ እውነታዎች በመነሳት ለቋንቋው አፈፊት የሆኑትም ሆኑ ኢአፈፊት ተማሪዎች ያላቸውን ግላዊ አመለካከት መፈተሹ ጠቃሚ ይሆናል። ምክንያቱም ተማሪዎቹ የቋንቋው በተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተት ያሳደረባቸው ስሜት ለመግለጽ መሠረት የሚያደርጉአቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። ከነዚያ ውስጥ ቋንቋው ባለመካተቱ የሚያጡት ጥቅም ወይም በመካተቱ የሚያስገኝላቸው ጥቅም አንዱ ሊሆን ይችላል። የሚያጡት ጥቅም ወይም በመካተቱ የሚያስገኝላቸው ጥቅም አንዱ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በቋንቋውና በቋንቋው ተናጋሪ ላይ ያላቸው ግላዊ አመለካከት ለአቋማቸው የመነሻ ሃሣብ ሊሆን ይችላል። ለዚህም ነው ስለተማሪዎች ግላዊ አመለካከት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጥያቄዎች በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱት።

በዚህ ግላዊ አመለካከት ሥር አራት አዎንታዊና አራት አሉታዊ የሆኑ በድምሩ ስምንት ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ ቀርበላቸዋል። በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተመዘገበውን ውጤት ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታለን።

#### 2.1. የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪን ስለምጠላ የአማርኛን ትምህርት አልወድም።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ 199 አፈፊት እና 198 ኢአፈፊት በድምሩ 397 ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተውበታል። የተመዘገበውም ውጤት በጣም እስማማለሁ 7(3.5%) 4(2%) በድምሩ 11(2.8%)፣ እስማማለሁ 0(0%) 17(8.6%) በድምሩ 17(4.3%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 4(2%) 10(5.1%) በድምሩ 14(3.%)፣ አልስማማም 22(11.1%) 18(9.1%) በድምሩ 40(10.1%)፣ ፍጹም አልስማማም 166(83.4%) 149(75.2%) በድምሩ 315(79.1%) ሲሆን፣ አማካይ ነጥቦቹ 4.7፣ 4.5፣ 4.6 ናቸው።

ውጤቱ በሠንጠረዥ መልክ ሲቀመጥ

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 7 | 4 | 11 | 7 | 4 | 11 | 3.5 | 2 | 2.8 |
| እስማማለሁ | 0 | 17 | 17 | 0 | 34 | 34 | 0 | 8.6 | 4.3 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 4 | 10 | 14 | 12 | 30 | 42 | 2 | 5.1 | 3 |
| አልስማማም | 22 | 18 | 40 | 88 | 72 | 160 | 11.1 | 9.1 | 10.1 |
| ፍጹም አልስማማም | 166 | 149 | 315 | 830 | 745 | 1575 | 83.4 | 75.2 | 79.1 |
| ድምር | 199 | 198 | 397 | 937 | 885 | 1822 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች 4.7፣ 4.5፣ 4.6 ናቸው፡፡

በዚህ ውጤት መሠረት ሃሣቡን የደገፉት አፊ.ፊ.ቶች 3.5% ሲሆኑ ኢ.አፊ.ፊ.ቶች ደግሞ 10.6% ናቸው፡፡ ሃሣቡን የተቃወሙት ደግሞ አፊ.ፊ.ቶች 94.5% ሲሆኑ፣ ኢ.አፊ.ፊ.ቶችም 84.3% ናቸው፡፡ ከዚህ ስሌት እንደምንረዳው በታሪኩ (1988) ጥናት ውስጥ እንደታየው እጅግ በጣም ጥቂት ተማሪዎች ካልሆኑ በቀር የሁለቱም ወገን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪውንም ሆነ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን አይጠሉም፡፡ እዚህም ላይ አበበ (1990) በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ግድ ሆኖባቸው እንጂ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማር አይፈልጉም በሚል ያሰፈሩት ማጠቃለያ ጥርጣሬ እንደሚያስከትል መገንዘብ እንችላለን፡፡

2.2. ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ ለአማርኛም ሆነ ለሌሎች ቋንቋዎች ጥሩ አመለካከት አለኝ፡፡

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ 199 እና 199 በድምሩ የ398 ተማሪዎች ውጤት ተመዝግቧል፡፡ የውጤቱንም ዝርዝር ብንመለከት፡- በጣም እስማማለሁ 137(68.9%) 142(71.4%) በድምሩ 279(70%)፣ እስማማለሁ 54(27.1%) 31(15.6%) በድምሩ 85(21.4%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 3(1.5%) 10(5%) በድምሩ 13(3.3%)፣ አልስማማም 3(1.5%) 11(5.5%) በድምሩ 14(3.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 2(1%) 5(2.5%) በድምሩ 7(1.8%) ሆኖ እናገኛለን፡፡ አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.6፣4.5፣4.5 ናቸው፡፡ በሃሳቡ የተስማሙት 96% አፊ.ፊ.ት እና 87% ኢ.አፊ.ፊ.ት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሃሳቡን የተቃወሙት 2.5% አፊ.ፊ.ትና 8% ኢ.አፊ.ፊ.ት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያ እንደሆነ ግንዛቤ አላቸው፤ ለማንኛውም ቋንቋ ጥሩ አመለካከት አላቸው፡፡

ለበለጠ ግንዛቤ ሠንጠረገፑን ይመልከቱ፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 137 | 142 | 279 | 685 | 710 | 1395 | 68.9 | 71.4 | 70 |
| እስማማለሁ | 54 | 31 | 85 | 216 | 124 | 340 | 27.1 | 15.6 | 21.4 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 3 | 10 | 13 | 9 | 30 | 39 | 1.5 | 5 | 3.3 |
| አልስማማም | 3 | 11 | 14 | 6 | 22 | 28 | 1.5 | 5.5 | 3.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 2 | 5 | 7 | 2 | 5 | 7 | 1 | 2.5 | 1.8 |
| ድምር | 199 | 199 | 398 | 918 | 891 | 1809 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ፡- 4.6፣4.5፣4.5

## 2.3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚከብደኝ አልወደውም፡፡

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ለጥያቄው ምላሻቸውን የሰጡት ተማሪዎች 195 እና 192 በድምሩ 387 ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተገኘው ውጤት፣ በጣም እስማማለሁ 8(4.2%) 17(8.9%) በድምሩ 25(6.5%)፣ እስማማለሁ 9(4.6%) 13(6.8%) በድምሩ 22(5.7%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 18(9.2%) 16(8.3%) በድምሩ 34(8.8%)፣ አልስማማም 87(44.6%) 49(25.5%) በድምሩ 136(35.1%)፣ ፍጹም አልስማማም 73(37.4%) 97(50.5%) በድምሩ 170(43.9%) ይሆናል፡፡ አማካይ ነጥቦቹ 4.1፣4.0%፣4.0% ናቸው፡፡

ከሠንጠረገፉ ዝርዝር ሀሳቦችን ማግኘት ይቻላል፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 8 | 17 | 25 | 8 | 17 | 25 | 4.2 | 8.9 | 6.5 |
| እስማማለሁ | 9 | 13 | 22 | 18 | 26 | 44 | 4.6 | 6.8 | 5.7 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 18 | 16 | 34 | 54 | 48 | 102 | 9.2 | 8.3 | 8.8 |
| አልስማማም | 87 | 49 | 136 | 348 | 196 | 544 | 44.6 | 25.5 | 35.1 |
| ፍጹም አልስማማም | 73 | 97 | 170 | 365 | 485 | 850 | 37.4 | 50.5 | 43.9 |
| ድምር | 195 | 192 | 387 | 793 | 772 | 1565 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች፡- 4.1፣4.0፣4.0

ይህንን አሉታዊ ሃሣብ የደገፉት አፈ.ፊቶች 8.8% ሲሆኑ፣ ኢ.አፈ.ፊቶች ደግሞ 15.7% ናቸው፡፡ ሃሳቡን የተቃወሙት ደግሞ አፈ.ፊቶች 82%፣ ኢ.አፈ.ፊቶች ደግሞ 76% ናቸው፡፡ በዚህ ውጤት መሠረት ለአብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች አፈ.ፊትም ሆኑ ኢ.አፈ.ፊት

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደማይከብዳቸውና ቋንቋውንም እንደሚወዱት መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.4. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የወደፊት ምርጫዬ ባለመሆኑ በትኩረት አልከታተልም፡፡

ዐረፍተ ነገሩ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ለጥያቄው ምላሻቸው የሰጡት 196 እና 199 በድምሩ 395 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ዝርዝር ውጤቱ በጣም እስማማለሁ 33(16.8%) 25(12.6%) በድምሩ 58(14.7%)፣ እስማማለሁ 42(21.4%) 22(11.1%) በድምሩ 64(16.2%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 35(17.9%) 40(20%) በድምሩ 75(19%)፣ አልስማማም 56(28.6%) 49(24.6%) በድምሩ 105(26.6%)፣ ፍጹም አልስማማም 30(15.3%) 63(31.7%) በድምሩ 93(23.5%) ሆኖ ስናገኝ አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.0፣3.5፣3.3 ናቸው፡፡

ውጤቱን በይበልጥ ለመረዳት ሠንጠረዡን ይመልከቱ፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 33 | 25 | 58 | 33 | 25 | 58 | 16.8 | 12.6 | 14.7 |
| እስማማለሁ | 42 | 22 | 64 | 84 | 44 | 128 | 21.4 | 11.1 | 16.2 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 35 | 40 | 75 | 105 | 120 | 225 | 17.9 | 20 | 19 |
| አልስማማም | 56 | 49 | 105 | 224 | 196 | 420 | 28.6 | 24.6 | 26.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 30 | 63 | 93 | 150 | 315 | 465 | 15.3 | 31.7 | 23.5 |
| ድምር | 196 | 199 | 395 | 596 | 700 | 1296 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.0፣3.5፣3.3 ናቸው

አፈፊት ተማሪዎች እንደ «5.2» እና «5.4» መሃል ቤት ናቸው፡፡ 38.2% አሉታዊ ዐረፍተነገሩን ሲደግፉ፣ 43.3% ደግሞ ተቃውመውታል፡፡ አማካይ ነጥቡም 3.0 ላይ ነው፡፡ ግማሹ ተማሪ የአማርኛ ቋንቋ የወደፊት ምርጫው ሊያደርገው እንደሚችል፣ ግማሾቹ ደግሞ ለወደፊት እንደማይመርጡት ውጤቱ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ግማሹ ተማሪ ትምህርቱን በወጉ ሲከታተሉ ሌሎቹ የአዲስ አበባ አፈፊት ተማሪዎች ግን ትምህርቱን በትኩረት አይከታተሉም፡፡ ኢአፈፊቶቹን ስንመለከት ደግሞ ሃሳቡን የደገፉት 23.7% ናቸው፡፡ ሃሳቡን የተቃወሙት ደግሞ 56.3% ናቸው፡፡ አማካይ ነጥቡ 3.5 ነው፡፡ ይህ የሚያሳያን ደግሞ አብዛኛ ዎቹ ኢአፈፊት የመሰናዶ ተማሪዎች በከፍተኛ ተቋማት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ሊመርጡ እንደሚችሉ፣ ቋንቋው የወደፊት ምርጫቸው ሊሆን ስለሚችል ትምህርቱን በትኩረት እንደሚከታተሉ እንገነዘባለን፡፡ ይህ ሃሳብ ደግሞ ዳንኤል መኮንን (1992) አብዛኛዎቹ በሀዲይኛ

አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በከፍተኛ ተቋማት አማርኛን መርጠው ለመከታተል ፍላጎት እንዳላቸው ከጠቀስው ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩን አንዳንድ ጊዜ ከአፈፌት የበለጠ ኢአፈፌቶች በቋንቋው ለመሰልጠን ፍላጎቱን እንዳላቸው ነው።

### 2.5. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሙሉ ልብ እከታተላለሁ።

አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ 197 እና 198 በድምሩ የ395 ተማሪዎች ምላሽ ተመዝግቦለታል። ዝርዝር ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል። በጣም እስማማለሁ 51(25.9%) 77(38.9%) በድምሩ 128(32.4%)፣ እስማማለሁ 74 (37.6%) 72(36.3%) በድምሩ 146(37%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 31(15.7%) 19(9.6%) በድምሩ 50(12.7%)፣ አልስማማም 29(14.7%) 13(6.6%) በድምሩ 42(10.6%)፣ ፍጹም አልስማማም 12(6.1%) 17(8.6%) በድምሩ 29(7.3%) ናቸው። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.6፣ 3.9፣ 3.8 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 51 | 77 | 128 | 255 | 385 | 640 | 25.9 | 38.9 | 32.4 |
| እስማማለሁ | 74 | 72 | 146 | 296 | 288 | 584 | 37.6 | 36.3 | 37 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 31 | 19 | 50 | 93 | 57 | 150 | 15.7 | 9.6 | 12.7 |
| አልስማማም | 29 | 13 | 42 | 58 | 26 | 84 | 14.7 | 6.6 | 10.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 12 | 17 | 29 | 12 | 17 | 29 | 6.1 | 8.6 | 7.3 |
| ድምር | 197 | 198 | 395 | 714 | 773 | 1487 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ:- 3.6፣3.9፣3.8 ናቸው።

በዚህ ውጤት መሠረት ሃሳቡን የደገፉት 63.5% እና 75.2% ሲሆኑ የተቃወሙት ደግሞ 20.8% እና 15.2% ናቸው። በሁለቱም ወገን ያሉት ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ትምህርቱን በሙሉ ልብ የሚከታተሉ ቢሆኑም፣ በተለይ በሌሎች ነጥቦች ሥር እንደተመለከትነውና በምልከታ እንደተረጋገጠው፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ተዕዕኖ ትምህርቱን በሙሉ ልብ የማይከታተሉ ተማሪዎች እንዳሉ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

### 2.6. አማርኛ ጨቋኝ ቋንቋ በመሆኑ በእርሱ ላይ ጥሩ አመለካከት የለኝም።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተነገር ነው። 199 እና 192 በድምሩ 391 ምላሽ ተመዝግቦለታል። ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል። በጣም እስማማለሁ 7(3.5%) 18(9.4%) በድምሩ 25(6.4%)፣ እስማማለሁ 4(2%) 14(7.3%) በድምሩ 18(4.6%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 9(4.5%) 15(7.8%) በድምሩ 24(6.1%)፣ አልስማማም 31(15.6%)

26(13.5%) በድምሩ 57(14.6)፣ ፍጹም አልስማማም 148(74.4%) 119(62%) በድምሩ 267(68.3%):: አማካይ ነጥቦቹን ስንመለከት 4.6፣4.1፣4.3 ሆነው እናገኛለን::

ለዝርዝሩ ሠንጠረዡን ይመልከቱ:::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 7 | 18 | 25 | 7 | 18 | 25 | 3.5 | 9.4 | 6.4 |
| እስማማለሁ | 4 | 14 | 18 | 8 | 28 | 36 | 2 | 7.3 | 4.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 9 | 15 | 24 | 27 | 45 | 72 | 4.5 | 7.8 | 6.1 |
| አልስማማም | 31 | 26 | 57 | 124 | 104 | 228 | 15.6 | 13.5 | 14.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 148 | 119 | 267 | 740 | 595 | 1335 | 74.4 | 62 | 68.3 |
| ድምር | 199 | 192 | 391 | 906 | 790 | 1696 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች፡- 4.6፣4.1፣4.3

በናሙናነት ከተወሰዱ ተማሪዎች መካከል 11% ሃሳቡን ሲደግፉት 6.1% ደግሞ ለመወሰን ተቸግረዋል:: በዚህ በመሰናዶ ደረጃ ያሉት ተማሪዎች ከሞላ ጎደል ስለቋንቋ ምንነት፣ አጀማመር፣ ባህሪያት ወዘተ ከመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የተማሩና እየተማሩ ያሉት በመሆኑ፣ ታች ካሉት ክፍሎች የተሻለ ግንዛቤ ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለ:: ዳሩ ግን ከተመዘገበው ውጤት ማየት እንደሚቻለው አሁንም ቢሆን ባለማወቅ ይሁን በፖለቲካ አመለካከት ተፅዕኖ፣ አንዱን ቋንቋ ጨቋኝ ሌላውን ተጨቋኝ አድርገው የሚገምቱ ክፍሎች እንዳሉ እንረዳለን:: በእርግጥ አብዛኛዎቹ 82.9% ተማሪዎቹ ሃሳቡን ይቃወሙታል:: ይህ ማለት ደግሞ ሥለቋንቋና ቋንቋ ባህሪያት ግንዛቤ ሳይኖራቸው እንደማይቀር የሚጠቁም ነው::

## 2.7. ለቋንቋዎች እኩል አክብሮት አለኝ::

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተነገር ሲሆን፣ 192 እና 194 በድምሩ 386 ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተውበታል:: ውጤቱን ስናይ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 134(69.8%) 124(63.9%) በድምሩ 258(66.8%)፣ እስማማለሁ 31(16.2%) 41(21.1%) በድምሩ 72(18.7%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 11(5.7%) 9(4.6%) በድምሩ 20(5.2%)፣ አልስማማም 11(5.7%) 9(4.6%) በድምሩ 20(5.2%)፣ ፍጹም አልስማማም 5(2.6%) 10(5.2%) በድምሩ 15(3.9%) ናቸው:: አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.5፣4.3፣4.4 ናቸው::

ለተጨማሪ መረጃ ሠንጠረዡን ይመልከቱ።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 134 | 124 | 258 | 670 | 620 | 1290 | 9.8 | 63.9 | 66.8 |
| እስማማለሁ | 31 | 41 | 72 | 124 | 164 | 288 | 16.2 | 21.1 | 18.7 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 11 | 10 | 21 | 33 | 30 | 63 | 5.7 | 4.6 | 5.2 |
| አልስማማም | 11 | 9 | 20 | 22 | 18 | 40 | 5.7 | 4.6 | 5.2 |
| ፍጹም አልስማማም | 5 | 10 | 15 | 5 | 10 | 15 | 2.6 | 5.2 | 3.9 |
| ድምር | 192 | 194 | 386 | 854 | 842 | 1696 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.5፣ 4.3፣ 4.4 ናቸው።

ከተመዘገበው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው 85.5% የመስናዶ ተማሪዎች ለቋንቋዎች እኩል አክብሮት አላቸው። ነገር ግን "2.6" ላይ እንዳነሳነው የግንዛቤ ችግር ይሁን የፖለቲካ ሁኔታ ባይታወቅም በቋንቋዎች እኩልነትት የማያምኑ 9.1% ተማሪዎች አሉ። በ«2.6» ሥር አንዱን ቋንቋ ጨቋኝ ሌላውን ተጨቋኝ አድርገው የሚመለከቱ ክፍሎች እንዳሉ ተመልክተናል። ይህ አተያያቸው በ«2.7» ስር በቋንቋዎች እኩልነት እንዳያምኑ ያደረጋቸው ይመስላል። አንዱን ቋንቋ ከፍ ሌላውን ቋንቋ ዝቅ ወይም ናቅ አድርጐ የመመልከት ዝንባሌ ይንፀባረቃል። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል በትዕዛዝ «ሠ» (አባሪ «ሀ»ን ይመልከቱ) አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው የሆኑት የህብረተሰቡ ክፍሎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከፍ፣ አማርኛን ዝቅ አድርገው መመልከታቸው ለአሉታዊ አተያይ በር የከፈተው።

## 2.8. የአማርኛ ስነጽሑፎችን ማንበብ፣ ጭውውቶችን ድራማዎችን መከታተል በጣም ያስደስተኛል።

አዎንታዊ ዐረፍተነገር ነው። የ199 እና 200 በድምሩ የ399 መላሾች ውጤት ተመዝግቧል። ዝርዝሩን ስንመለከት ደግሞ በጣም እስማማለሁ 139(69.9%) 145(72.5%) በድምሩ 284(71.2%)፣ እስማማለሁ 50(25.1%) 39(19.5%) በድምሩ 89(22.3%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 5(2.5%) 8(4%) በድምሩ 13(3.3%)፣ አልስማማም 1(0.5%) 5(2.5%) በድምሩ 6(1.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 4(2%) 3(1.5%) በድምሩ 7(1.7%) ይሆናል። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.6፣ 4.6፣ 4.6 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 139 | 145 | 284 | 695 | 725 | 1420 | 69.9 | 72.5 | 71.2 |
| እስማማለሁ | 50 | 39 | 89 | 200 | 156 | 356 | 25.1 | 19.5 | 22.3 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 5 | 8 | 13 | 15 | 24 | 39 | 2.5 | 4 | 3.3 |
| አልስማማም | 1 | 5 | 6 | 2 | 10 | 12 | 0.5 | 2.5 | 1.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 4 | 3 | 7 | 4 | 3 | 7 | 2 | 1.5 | 1.7 |
| ድምር | 199 | 200 | 399 | 916 | 918 | 1834 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ:- 4.6፣ 4.6፣ 4.6 ናቸው።

በዚህ ስሌት መሠረት 93.5% ተማሪዎች ሃሳቡን ሲደግፉ፣ 3.2% ብቻ ተቃውመውታል። ስነ ጽሁፍ ቋንቋን ለማስተማር የሚጫወተው ሚና እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል ነጥብ ነው። ስነጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በተማሪዎች ዘንድ ለምን እንደሚወደድ Colle and Slater (1987:2) እንዲህ በማለት ይገልፃሉ።

> *«ስነጽሁፍ ነገሮችን አስውቦና አድምቆ ስለሚያቀርብ ለአእምሮ የሚደመጠውን ያህል ለልቦናም ይሰማል። ከተማሪው የህይወት ልምድ ጋር ቁርኝት የሚፈጥሩ ስራዎችን ያቀርባል። ስለዚህ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡትን ልዩ ልዩ የትምህርት ልምዶች ተማሪዎች ከህይወታቸው ጋር እንዲያዛምዷቸው ያደርጋል።»*

ዶክተር ፍቃደ (1982) በበኩላቸው የስነጽሁፍ ሚና ሁለንተናዊ የገጠመኝ እውቀቶቹን በማስተላለፍ ብቻ እንዳልተወሰነና ለቋንቋ ትምህርት መዳበር ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይጠቅሳሉ። ስለዚህ የተማሪው ለቋንቋው ያሳየው ፍቅር የመነጨው በዚህ ስነጽሁፍ በቋንቋ ማስተማር ውስጥ ከሚጫወተው ሚና ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ አንዳንድ ተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ትምህርቱን ለመከታተል ቸል እንዲሉ ያደረጋቸው የቋንቋው ጥላቻ አይደለም ማለት ነው። የቋንቋውን ትምህርት የሚኳለው ነገር አለ ማለት ነው። ከነዚያ ምክንያቶች መካከል አንዱ ደግሞ ትምህርቱን ተምረው ለተቋም የመግቢያ ፈተና አለመስጠቱ ሊሆን ይችላል። አበበ ሽፈራው (1990) በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ የተፃፉ ጽሑፎችን እንደሚጠሉ፣ የአማርኛን ፕሮግራም በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን መከታተል እንደማይፈልጉ የገለጹት በዚህ ጥናት ውጤት መሠረት ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል ያዳግታል።

### 4.2.4. የአማርኛ ቋንቋን መማር ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንፃር

Hurlock (1996) ለአንድ የትምህርት አይነት ያለንን አመለካከት ከሚወስኑት ነገሮች አንዱ የትምህርቱ አስፈላጊነት ወይም አገልግሎታዊ ጠቀሜታው ነው ይሉናል:: ስለዚህ ተማሪው በመሰናዶ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን መማሩ የሚያስገኝለት ጠቀሜታ አለ ወይስ የለም? እነዚህን ሃሳቦች ለመዳሰስ የሚያስችሉ አራት አዎንታዊ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበላቸዋል:: በመቀጠል ለነዚሁ አራት ጥያቄዎች የተመዘገቡትን ምላሾች አንድ ባንድ እንመለከታለን::

#### 3.1. በአማርኛ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛ፣ ደራሲ. . . መሆን እፈልጋለሁ::

አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው:: ለዚህ ጥያቄ 199 እና 199 በድምሩ 398 ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተውበታል:: የተመዘገበውን ውጤት በዝርዝር ስንመለከት፣ በጣም እስማማለሁ 30(15%) 65(32.7%) በድምሩ 95(24%)፣ እስማማለሁ 23(11.6%) 42(21.1%) በድምሩ 65(16.3%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 65(32.7%) 43(21.6%) በድምሩ 108(27.1%)፣ አልስማማም 43(21.6%) 32(16.1%) በድምሩ 75(18.8%)፣ ፍጹም አልስማማም 38(19.1%) 17(8.5%) በድምሩ 55(13.8%) ሲ.መለስ:: አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 2.8፣3.5፣3.2 ናቸው::

የተመዘገበውን ውጤት በጥልቀት ለማየት ሠንጠረዡን መመልከቱ ይመረጣል::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 30 | 65 | 95 | 150 | 325 | 475 | 15 | 32.7 | 24 |
| እስማማለሁ | 23 | 42 | 65 | 92 | 168 | 260 | 11.6 | 21.1 | 16.3 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 65 | 43 | 108 | 195 | 129 | 324 | 32.7 | 21.6 | 27.1 |
| አልስማማም | 43 | 32 | 75 | 86 | 64 | 150 | 21.6 | 16.1 | 18.8 |
| ፍጹም አልስማማም | 38 | 17 | 55 | 38 | 70 | 55 | 19.1 | 8.5 | 13.8 |
| ድምር | 199 | 199 | 398 | 561 | 703 | 1264 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች 2.8፣3.5፣3.2 ይሆናሉ::

በአፈፃቶች በኩል ከፍተኛውን መቶኛ የያዘው "በአማርኛ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛ፣ ደራሲ . . . መሆን መፈለግን" የሚቃወሙት ናቸው:: በ2.4 "የአማርኛ ቋንቋ የወደፊት ምርጫዬ ባለመሆኑ ትምህርቱን በደንብ አልከታተልም" ለሚለው የአፈፃቶች ምላሽ መሳ ለመሳ ነበር:: በመሰናዶ ደረጃ እያሉ የወደፊት ራዕያቸውን መጠቆም ያልቻሉት 32.7% ቀላል ቁጥር አይደለም:: እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ተደማምረው ሲጤኑ የአዲስ አበባ የመሰናዶ

ተማሪዎች ለወደፊቱ ጋዜጠኛ፣ ደራሲ ወዘተ የመሆን ፍላጎታቸው አነስተኛ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ኢአፈፈቶችን የተመለከትን እንደሆነ ውጤታቸው ከአፈፈቶች ይለያል፡፡ 53.8% ሃሳቡን ሲደግፉ 24.6% ናቸው የተቃወሙት፡፡ ቀደም ሲል በ"2.4" ሥር እንደተመለከትነው ቋንቋውን እንደሚወዱት፣ በቋንቋው መስልጠን እንደሚፈልጉ እንዳረጋገጡልን ሁሉ አሁንም በአማርኛ ትምህርት ገፍተው ጋዜጠኛ፣ ደራሲ መሆን እንደሚፈልጉ ውጤቱ ያሳያል፡፡ ምናልባት ለዚህ እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ ለምሳሌ እነዚህ ተማሪዎች ከመጀመሪያው ከአፍ መፍቻ ይልቅ አማርኛን መርጠው ሲገቡ ይህን አላማ ይዘው ገብተው ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል አፈፈቶች አማርኛ ን እናውቀዋለን የሚል እምነት ስላላቸው በማያውቁት በሌላ ቋንቋ ወይም ሙያ መሰልጠን ስለሚፈልጉም ሊሆን ይችላል፡፡

## 3.2. የአማርኛ ቋንቋ በመማሬ ስለቋንቋና የቋንቋ ባህሪያት እንዲሁም ስለስነጽሑፍ ጥሩ ግንዛቤ ለመጨበጥ ችያለሁ፡፡

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ለጥያቄው ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች 199 እና 197 በድምሩ 396 ናቸው፡፡ ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በጣም እስማማለሁ 64(32.2%) 72(36.5%) በድምሩ 136(34.3%)፣ እስማማለሁ 95(47.7%) 79(40.1%) በድምሩ 174(44%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 26(13.1%) 30(15.2%) በድምሩ 56(14.1%)፣ አልስማማም 9(4.5%) 9(4.6%) በድምሩ 18(4.6%)፣ ፍጹም አልስማማም 5(2.5%) 7(3.6%) በድምሩ 12(3%) ሲመስል፣ አማካይ ነጥቦቹ 4.0፣4.0፣4.0 ናቸው፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ሊ | ድ | አ | ሊ | ድ | አ | ሊ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 64 | 72 | 136 | 320 | 360 | 650 | 32.2 | 36.5 | 34.3 |
| እስማማለሁ | 95 | 79 | 174 | 380 | 316 | 696 | 47.7 | 40.1 | 44 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 26 | 30 | 56 | 78 | 90 | 168 | 13.1 | 15.2 | 14.1 |
| አልስማማም | 9 | 9 | 18 | 18 | 18 | 36 | 4.5 | 4.6 | 4.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 5 | 7 | 12 | 5 | 7 | 12 | 2.5 | 3.6 | 3 |
| ድምር | 199 | 197 | 396 | 801 | 791 | 15 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ፡- 4.0፣4.0፣4.0

ከዚህ ውጤት ማየት እንደሚቻለው 78.3% ተማሪዎች ሃሳቡን ሲደግፉት 7.6% ብቻ ተቃውመውታል፡፡ በዚህ አሃዝ መሠረት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አፈፈቶችም ሆነ ኢአፈፈቶቹ

የአማርኛ ቋንቋ በመማራቸው ስለቋንቋና የቋንቋ ባህሪያት እንዲሁም ስነጽሑፍ ጥሩ ግንዛቤ አግኝተዋል።

### 3.4. በመሰናዶ ደረጃ የሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መሠረት በመሆናቸው ወድጀአቸዋለሁ።

አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። 196 እና 195 በድምሩ 391 ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተውበታል። የውጤቱን ዝርዝር ስንመለከት ደግሞ፣ በጣም እስማማለሁ 43(21.9%) 68(34.9%) በድምሩ 111(28.4%)፣ እስማማለሁ 76(38.8%) 79(40.5%) በድምሩ 155(39.6%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 44(22.5%) 28(14.4%) በድምሩ 72(18.4%)፣ አልስማማም 23(11.7%) 12(6.1%) በድምሩ 35(9%)፣ ፍጹም አልስማማም 10(5.1%) 8(4.1%) በድምሩ 18(4.6%) ሆኖ እናገኛለን። አማካይ ነጥቦቹ 3.6፣4.0፣3.8 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሴ | ወ | ድ | ሴ | ወ | ድ | ሴ | ወ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 43 | 68 | 111 | 215 | 340 | 555 | 21.9 | 34.9 | 28.4 |
| እስማማለሁ | 76 | 79 | 155 | 304 | 316 | 620 | 38.8 | 40.5 | 39.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 44 | 28 | 72 | 132 | 84 | 216 | 22.5 | 14.4 | 18.4 |
| አልስማማም | 23 | 12 | 35 | 46 | 24 | 7 | 11.7 | 6.1 | 9 |
| ፍጹም አልስማማም | 10 | 8 | 18 | 10 | 8 | 18 | 5.1 | 4.1 | 4.6 |
| ድምር | 196 | 195 | 319 | 707 | 772 | 1479 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦች ደግሞ 3.6፣4.0፣3.8 ናቸው።

በውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው ሃሳቡን የደገፉት 68% ሲሆኑ፣ የተቃወሙት ደግሞ 13.6% ናቸው። አንዳንድ ተማሪዎች መጠይቁን በሚሞሉበት ወቅት እንደሚጠይቁት ከሆነ በከፍተኛ ተቋማት የሚሰጡትን ይዘቶች በትክክል አናውቅም ከማለት የመነጨ ሊሆን ይችላል 18.4% መወሰን አልቻሉም። ከእነዚህ አሃዛዊ ስሌት መረዳት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በመሰናዶ ደረጃ የሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለከፍተኛ ተቋማት መሠረት ስለሚሆኑአቸው ተወዳጅነትን አትርፎአል።

### 3.5. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በስነጽሑፍና ድራማ ክበብ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንድሆን ረድቶኛል።

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ በ197 እና በ196 በድምሩ 393 ተማሪዎች ምላሽ ተሰጥቶበታል። ዝርዝር ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል። በጣም እስማማለሁ 18(9.1%) 30(15.3%) በድምሩ 48(12.2%)፣ እስማማለሁ 33(16.8%) 55(28%) በድምሩ

88(22.4%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 45(22.8%) 49(25%) በድምሩ 94(23.9%)፣ አልስማማም 67(34%) 45(23%) በድምሩ 112(28.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 34(17.3%) 17(8.7%) በድምሩ 51(13%) ሆኖ እናገኛለን:: አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 2.7፣3.2፣2.9 ናቸው::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ | ለ | ድ | ሀ | ለ | ድ | ሀ | ለ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 18 | 30 | 48 | 90 | 150 | 240 | 9.1 | 15.3 | 12.2 |
| እስማማለሁ | 33 | 55 | 88 | 132 | 220 | 352 | 16.8 | 28 | 22.4 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 45 | 49 | 94 | 135 | 147 | 282 | 22.8 | 25 | 23.9 |
| አልስማማም | 67 | 45 | 112 | 134 | 90 | 224 | 34 | 23 | 28.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 34 | 17 | 51 | 34 | 17 | 51 | 17.3 | 8.7 | 13 |
| ድምር | 197 | 196 | 393 | 525 | 624 | 1149 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ 2.7፣3.2፣2.9 ይሆናሉ::

የአፈፌት ተማሪዎች አማካይ ነጥብ ከግማሽ በታች 2.7 ሲሆን፣ 51.3% ተማሪዎች ሃሳቡን ተቃውመውታል:: የኢአፈፌቶቹን ያየን እንደሆነ አማካይ ነጥብ 3.2 ሲሆን ሃሳቡን የደገፉት 43.3% ናቸው:: ከዚህ ስሌት በመነሳት አንዳንድ የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት ይቻላል:: አብዛኛዎቹ አፈፌት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በስነጽሑፍና ድራማ ክበብ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አልረዳቸውም:: ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ተማሪው ለቋንቋው ትምህርት ቦታ አለመስጠቱ ሊሆን ይችላል:: በአንፃሩ ወደ ግማሽ የሚጠጉ ኢአፈፌት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በስነጽሑፍና ድራማ ክበብ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል::

### 4.2.5. የወላጅ፣ የእኩዮች፣ የህብረተሰቡና የመገናኛ ብዙሃን አመለካከት::

በተደጋጋሚ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት መሠረታዊ ጥያቄ "የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ተማሪው ለቋንቋው ትምህርት ያለው አመለካከት ለውጧል/አልለወጠም" የሚል ነው:: ይሁን እንጂ በሌሎች ነጥቦች ሥር ለማንሳት እንደተሞከረው ለመሰረታዊ ተፅዕኖ ሃይል የሚጨምሩ (Energizer) ሁኔታዎች እንዳሉ ለመገንዘብ ይቻላል:: አመለካከታችንን ሊያስለውጡን የሚችሉ በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ በክለሳ ድርሳን ውስጥ Morgan (1961, 1986), Roger and Houghton (1995) እና ሌሎችም የተጠቀሙትን ለመዳሰስ እንደተሞከረ ይታወሳል:: ስለዚህ እነዚህ ሁኔታዎች ተማሪዎች ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደሩ ወይም እንዳላሳደሩ መረጋገጥ ይገባቸዋል:: ስለሆነም እነኚህን ነጥቦች ለመፈተሽ ያስችላሉ ተብለው ሁለት አዎንታዊና አራት አሉታዊ

በድምሩ ስድስት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበላቸዋል፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሾችና የተገኘውን ውጤት ቀጥለን አንድ ባንድ እንመለከታለን፡፡

## 4.1. ቤተሰቦቼ የአማርኛን ትምህርት በወጉ እንድከታተል ያበረታቱኛል፡፡

ዐረፍተ ነገሩ አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ ለጥያቄው ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ብዛት 193 እና 194 በድምሩ 387 ናቸው፡፡ ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት ደግሞ በጣም እስማማለሁ 28(14.5%) 41(21.1%) በድምሩ 69(17.8%)፣ እስማማለሁ 53(27.5%) 51(26.3%) በድምሩ 104(26.9%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 45(23.3%) 54(27.8%) በድምሩ 99(25.6%)፣ አልስማማም 36(18.7%) 33(17%) በድምሩ 69(17.8%)፣ ፍጹም አልስማማም 31(16%) 15(7.7%) በድምሩ 46(11.9%) ሆኖ እናገኛለን፡፡ አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.1፣3.4፣3.2 ናቸው፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 28 | 41 | 69 | 140 | 205 | 345 | 14.5 | 21.1 | 17.8 |
| እስማማለሁ | 53 | 51 | 104 | 212 | 204 | 416 | 27.5 | 26.3 | 26.9 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 45 | 54 | 99 | 135 | 162 | 297 | 23.3 | 27.8 | 25.6 |
| አልስማማም | 36 | 33 | 69 | 72 | 66 | 138 | 18.7 | 17 | 17.8 |
| ፍጹም አልስማማም | 31 | 15 | 46 | 31 | 15 | 46 | 16 | 7.7 | 11.9 |
| ድምር | 193 | 194 | 387 | 590 | 652 | 1242 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ፡- 3.1፣3.4፣3.2 ናቸው፡፡

በዚህ ውጤት መሠረት 42% አፈ.ፊትና 47.4% ኢ.አፈ.ፊት ተማሪዎች ሃሳቡን በዚህ ውጤት መሠረት ተቀውመውታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሲደግሩት 34.7% አፈ.ፊትና 24.7% ኢ.አፈ.ፊት ሃሳቡን ተቃውመውታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 23.3% አፈ.ፊትና 27.8% ኢ.አፈ.ፊት ተማሪዎች ስለቤተሰቦቻቸው አቋም መወሰን አልቻሉም፡፡ ምንም እንኳን ነጥቦቹ አዎንታዊ ደረጃ ላይ ያሉ ቢሆንም፣ ከመቶኛው አንፃር ቤተሰብ ልጆቹን የአማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ ያበረታታል ብሎ ለማጠቃለል አያስደፍርም፡፡ ታሪኩ ፋንታዬ (1988) የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወላጆች ልጆቻቸውን እንደሚያበረታቱና እንደሚደግፏቸው የገለጹት ሃሳብ በዚህ ጥናት መሠረት በከፊል ብቻ ተደጋፊነት አላቸው፡፡ ምናልባት የሁለቱ የጥናት ደረጃና የተጠኑበት የጊዜ ሁኔታ እነዚህን መጠነኛ ልዩነቶች አስከትሎ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ (ሡንጠረዥ ዘጠኝ ይመልከቱ) "ወላጆች፣ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆን" የሚለው ተላውጦ ከችግሩ ክብደት አንፃር ከ388 ተማሪዎች መካከል በአንደኛ ደረጃ በ51፣ በሁለተኛ

ደረጃ በ39፣ በሶስተኛ ደረጃ በ67 ተመርጦ እናገኛለን። ስለዚህ ቤተሰብ ለቋንቋው ያለው ቦታ (Status) ያን ያህል ስለሆነ ከታሪኩ ሃሳብ ጋር አሁንም ይቃረናል።

## 4.2. ቤተሰቦቼ የአማርኛን ቋንቋ ከፖለቲካ ጋር አያይዘው ስለሚመለከቱ በኔ አማርኛ መማር በጎ አመለካከት የላቸውም።

አሉታዊ የሆነ ጥያቄ ነው። 197 እና 198 በድምሩ 395 ተማሪዎች ምላሽ ተመዝግቧል። ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 3(1.5%) 13(6.6%) በድምሩ 16(4.1%)፣ እስማማለሁ 2(1%) 12(6.1%) በድምሩ 14(3.5%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 9(4.6%) 16(8%) በድምሩ 25(6.3%)፣ አልስማማም 40(20.3%) 45(22.7%) በድምሩ 85(21.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 143(72.6%) 112(56.6%) በድምሩ 255(64.6%) ሆኖ እናገኛለን። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.6፣4.2፣4.4 ናቸው። በዚህ ውጤት መሠረት ሃሳቡን የደገፉት 7.6% ብቻ ሲሆኑ፣ የተቃወሙት ደግሞ 86.1% ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ሊ | ድ | አ | ሊ | ድ | አ | ሊ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 3 | 13 | 16 | 3 | 13 | 16 | 1.5 | 6.6 | 4.1 |
| እስማማለሁ | 2 | 12 | 14 | 4 | 24 | 28 | 1 | 6.1 | 3.5 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 9 | 16 | 25 | 27 | 48 | 75 | 4.6 | 8 | 6.3 |
| አልስማማም | 40 | 45 | 85 | 160 | 180 | 340 | 20.3 | 22.7 | 21.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 143 | 112 | 255 | 715 | 560 | 1275 | 72.6 | 56.6 | 64.6 |
| ድምር | 197 | 198 | 395 | 909 | 825 | 1734 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ:- 4.6፣4.2፣4.4 ናቸው።

ይህ ማለት ቋንቋውን ከፖለቲካ ጋር እንደማያያይዙትና በጎ አመለካከትም እንዳላቸው ነው ስለቱ የሚገልፀው። ይህ ሁኔታ በሠንጠረዥ ዘጠኝ ላይ "ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛን ቋንቋ እንደ ጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበራከት" ለሚለው ተላውጦ ከተሰጠው ምላሽ ጋር ይቃረናል። ይህ ተላውጦ ከችግሩ ክብደት አንፃር ከ388 ተማሪዎች መካከል በአንደኛ ደረጃ በ77፣ በሁለተኛ ደረጃ በ65፣ እና በሶስተኛ ደረጃ በ61 በሶስቱ ደረጃ ብቻ በ203 ተማሪዎች የተደገፈውን ሐሳብ ይቃረናል። ከዚህም በተጨማሪ በምልከታ ወቅት በተዘዋዋሪ ከአንዳንድ ተማሪዎች ባህሪ ለመረዳት የተሞከረውን እውነታዎች ይሽሩፍናል።

## 4.3. በኔ አማርኛ መማር ጓደኞቼ ይሳለቁብኛል።

ዐረፍተ ነገሩ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ 195 እና 192 በድምሩ 387 ተማሪዎች ለጥያቄው ምላሻቸውን ሰጥቷል። ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት ደግሞ፣ በጣም እስማማለሁ

5(2.6%) 10(5.2%) በድምሩ 15(3.9%)፣ እስማማለሁ 10(5.1%) 8(4.2%) በድምሩ 18(4.6%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 3(1.5%) 13(6.8%) በድምሩ 16(4.1%)፣ አልስማማም 34(17.5%) 34(17.7%) በድምሩ 68(17.6%)፣ ፍጹም አልስማማም 143(73.3%) 127(66.1%) በድምሩ 270(69.8%) ነው። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.5፣ 4.4፣4.5 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰ | ሲ. | ድ | ሰ | ሲ. | ድ | ሰ | ሲ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 5 | 10 | 15 | 5 | 10 | 15 | 2.6 | 5.2 | 3.9 |
| እስማማለሁ | 10 | 8 | 18 | 20 | 16 | 36 | 5.1 | 4.2 | 4.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 10 | 13 | 16 | 9 | 39 | 48 | 1.5 | 6.2 | 4.1 |
| አልስማማም | 3 | 34 | 68 | 136 | 136 | 272 | 17.5 | 17.7 | 17.6 |
| ፍጹም አልስማማም | 34 | 127 | 270 | 715 | 635 | 1350 | 73.3 | 66.1 | 69.8 |
| ድምር | 143 | 192 | 387 | 885 | 836 | 1721 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ 4.5፣4.4፣4.5 ይሆናሉ።

በውጤቱ መሠረት ሃሳቡን የደገፉት 8.5% ብቻ ሲሆኑ፣ የተቃወሙት ግን 87.4% ናቸው። ከዚህ ስሌት የምንረዳው ነገር በአፈፌቱም ሆነ በኢአፈፌቱ ላይ በጓደኞቻቸው በኩል አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሌለባቸው ያሳየናል።

## 4.4. የአካባቢዬ ሰዎች አማርኛን "ወንዝ የማያሻግር" እያሉ እንደትምህርት አይቆጥሩትም።

አሉታዊ የሆነ ዐረፍተ ነገር ነው። ለጥያቄው ውጤታቸው የተመዘገበው የተማሪዎች ብዛት ደግሞ 197 እና 197 በድምሩ 394 ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ 22(11.2%) 28(14.7%) በድምሩ 50(12.7%)፣ እስማማለሁ 38(19.3%) 29(14.7%) በድምሩ 67(17%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 27(13.7%) 22(11.2%) በድምሩ 49(12.4%)፣ አልስማማም 41(20.8%) 43(21.8%) በድምሩ 84(21.3%)፣ ፍጹም አልስማማም 69(35%) 75(38.1%) በድምሩ 144(36.6%) በማለት መልሰዋል። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.5፣3.6፣3.5 ሆነዋል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰ | ሲ. | ድ | ሰ | ሲ. | ድ | ሰ | ሲ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 22 | 28 | 50 | 22 | 28 | 50 | 11.2 | 14.7 | 12.7 |
| እስማማለሁ | 38 | 29 | 67 | 76 | 58 | 134 | 19.3 | 14.7 | 17 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 27 | 22 | 49 | 81 | 66 | 147 | 13.7 | 11.2 | 12.4 |
| አልስማማም | 41 | 43 | 84 | 164 | 172 | 336 | 20.8 | 21.8 | 21.3 |
| ፍጹም አልስማማም | 69 | 75 | 144 | 345 | 375 | 720 | 35 | 38.1 | 36.6 |
| ድምር | 197 | 197 | 394 | 688 | 699 | 1387 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ውጤቶች ደግሞ 3.5፣3.6፣3.5 ሆነዋል።

እዚህ ላይ 29.7% ተማሪዎች ሀሳቡን ሲደግፉ፣ 57.9% ተማሪዎች ሀሳቡን ተቃውመውታል። ይህ ማለት የአብዛኞዎቹ ተማሪዎች የአካባቢ ኅብረተሰብ ቋንቋውን "ወንዝ የማያሻግር" እያሉ አያጥላሉም። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አካባቢዎች ይህ ሁኔታ መኖሩን መረጃዎቹ አመላካች ሳይሆኑ አይቀሩም።

## 4.5. አንዳንዴ በመገናኛ ብዙሃን አማርኛን ከነፍጠኛ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡት ዝግጅቶች በአማርኛ ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዳይኖረኝ አድርጎኛል።

ይኸኛው ጥያቄ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። 197 እና 198 በድምሩ 395 ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተውበታል። ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ ቀጥሎ ያለውን ይመስላል። በጣም እስማማለሁ 12(6.1%) 33(16.7%) በድምሩ 45(11.4%)፣ እስማማለሁ 29(14.7%) 29(14.6%) በድምሩ 58(14.7%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 26(13.2%) 34(17.2%) በድምሩ 60(15.2%)፣ አልስማማም 49(24.9%) 44(22.2%) በድምሩ 93(23.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 81(41.1%) 58(29.3%) በድምሩ 139(35.2%)ነው። አማካይ 3.8፣3.3፣3.6 ደግሞ አማካይ ነጥቦች ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 12 | 33 | 45 | 12 | 33 | 45 | 61 | 16.7 | 11.4 |
| እስማማለሁ | 29 | 29 | 58 | 58 | 58 | 116 | 14.7 | 14.6 | 14.7 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 26 | 34 | 60 | 78 | 102 | 180 | 13.2 | 17.2 | 15.2 |
| አልስማማም | 49 | 44 | 93 | 196 | 176 | 372 | 24.9 | 22.2 | 23.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 81 | 58 | 139 | 405 | 290 | 695 | 41.1 | 27.3 | 35.2 |
| ድምር | 197 | 198 | 395 | 449 | 659 | 1408 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ 3.8፣3.3፣3.6 ይሆናሉ።

ሀሳቡን አፈፊቶች በ20.8% ሲደግፉት፣ ኢአፈፊቶች ደግሞ 31.3% ደግፈውታል። የሁለቱን መቶኛ እና አማካይ ነጥብ (3.8፣3.3) ስናነፃፅር በጣም ከፍተኛ ባይሆንም ልዩነት አለ። ይህ ደግሞ የሚጠቁመን በምስራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ የሚገኙ ኢአፈፊት ተማሪዎች ከአዲስ አበባዎቹ በበለጠ አንዳንዴ የመገናኛ ብዙሃን ስለቋንቋው የሚያስተላልፉአቸው ነገሮች በተማሪዎች አመለካከት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ያሳያል። እንዲሁም ሀሳቡን የተቃወሙትን የአፈፊቶችንና የኢአፈፊቶችን አሃዝ ብናነፃፅር የአፈፊቶች በልጠ እናገኛለን። ይኸኛውም ቢሆን በኢአፈፊቶቹ ላይ ጫና መኖሩን ይጠቁማል።

### 4.6. በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪዎች አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ለማዳበር የመምህሩ ሁኔታ ትልቅ ድርሻ አለው::

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው:: 198 እና 198 በድምሩ የ396 ተማሪዎች ምላሽ ተመዝግቧል:: ውጤቱን በዝርዝር ስናስቀምጥ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 140(70.7%) 110(55.6%) በድምሩ 250(63.1%)፣ እስማማለሁ 46(23.2%) 53(26.8%) በድምሩ 99(25%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 2(1%) 15(7.6%) በድምሩ 17(4.3%)፣ አልስማማም 4(2%) 10(5%) በድምሩ 14(3.5%)፣ ፍጹም አልስማማም 6(3%) 10(5%) በድምሩ 16(4%) የሚል ነው:: 4.6፣ 4.2፣ 4.4 ይሆናሉ::

ሀሳቡን የደገፉት 88.1% ሲሆኑ፣ የተቃወሙት 7.5% ብቻ ናቸው:: በዚህ ስሌትና ከአማካይ ነጥቦቹ አንፃር ስንመለከት አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ለማዳበር የመምህሩ ሁኔታ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ያምናሉ:: በምልከታ ወቅትም የታየው ነገር ከመምህሩን መምህሩን የተማሪዎች አመለካከት ሊለያይ እንደሚችል ነው::

ለበለጠ ግንዛቤ ሰንጠረዡን ይመልከቱ:::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 140 | 110 | 250 | 700 | 550 | 1250 | 70.7 | 55.6 | 63.1 |
| እስማማለሁ | 46 | 53 | 99 | 184 | 212 | 396 | 23.2 | 26.8 | 25 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 2 | 15 | 17 | 6 | 45 | 51 | 1 | 7.6 | 4.3 |
| አልስማማም | 4 | 10 | 14 | 8 | 20 | 28 | 2 | 5 | 3.5 |
| ፍጹም አልስማማም | 6 | 10 | 16 | 6 | 10 | 16 | 3 | 5 | 4 |
| ድምር | 198 | 198 | 396 | 904 | 837 | 1741 | 100 | 100 | 100 |

4.6፣ 4.2፣ 4.4 አማካይ ነጥቦች ናቸው::

## 4.2.6. የመማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ

መድሃኔ (1986)፣ ታሪኩ (1988)፣ አበበ (1990)፣ ዳንኤል (1992) እና ሌሎችም ሥራዎች እንደሚያረጋግጡልን የመማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ በተማሪዎች አመለካከት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አለው:: የመጻሕፍቱ ይዘትና አቀራረብ ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት እንዲወዱትም ወይም እንዲጠሉትም የበኩሉን ድርሻ ይጫወታል:: የተማረውን ትምህርት እንዲወዱትም ወይም እንዲጠሉትም የበኩሉን ድርሻ ይጫወታል:: የተማረውን ስሜት የሚገዛ ከሆነ በትኩረት ትምህርቱን ስለሚከታተሉ አጥጋቢ ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ:: ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡበት ከሆነ ደግሞ በተቋሙ የመግቢያ ፈተና ውስጥ

አለመካተቱ ይጎዳቸዋል ማለት ነው። በተፃራሪው ደግሞ የመጻሕፍቱ ይዘትና አቀራረብ ያን ያህል ከሆነ ደግሞ በፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ምክንያት በስሜታቸው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እስከዚህም ነው ማለት ነው።

ከእነዚህ እውነታዎች በመነሳት በመሰናዶ ደረጃ የሚሰጡትን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አስመልክቶ አንድ አዎንታዊና አንድ አሉታዊ በድምሩ ሁለት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበላቸዋል። ለነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ውጤት ቀጥለን የምንመለከት ይሆናል።

## 6.1. የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ ቋንቋውን ተወዳጅ ያደርገዋል።

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሻቸውን የሰጡት 196 እና 197 በድምሩ 393 ናቸው። ዝርዝር ውጤቶችን ስንመለከት፣ በጣም እስማማለሁ 42(21.4%) 56(28.4%) በድምሩ 98(24.9%)፣ እስማማለሁ 62(31.6%) 68(34.5%) በድምሩ 130(33.1%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 55(28.1%) 43(21.8%) በድምሩ 98(24.9%)፣ አልስማማም 22(11.2%) 20(10.2%) በድምሩ 42(10.7%)፣ ፍጹም አልስማማም 15(7.7%) 10(5.1%) በድምሩ 25(6.4%) ይሆናል። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.5፣ 3.7፣ 3.6 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ | አ | ኢ | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 42 | 56 | 98 | 210 | 280 | 490 | 21.4 | 28.4 | 24.9 |
| እስማማለሁ | 62 | 68 | 130 | 248 | 272 | 520 | 31.6 | 34.5 | 33.1 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 55 | 43 | 98 | 165 | 129 | 294 | 28.1 | 21.8 | 24.9 |
| አልስማማም | 22 | 20 | 42 | 44 | 40 | 84 | 11.2 | 10.2 | 10.7 |
| ፍጹም አልስማማም | 15 | 10 | 25 | 15 | 10 | 25 | 7.7 | 5.1 | 6.4 |
| ድምር | 196 | 197 | 393 | 682 | 731 | 1413 | 100 | 100 | 100 |

3.5፣ 3.7፣ 3.6 አማካይ ነጥቦች ናቸው።

በዚህ ውጤት መሠረት አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት ወይም ሃሳቡን የደገፉት 58.7% ሲሆኑ፣ በሃሳቡ ያልተስማሙት ደግሞ 17.1% ናቸው። መወሰን ያልቻሉት 24.9% ይሁኑ እንጂ ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የመጽሐፍቱ ይዘትና አቀራረብ ቋንቋውን እንዲወዱት አድርጓቸዋል። ቀደም ሲል በ"3.4" ሥር "በመሰናዶ ደረጃ የሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለከፍተኛ ተቋማት መሠረት በመሆናቸው ወድጄአቸዋለሁ" ለሚለው የተሰጠው ምላሽ አዎንታዊ ነበር 68% ሃሳቡን ሲደግፉት 13.6% ብቻ ነው የተቃወሙት።

እንዲሁም በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት ሊያዳብሩ ይችላሉ ተብለው በጥያቄ “ሠ” (አባሪ “ሀ”ን ይመልከቱ) ከቀረቡት ተላውጦዎች አንዱ የመማሪያ መጻሕፍት ነበር። ተማሪዎቹ እንደችግሩ ክብደት በደረጃ በሚያስቀምጡበት ወቅት ከፍተኛውን አሃዝ የያዙት የመጨረሻዎቹ ሶስት ደረጃዎች ናቸው። ከእነዚህ እውነታዎች በመነሳት በመሰናዶ ደረጃ የሚቀርቡት ይዘቶችና አቀራረባቸው አብዛኛዎቹን ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲወዱት አድርጎአቸዋል።

### 6.2. በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል ውስጥ የተካተቱ ይዘቶችና አቀራረባቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንድጠላ አድርጎኛል።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ የተመዘገበው ምላሽ 198 እና 196 በድምሩ የ394 ተማሪዎች ነው። የተገኘውም ውጤት፣ በጣም እስማማለሁ 8(4%) 13(6.6%) በድምሩ 21(5.3%)፣ እስማማለሁ 6(3%) 20(10.2%) በድምሩ 26(6.6%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 31(15.7%) 32(16.3%) በድምሩ 63(16%)፣ አልስማማም 61(30.8%) 43(22%) በድምሩ 104(26.4%)፣ ፍጹም አልስማማም 92(46.5%) 88(44.9%) በድምሩ 180(45.7%) ሆኖ ተገኝቷል። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.1፣3.9፣4.0 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ሴ. | ድ | አ | ሴ. | ድ | አ | ሴ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 8 | 13 | 21 | 8 | 13 | 21 | 4 | 6.6 | 5.3 |
| እስማማለሁ | 6 | 20 | 26 | 12 | 40 | 52 | 3 | 10.2 | 6.6 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 31 | 32 | 63 | 93 | 96 | 189 | 15.7 | 16.3 | 16 |
| አልስማማም | 61 | 43 | 104 | 244 | 172 | 416 | 30.8 | 22 | 26.4 |
| ፍጹም አልስማማም | 92 | 88 | 180 | 460 | 440 | 900 | 46.5 | 44.9 | 45.7 |
| ድምር | 198 | 196 | 394 | 817 | 761 | 1578 | 100 | 100 | 100 |

አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.1፣3.9፣4.0 ናቸው።

ሃሳቡን የደገፉት 11.9% ሲሆኑ፣ ሀሳቡን የተቃወሙት ደግሞ 72.9% ይሆናሉ። ይህ ስሌት ከ«6.1» በተጨማሪ የሚያስገነዝበን በመሰናዶ ደረጃ የሚቀርቡት ይዘቶችና አቀራረባቸው አብዛኛውን ተማሪ ቋንቋውን እንዲጠላ ሳይሆን፣ ቋንቋውን እንዲወደው አድርገውታል። መምህራንም በመጠይቆቹ ተ.ቁ. «3» (አባሪ «ለ»ን ይመልከቱ) ላይ «በመሰናዶ ደረጃ የተዘጋጁት መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ አመለካከት የሚያሳድሩ አይደሉም» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ የተገኘው ምላሽ ከአስሩ መምህራን ዘጠኙ በሃሳቡ ተስማምተዋል። እንዲሁም በሠንጠረዥ አሥራ አምስት ላይ

አሉታዊ ተላውጦዎችን እንደ ችግሩ ክብደት በደረጃ ሲያስቀምጡ ስምንት መምህራን በመጨረሻዎቹ ሁለት ደረጃዎች (7 እና 8) ላይ አስቀምጠዋል።

## 4.2.7. ለአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከተሰጠው ዝቅተኛ ደረጃ አንፃር

እዚህ ላይ ወደ ዋናው ነጥብ ከመግባታችን በፊት የኢፌዲሪ የ1987 ዓ.ም ሕገ መንግሥት የቋንቋ ድንጋጌና በ1986 ዓ.ም በሽግግር መንግስት የወጣው የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ ለአማርኛ ቋንቋ የሰጡትን ቦታ (Status) ባጭሩ እንመልከት። ሕገ መንግስቱ የፌደራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ አማርኛ እንደሆነ ደንግጎ እናገኛለን። በአንፃሩ የትምህርት ፖሊሲው አስፈፃሚ የትምህርት ሚኒስቴር የቋንቋው ትምህርት ለአፈፈቶችና ለኢአፈፈቶች የሚሰጥበት ደረጃ ለያይቶ አውጥቷል። ነገር ግን በአንዳንድ ክልሎች ከፖሊሲ ውጭ ትምህርቱን በሚሰጡበት ወቅት በዝምታ አልፎታል። በእነዚህ ሁኔታ መፈጠር ምክንያት ይመስላል አሥረኛ ክፍል ላይ በሚሰጠው ብሔራዊ ፈተና የአማርኛ ውጤት አማራጭ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። ቀደም ሲል 3 እና 4 ክፍለ ጊዜ ለቋንቋው ይሰጠው የነበረው ወደ ሁለት ወርዶ እናገኘዋለን። በአጥኚው ግምት እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ተደማምረው ለተቋም የመግቢያ ፈተና ላይ ካለመካተቱ ጋር የተማሪው አመለካከት ሊያስለውጥ ይችላል የሚል እምነት አለው። በመሆኑም ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አንድ አዎንታዊና አንድ አሉታዊ በድምሩ ሁለት ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርቦላቸዋል። በመቀጠል ደግሞ ለእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ውጤት እንመለከታለን።

### 7.1. አማርኛ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ በመሰናዶ ክፍሎች (Preparatory Classes) ያለአማራጭ ቢሰጥ ደስ ይለኛል።

ዐረፍተ ነገሩ አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሻቸውን የሰጡት ተማሪዎች ብዛት 200 እና 199 በድምሩ 399 ናቸው። የምላሹ ዝርዝር ውጤት ቀጥሎ ይቀርባል። በጣም እስማማለሁ 47(23.5%) 47(23.6%) በድምሩ 94(23.6%)፣ እስማማለሁ 71(35.5%) 45(22.6%) በድምሩ 116(29.1%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 41(20.5%) 42(21.1%) በድምሩ 83(20.8%)፣ አልስማማም 25(12.5%) 27(13.6%) በድምሩ 52(13.1%)፣ ፍጹም አልስማማም 16(8%) 38(19.1%) በድምሩ 54(13.5%) ሆኖ እናገኛለን። አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 3.54፣ 3.18፣ 3.36 ናቸው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 47 | 47 | 34 | 235 | 235 | 470 | 23.5 | 23.6 | 23.6 |
| እስማማለሁ | 71 | 45 | 116 | 284 | 180 | 464 | 35.5 | 22.6 | 29.1 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 41 | 42 | 83 | 123 | 126 | 249 | 20.5 | 21.1 | 20.8 |
| አልስማማም | 25 | 27 | 52 | 50 | 54 | 104 | 12.5 | 13.6 | 13.1 |
| ፍጹም አልስማማም | 16 | 38 | 54 | 16 | 38 | 54 | 8 | 19.1 | 13.5 |
| ድምር | 200 | 199 | 399 | 708 | 633 | 1341 | 100 | 100 | 100 |

3.54፣ 3.58፣ 3.36 አማካይ ነጥቦቹ ናቸው::

አማካይ ነጥቦቹም አዎንታዊ ሲሆኑ፣ በመቶኛ ሲታይ ሃሳቡን የደገፉት 52.7% ናቸው:: በአንፃሩ ሃሳቡን የተቃወሙት ደግሞ 26.6% ናቸው:: ለመወሰን ያልቻሉት 20.8% ናቸው:: ይህ የሚያስገነዝበውን በአፈፈቱም ሆነ በኢአፈፈቱ በኩል አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመሰናዶ ደረጃ ያለአማራጭ እንዲሰጥ ይፈልጋሉ::

## 7.2. የአማርኛ ውጤት ቦታ ስለሌለው ዋጋ እንዳለው ትምህርት አልቆጥረውም::

አሉታዊ የሆነ ዐረፍተ ነገር ነው:: የ199 እና የ199 በድምሩ የ398 ተማሪዎች ውጤት ተመዝግቧል::የውጤቱ ዝርዝር ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል:: በጣም እስማማለሁ 11(5.5%) 25(12.7%) በድምሩ 35(8.8%)፣ እስማማለሁ 24(12.1%) 21(10.6%) በድምሩ 45(11.3%)፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 19(9.6%) 23(11.6%) በድምሩ 42(10.6%)፣ አልስማማም 50(25.1%) 37(18.6%) በድምሩ 87(21.9%)፣ ፍጹም አልስማማም 95(47.7%) 94(47.2%) በድምሩ 189(47.4%) :: አማካይ ነጥቦቹ ደግሞ 4.0፣ 3.8፣ 3.9 ናቸው::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | | የተገኘው ነጥብ | | | መ ቶ ኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ | አ | ኢ. | ድ |
| በጣም እስማማለሁ | 11 | 24 | 35 | 11 | 24 | 35 | 5.5 | 12.7 | 8.8 |
| እስማማለሁ | 24 | 21 | 45 | 48 | 42 | 90 | 12.1 | 10.6 | 11.3 |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 19 | 23 | 42 | 57 | 69 | 126 | 9.6 | 11.6 | 10.6 |
| አልስማማም | 50 | 37 | 87 | 200 | 148 | 348 | 25.1 | 18.6 | 21.9 |
| ፍጹም አልስማማም | 95 | 94 | 189 | 475 | 470 | 945 | 47.7 | 47.2 | 47.4 |
| ድምር | 199 | 199 | 398 | 791 | 753 | 1544 | 100 | 100 | 100 |

4.0፣ 3.8፣ 3.9 አማካይ ነጥቦቹ ናቸው::

ውጤቱ ስምንም የማያበቃ ስለሆነ ዋጋ እንዳለው ትምህርት አልቶጥረውም የሚለውን ሀሳብ የደገፉት 20.1% ናቸው። በአንፃሩ ሃሳቡን የተቃወሙት ደግሞ 69.3% ናቸው። እስቲ የድጋፉንም ሆነ የተቃውሞውን ምላሽ ከሌሎች መልሶች ጋር እያስተያየን እንመልከት። ክፍለ ጊዜው ከሌሎች ያነሰ መሆን፣ ለተቋም የመግቢያ ፈተና አለመስጠት፣ ሕብረተሰቡ ለቋንቋው የሚሰጠው ቦታ አልፎ አልፎ አሉታዊ መሆን በብሔራዊ ፈተና ውጤቱ አማራጭ ውስጥ መግባቱ ወዘተ ጉዳዮች አሉታዊውን ሃሳብ እንደሚደግፉ ገፋፍቶአቸው ሊሆን ይችላል። አሉታዊውን ሃሳብ የተቃወሙት ደግሞ ምንም እንኳን የተለያየ ተፅዕኖ ቢኖርባቸውም ቋንቋውን እንደማይጠሉት፣ የመማሪያ መፃሕፍቱ ይዘቶች ጠቃሚ እንደሆኑ ወዘተ ቀደም ሲል በተማሪዎች እንደተረጋገጠ ተመልክተናል። ያም ሆነ ይህ ከተመዘገቡት ውጤቶች በመነሳት ሃሳቡን በሚከተለው መልክ ማጠቃለል ይቻላል። ምንም እንኳን የተለያዩ ተፅዕኖዎች ቢኖሩና ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ባይሰጥም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ትምህርቱን ይወዱታል።

## 4.2.8. ልቅ (Open) ጥያቄዎች

በጽሑፍ መጠይቁ በስተመጨረሻ ሁለት ልቅ ጥያቄዎች ለተማሪዎቹ ቀርቦላቸዋል። ጥያቄዎቹ አጠቃላይ አስተያየት ወይም ምክንያት ለመመለስ የሚጋብዙ ናቸው። የመጀመሪያው «ረ.ሀ» ሥር የአማርኛ ቋንቋን መማር በጣም የሚያስደስትሽ/ የሚያስደስትህ ከሆነ ምን ምን ነገሮች እንዲሻሻል ትጠቁሚያለሽ/ትጠቁማለህ? የሚል አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ሁለተኛው «ረ.ለ» ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ከሌለሽ/ከሌለህ ቋንቋውን እንድትጠይ/እንድትጠላ ያደረገሽ/ያደረገህ ነጥቦች አስፍሪ/አስፍር። ይኸኛው ዐረፍተ ነገር ደግሞ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው።

ለእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች (ረ.ሀ እና ረ.ለ) የተሰጡት ምላሾች ተሰብስበው በሰንጠረዥ መልክ ቀርበዋል። በዚሁ መሠረት ለ«ረ.ሀ» የተሰጡት ገንቢ አስተያየቶች በሰንጠረዥ አሥራ ሶስት ላይ ተጠናቅረው ቀርበዋል። እንዲሁም ለ«ረ.ለ» የተሰጡት ምክንያቶች በሠንጠረዥ አሥራ አራት ተጠናቅረዋል። ስለዚህ ለአጠቃላይ ግንዛቤ ሠንጠረገዦቹን ይመልከቱ።

በሠንጠረገዡ ላይ የድግግሞሹ መቶኛ የተሠራው በሚከተለው ቀመር መሠረት መሆኑን አጥኚው ለመግለጽ ይወዳል።

ቀመር = ድግግሞሽ ሲባዛ በመቶ ሲካፈል ለመላሾች ብዛት ነው።

የተሰጡት ገንቢ አስተያየቶችም ሆነ ለቋንቋው መጠላት ምክንያት ብለው ያስቀመጧቸው ነጥቦች በሶስት ተከፍለው ቀርበዋል። መክፈል ያስፈለገበት ምክንያት

1ኛ/ የቀረቡት አስተያየቶች ከየትኛው ወገን እንደሆነ ከነምንጩ እንድናውቀው፣

2ኛ/ አንዳንዱ አስተያየቶች የአንድ ወገን ብቻ በመሆናቸው። ይኸውም ነጥቡ አፈፊቱን ብቻ ወይም ኢአፈፊቱን ብቻ የሚመለከት ሆኖ ስለሚገኝ ነው።

በዚሁ መሠረት «ሀ» ሥር የተዘረዘሩት ከአፈፊቶች ብቻ የቀረቡ አስተያየቶች ወይም ምክንያቶች ናቸው። «ለ» ሥር የተጠቀሱት ደግሞ ከኢአፈፊቶች ብቻ የቀረቡ ሐሳቦች ናቸው። «ሐ» ሥር የተዘረዘሩት ግን በሁለቱም ወገን የተጠቀሱ ነጥቦች ናቸው።

ሰንጠረዥ አሥራ ሶስት፡-

ለ«ረ.ሀ» የሰፈሩ አዎንታዊ አስተያየቶች

| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| | ሀ/ በቋንቋው አፈፊት ተማሪዎች ብቻ የተሰጡ አስተያየቶች | | |
| 1 | ማህበረሰቡ፣ ትምህርት ሚኒስቴር በተለይ መንግስት ለአማርኛ ቋንቋ ያለውን አዎንታዊ አመለካከት ከፍ ቢያደርግና ለቋንቋው ትኩረት ቢሰጥ፣ | 27 | 13.5 |
| 2 | ህብረተሰቡ በባዕድ ቋንቋ ማምለኩን ቢያቆም፣ | 25 | 12.5 |
| 3 | 10 እና 12 ላይ ቋንቋው ወሳኝ ('Compulsory) ትምህርት ቢሆን፣ | 22 | 11 |
| 4 | አንዳንድ ብሔረሰቦች በአማርኛ ቋንቋ ላይ በጎ አመለካከት ስለሌላቸው ይህ አስተሳሰብ የሚለወጥበት ስልት ቢቀየስ፣ | 21 | 10.5 |
| 5 | ታች ባሉት ክፍሎች በቂ ችሎታ ያላቸው መምህራን ቢመደቡ፣ | 10 | 5 |
| 6 | ለመምህራን በየጊዜው የሞያ ማሻሻያ ኮርስ ቢሰጥ፣ | 10 | 5 |
| 7 | የሀገሪቷ የጋራ መግባቢያ በመሆኑ ትኩረት ቢሰጠው፣ | 8 | 4 |
| 8 | መምህራን ተማሪዎችን በማነሳሳት በኩል ትልቅ ሚና መጫወት አለባቸው፣ | 6 | 3 |
| 9 | በየጊዜው የስነጽሁፍ ዝግጅት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ቢዘጋጁ፣ | 6 | 3 |
| 10 | መምህራን በማስተማሩም ሆነ በውጤት አሰጣጡ ግዴለሽ ባይሆኑ፣ | 5 | 2.5 |
| 11 | መጻሕፍቱ ምንባብ ላይ ከማተኮር እንደ ቃላት፣ ቅኔ፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ወዘተ ላይ ትኩረት ቢያደርግ | 5 | 2.5 |
| 12 | በICT በሚተላለፈው ትምህርት ውስጥ አማርኛ ቢካተት፣ | 5 | 2.5 |
| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት | መቶኛ |
| | ለ/ ለቋንቋው ኢአፈፊት የሆኑ ተማሪዎች ብቻ የሰጡት አስተያየት | | |
| 1 | በመሰናዶ ደረጃ ቋንቋው ያለአማራጭ ቢሰጥ | 31 | 15.5 |
| 2 | ከ1-4 ባሉ ክፍሎች ትምህርቱ ቢሰጥ፣ | 30 | 15 |
| 3 | የተማሪዎች በታች ክፍሎች መሠረት ማጣት | 30 | 15 |
| 4 | መጽሐፉ ለሁለተኛ ቋንቋ የተማሪዎችም በሚገባ መልኩ በቀላል አቀራረብ ቢቀርብ፣ | 25 | 12.5 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | የመገናኛ ብዙሃን ስለቋንቋው የሚያስተላልፉት የተሳሳተ (የተዛባ) አስተሳሰብ እንዲቆም ቢደረግ፣ | 19 | 9.5 |
| 6 | በየትምህርት ቤቶቹ የስነጽሑፍ ክበባት ቢጠናከሩና ተማሪዎች በስነጽሁፍ፣ በድራማ ወዘተ እንዲሳተፉ ቢደረግ፣ | 19 | 9.5 |
| 7 | የመማሪያ መጽሐፎቹ በውስጣቸው አንዳንድ አስፈላጊ ማስታወሻዎችን (Notes) ቢኖራቸው፣ | 10 | 5 |
| 8 | ስለቋንቋው እኩልነት በደንብ ብንማር፣ | | |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ ይበልጣል ብሎ መከራከሪያ ቢቀር፣ | 5 | 2.5 |
| 10 | ለቲአትር ጥበብ ትኩረት ቢሰጥ:: | 2 | 1 |

| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| | **ሐ/ በሁለቱም ወገን የተሰነዘሩ አስተያየቶች** | | |
| 1 | ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ቢሰጥ፣ | 325 | 81.25 |
| 2 | ተደጋጋሚና አሰልቺ የመልመጃዎች አቀራረብ ቢሻሻል፣ | 101 | 25.25 |
| 3 | ስለቋንቋው ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መርጃ መጽሐፍት በበቂ ሁኔታ ቤተ መፃሕፍት ውስጥ ቢኖሩ፣ | 99 | 24.75 |
| 4 | መጽሐፎቹ ዘና የሚያደርጉ ሆነው ቀለል ባለ መልኩ ቢዘጋጁ፣ | 99 | 24.75 |
| 5 | የተሰጠው ክፍለጊዜ በጣም ያንሳል፣ | 91 | 22.75 |
| 6 | በይበልጥ ለቋንቋው ፍላጎት ያላቸው መምህራን ቢያስተምሩ፣ | 75 | 18.75 |
| 7 | መምህራን ተማሪውን የሚያሳትፍ የማስተማር ስልት ቢያዘወትሩ፣ | 75 | 18.75 |
| 8 | ተማሪውን የሚስብ እንደ ግጥም፣ ልብወለድ፣ ቅኔ፣ ስነቃሎች፣ ትረካ፣ ቀልድ፣ ድርሰት መፃፍ ወዘተ በርከት ብለው ቢቀርቡና ብንለማመድ፣ | 75 | 18.75 |
| 9 | ብቁ ችሎታ ያላቸው መምህራን ቢመደቡ፣ | 70 | 17.5 |
| 10 | ሰዎች ቋንቋውን ከፖለቲካ ጋር እንዳያያይዙት ማስተማር፣ | 21 | 25.25 |
| 11 | ህብረተሰቡ ለቋንቋው አክብሮትና ፍቅር ቢሰጠው ቋንቋውን በይበልጥ ተመራጭ ያደርገዋል፣ | 18 | 4.5 |
| 12 | የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ለመለወጥ ቅስቀሳ ቢደረግና ከታች ክፍሎች ጀምሮ በተጠናከረ መልክ ትምህርቱ ቢሰጥ፣ | 18 | 4.5 |
| 13 | አንዳንድ ከበድ ከበድ ያሉ ቃላት ባይካተቱ ወይም አማራጭ ፍቺ በቅንፍ ውስጥ ቢቀመጥ፣ | 15 | 3.75 |
| 14 | አንዳንዶቹ ምንባቦች አጥረው ቢቀርቡ | 15 | 3.75 |

## ሠንጠረዥ አሥራ አራት

«ረ.ስ» ቋንቋውን እንዲጠሉት ያደረጋቸው ምክንያቶች

| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| | **ሀ/ ከአፈፌት ተማሪዎች** | | |
| 1 | ቋንቋውን እናውቀዋለን ብለን ስለምንገምተው ቦታ አንሰጠውም፤ | 19 | 9.5 |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለሰለጠኑ ሰዎች ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት፤ | 16 | 8 |
| 3 | አንዳንድ ጊዜ ትምህርቱ ከምንገምተው በላይ ስለሚከብድ እንጠላዋለን፤ | 10 | 5 |
| 4 | የአስራ ሁለተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አሰልቺና ሰዋስው ላይ ያተኮረ በመሆኑ | 5 | 2.5 |
| | **ለ/ ከኢአፈፌት ተማሪዎች** | | |
| 1 | ከህብረተሰቡ የሚነገሩ አሉታዊ አባባሎች፤ | 31 | 15.5 |
| 2 | ከፖለቲካና ከዘረኝነት ጋር ቋንቋውን ስለሚያያይዙት ተምረንም ስለማንጠቀምበት፤ | 30 | 15 |
| 3 | ብንማረውም ሥራ ስለማናገኝበት፤ | 28 | 14 |
| 4 | የአንዳንድ መምህራን አቀራረብ፤ | 11 | 5.5 |
| | **ሐ/ ከሁለቱም ወገን የቀረቡ ምክንያቶች** | | |
| 1 | በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ፤ | 155 | 38.75 |
| 2 | ተምረንም ትምህርቱ ዋጋ ስለሌለው፤ | 89 | 22.25 |

በሠንጠረዥ አሥራ ሶስት ሥር የቀረቡት አስተያየቶች ብዙ ክፍሎችን የሚመለከቱ ናቸው። በሌላ አነጋገር ፈርጀ ብዙ ናቸው። የመንግስት ፖሊሲን የሚጠይቁ፣ የህብረተሰብ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት የሚመለከቱ፣ መምህራን ላይ ያተኮሩ፣ ሥርዓተ ትምህርትን የሚጠቅሱ፣ በጀትን የሚጠይቁ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ ሊቀረፉ የሚችሉ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። በጥቅሉ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ሁሉ አውቀውት የግልም ሆነ የጋራ እልባት ቢፈልጉለት አሁን በቋንቋው ላይ እየተቀጣጠለ የመጣው አሉታዊ አመለካከት ተለውጦ አዎንታዊ የማይሆንበት ምክንያት የለም።

ሠንጠረዥ አሥራ አራትንም ያየን እንደሆነ ከአስራ ሶስቱ ብዙም አይለይም፤ ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው። በአስተያየት መልክ እንዲሻሻሉ የተጠየቁት ነገሮች ናቸው ለቋንቋው መጠላት እንደ ምክንያት በዚህኛው ሠንጠረዥ ሥር የሰፈሩት። ሠንጠረዥ አስራ ሶስት ላይ የተሰጡት አስተያየቶች እልባት ካገኙ የዚህኛውም ችግር ይፈታል።

## 4.3. ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በናሙናነት ተወስደው መጠይቁን የሞሉት መምህራን ብዛት አሥር ናቸው:: ለመምህራኑ የቀረቡት ጥያቄዎች ከሁለቱም ዓይነት ማለትም ውስን አጠያየቅ (Closed form) እና ልቅ አጠያየቅ (Open form) ያቀፉ ጥያቄዎች ናቸው:: በውስን መልክ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል አስሮቹ በሊከርት ስኬል መሠረት የቀረቡላቸው ሲሆን፣ ስምንት ጥያቄዎች ደግሞ የተሰጡትን ተላውጦዎች በደረጃ ማስቀመጥ ነው:: በልቅ መልክ የቀረቡት ሶስት ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ መምህራኑ ነፃ ሆነው የራሳቸውን አስተያየት ወይም መልስ የሚያሰፍሩበት የጥያቄ ክፍል ነው::

ከዚህ በመቀጠል እነዚህን ለመምህራን የቀረቡትን ጥያቄዎችና የተመዘገቡትን ምላሾች አንድ ባንድ የምንመለከት ይሆናል::

### 4.3.1. በሊከርት ስኬል የአለካክ ዘዴ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገበ ውጤት::

1/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ ከመታወቁ በፊትና ከታወቀ በኋላ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ አስከትሏል::

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው:: አስሩም መምህራን ምላሻቸውን የሰጡበት ሲሆን፣ ዝርዝር ውጤቱ የሚከተለውን ይመስላል::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 7 | 35 | |
| እስማማለሁ | 1 | 4 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 1 | 3 | |
| አልስማማም | 1 | 2 | |
| ፍጹም አልስማማም | 0 | - | |
| ድምር | 10 | 44 | 4.4 |

2/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተናነት መሰጠት አለመሰጠቱ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ያመጣው ለውጥ የለም::

አዎንታዊ ጥያቄ ነው:: አስሩም መምህራን ምላሻቸውን አስፍረዋል:: ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ የሚከተለውን ሆኖ ተገኝቷል::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 1 | 5 | |
| እስማማለሁ | 1 | 4 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 0 | - | |
| አልስማማም | 1 | 2 | |
| ፍጹም አልስማማም | 7 | 7 | |
| ድምር | 10 | 18 | 1.8 |

ከተመዘገበው ውጤትና ከአማካይ ነጥቡ እንደምንረዳው መምህራኑ በከፍተኛ ደረጃ ሃሳቡን ተቃውመውታል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየን በተራ ቁጥር «1» እንዳረጋገጡት ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም አለመሰጠቱ ከታወቀ በኋላ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ በተማሪዎች ላይ ተከስቷል፡፡

3/ በመሰናዶ ደረጃ የተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ አመለካከት የሚያሳድሩ አይደሉም፡፡

አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሆኖ፣ የሚከተለውን ውጤት ተገኝቷል፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 5 | 25 | |
| እስማማለሁ | 4 | 16 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 0 | - | |
| አልስማማም | 0 | - | |
| ፍጹም አልስማማም | 1 | 1 | |
| ድምር | 10 | 42 | 4.2 |

ከአንድ መምህር በስተቀር ዘጠኙም የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘትና አቀራረብ አሉታዊ አመለካከትን የሚያሳድሩ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

4/ ቋንቋውን በማስተማሬ ብዙ የስነጽሑፍ፣ የስነልሳን ወዘተ በለሙያዎችን እንዳፈራ ስለሚያስችለኝ፣ እረካበታለሁ፡፡

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡ አስሩ መምህራን የሚከተለውን መልስ ሞልተዋል፡፡ በጣም እስማማለሁ 2፣ እስማማለሁ 2፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 6፣ አልስማማም 0፣ ፍጹም አልስማማም 0 የሚል ሲሆን፣ አማካይ ነጥቡም 3.6 ነው፡፡

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 2 | 10 | |
| እስማማለሁ | 2 | 8 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 6 | 18 | |
| አልስማማም | 0 | - | |
| ፍጹም አልስማማም | 0 | - | |
| ድምር | 10 | 36 | 3.6 |

እዚህ ላይ ከፍተኛውን አሃዝ ለመወሰን ያስቸግረኛል የሚለው ነው። ምናልባት መምህራኑ ይህን ሊሉ የቻሉት የተማሪዎቹን የምርጫ መስክ ስለማያውቁት ሊሆን ይችላል።

5/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ላይ ቢሰጥ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉት ያደርጋቸዋል።

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ሲሆን፣ አስሩም መምህራን ምላሽ ሰጥተውበታል። የተመዘገበውን ውጤት ስንመለከት ደግሞ ሁሉም መምህራን በጣም እስማማለሁ ብለው ስለመለሱ አማካይ ነጥቡ 5.0 ነው።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 10 | 50 | |
| እስማማለሁ | - | - | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | - | - | |
| አልስማማም | - | - | |
| ፍጹም አልስማማም | - | - | |
| ድምር | 10 | 50 | 5.0 |

ከዚህ ምላሽ ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ቋንቋው በመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ምን ያህል ችግር እንደፈጠረ ነው። አስሩም ምክንያት በመማር ማስተማሩ ክንውን ላይ ምን ያህል ችግር እንደፈጠረ ነው። አስሩም መምህራን ተመሳሳይ መልስ መስጠታቸው ችግሩ በሁለቱም ወገን ማለትም በአፈፌቱም አካባቢ ሆነ በኢአፈፌቱ ዘንድ የሚንፀባረቅ ችግር እንደሆነ ያሳየናል።

6/ ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ስለማይሰጡና ጥሩም አመለካከት ስለሌላቸው ሌላ ትምህርት ባስተምር ደስ ይለኛል።

ጥያቄው አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ የሰጡት መምህራን 8 ብቻ ሲሆኑ፣ ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ ቀጥሎ ያለውን ይመስላል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 1 | 1 | |
| እስማማለሁ | 0 | - | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 0 | - | |
| አልስማማም | 5 | 20 | |
| ፍጹም አልስማማም | 2 | 10 | |
| ድምር | 8 | 31 | 3.9 |

ሀሳቡን የደገፈው አንድ ሰው ብቻ ሲሆን ሰባቱ ሃሳቡን ተቃውመውታል። ይህ ማለት ደግሞ አብዛኞዎቹ መምህራን ሌላ ትምህርት ከማስተማር የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር እንደሚፈልጉ ያስገነዝበናል። ይሁን እንጂ በተማሪዎቹ የአመለካከት ለውጥ ምክንያት የእንጀራ ጉዳይ ሆኖባቸው እንጂ የሥራ ሞራሉ የሸሻቸው መምህራን እንዳሉ በምልከታ ወቅት ለመታዘብ ተችሏል።

7/ አማርኛ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ በመሰናዶ ደረጃ አማራጭ ውስጥ ባይገባ ይመረጣል።

ጥያቄው አዎንታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ለጥያቄው የአስሩም መምህራን ምላሽ ተመዝግቦለታል። ዝርዝር ውጤቱን ስንመለከት የሚከተለውን ይመስላል። በጣም እስማማለሁ 4፣ እስማማለሁ 1፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 0፣ አልስማማም 2፣ ፍጹም አልስማማም 3 ሆኖ እናገኛለን።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 4 | 20 | |
| እስማማለሁ | 1 | 4 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 0 | - | |
| አልስማማም | 2 | 4 | |
| ፍጹም አልስማማም | 3 | 3 | |
| ድምር | 10 | 31 | 3.1 |

ውጤቱ አምስት ድጋፍና አምስት ተቃውሞ ሲሆን፣ አማካይ ነጥቡ 3.1 ይመጣል። ከዚህ ስሌት ማጠቃለል የምንችለው አብዛኞዎቹ መምህራን ቋንቋው በመሰናዶ ደረጃ ያለ

አማራጭ እንዲሰጥ እንደሚፈልጉ ነው። ነገር ግን ቋንቋው ያለ አማራጭ ሳይሆን በተማሪዎቹ ምርጫ ትምህርቱ እንዲሰጥ የሚፈልጉ እንዳሉ ከተመዘገበው ውጤት መገመት እንችላለን።

8/ የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትም ሆኑ ኢአፈፊት ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ባላቸው አመለካከት ተመሳሳይ ናቸው።

አዎንታዊ ጥያቄ ነው። አስሩም መምህራን ምላሽ ሰጥተውበታል። ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 1፣ እስማማለሁ 1፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 2፣ አልስማማም 6፣ ፍጹም አልስማማም 0 ሆኖ እናገኛለን። አማካይ ነጥቡ ደግሞ 2.7 ይሆናል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 1 | 5 | |
| እስማማለሁ | 1 | 4 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 2 | 6 | |
| አልስማማም | 6 | 12 | |
| ፍጹም አልስማማም | 0 | - | |
| ድምር | 10 | 27 | 2.7 |

ሃሳቡን የደገፉት ሁለት ሲሆኑ፣ የተቃወሙት ደግሞ ስድስት ናቸው። እንዲሁም መወሰን ያልቻሉት ሁለት መምህራን ናቸው። በዚህ አሃዝ መሠረት አብዛኛዎቹ የመሰናዶ መምህራን በቋንቋው ትምህርት ላይ ባላቸው አመለካከት በአፈፊት ተማሪዎችና በኢአፈፊት ተማሪዎች መካከል ልዩነት እንዳለ ያምናሉ። ይህ ማለት መምህራን በልቅ ጥያቄ ተራ ቁጥር «3» ላይ እንዳስቀመጡት ትምህርቱን በትኩረት የመከታተል አለመከታተል ልዩነት እንጂ፣ በተለይ ከከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውጭ ቋንቋው መሆኑን ሁለቱም ወገኖች ይቃወሙታል።

9/ በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት አላቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

ዐረፍተ ነገሩ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው። ለጥያቄው አሥሩም መምህራን ምላሽ ሰጥተውበታል። ዝርዝር ምላሻቸውን ስንመለከት በጣም እስማማለሁ 0፣ እስማማለሁ 0፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 2፣ አልስማማም 4፣ ፍጹም አልስማማም 4 ሲሆን። አማካይ ነጥቡ 4.2 ነው። ሀሳቡ ምንም ድጋፍ አላገኘም። ባንፃሩ ሃሳቡን የተቃወሙት ስምንት መምህራን ናቸው። አማካይ ነጥቡም በተቃውሞ 4.2 ያሳያል።

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 0 | - | |
| እስማማለሁ | 0 | - | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 2 | 6 | |
| አልስማማም | 4 | 16 | |
| ፍጹም አልስማማም | 4 | 20 | |
| ድምር | 10 | 42 | 4.2 |

በዚህ አሃዝ መሠረት የመምህራትን አቋም እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል:: አብዛኞዎቹ መምህራን የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ አሉታዊ አመለካከት እንደሌላቸው ያምናሉ::

10/ ትምህርቱን ለማሻሻል ዕድል ቢሰጠኝ በአማርኛ ማስተማር መቀጠል አልፈልግም:: ይኸኛውም ጥያቄ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር ነው:: የአስሩም መምህራን ምላሽ ተመዝግቦለታል:: ዝርዝር ውጤቱ ደግሞ በጣም እስማማለሁ 2፣ እስማማለሁ 1፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 3፣ አልስማማም 4፣ ፍጹም አልስማማም 0 ሆኖ አማካይ ነጥቡ 2.9 ነው::

| አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | የተገኘው ውጤት | አማካይ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | 2 | 2 | |
| እስማማለሁ | 1 | 2 | |
| ለመወሰን ያስቸግረኛል | 3 | 9 | |
| አልስማማም | 4 | 16 | |
| ፍጹም አልስማማም | 0 | - | |
| ድምር | 10 | 29 | 2.9 |

በዚህ ውጤት መሠረት ሃሳቡን የደገፉት 3፣ የተቃወሙት 4፣ መወሰን ያልቻሉት 3 ናቸው:: አማካይ ነጥቡም ከ3.0 በታች ያሳያል:: ይህ ማለት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ መምህራን ትምህርታቸውን ለማሻሻል ዕድል ቢሰጣቸው በአማርኛ ማስተማር መቀጠል እንደሚፈልጉ ያመለክታል:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በአማርኛ ማስተማር የሚፈልጉት መምህራን ቁጥር በአንፃራዊ መልኩ ቢበልጥም፣ ቀደም ሲል በትምህርቱ ለፈተና አለመስጠት ሞራላቸውን እንደነካና ስሜታቸውን እንደጎዳ ተመልክተናል:: ይህ ምክንያት

ሊሆን ይችላል መምህራኑን አሉታዊውን ምላሽ እንዲመርጡ የገፋፋቸው ወይም አቋም እንዳይወስዱ ያደረጋቸው፡፡

### 4.3.2. በደረጃ ለሚቀመጡ ጥያቄዎች የተሰጠ ምላሽ

በጽሑፍ መጠይቅ «ለ» (አባሪ «ለ»ን ይመልከቱ) ሥር የተዘረዘሩት ተላውጦዎች ለተማሪዎች «ሠ» (አባሪ «ለ»ን ይመልከቱ) ሥር ከተሰጡት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህን ማድረጉን ያስፈለገው የተማሪዎችንና የመምህራንን ምላሾች ለማነጻጸር እንዲያመች ሆኖ ተብሎ የተደረገ ነው፡፡ ይህንኑን ለማሳካት የመምህራኑ ምላሽ ተጠናቅረው በሰንጠረዥ መልክ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ዝርዝር ውጤቱ ከሰንጠረዥ አሥራ አምስት ማግኘት ይቻላል፡፡ ከሠንጠረዡ ላይ መረዳት እንደሚቻለው በአኩል ነጥብ ከፍተኛውን ነጥብ የያዙት ሁለት ተላውጦዎች ናቸው፡፡ እነሱም «ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ» እና «በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚደረጉ ቅስቀሳዎች» የሚሉት ናቸው፡፡ በመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኙት ደግሞ «ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት መጽሐፍት ይዘትና አቀራረብ ሳቢ አለመሆን» እና «የመምህራን ብቁ ሆነው አለመገኘት» ናቸው፡፡ ቋንቋው በመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ የሚለው በተማሪዎች ምላሽ ላይም ከችግሩ ክብደት አንጻር በአንደኛ ደረጃ (ሠንጠረዥ ዘጠኝን ይመልከቱ) ላይ እንደተመረጠ ይታወሳል፡፡ ከአንዳንድ የመገናኛ ብዙሃን ጀምሮ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ግለሰቦች ወዘተ ቋንቋውን በማጥላላትና ስሙን በማጉደፍ በስውር የሚደረጉት ቅስቀሳዎች ቀላል እንዳልሆነ ከመምህራኑ ምላሽ ብቻ ሳይሆን ከተማሪዎችም ምላሽ (ሠንጠረዥ ዘጠኝ ይመልከቱ) መገንዘብ እንችላለን፡፡ ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት አንዳንድ የየትምህርት ቤቶቹ ማህበረሰብ አባላት ወርወር የሚያደርጉአቸው አባባሎች ይህንኑ ያረጋግጣሉ፡፡

ሠንጠረዥ አሥራ አምስት፡- መምህራን በደረጃ ለሚቀመጡ ተላውጦዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ነው፡፡

| በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ ተብለው በተዘረዘሩ ተላውጦዎች | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት መጽሐፍት ይዘትና አቀራረብ ሳቢ አለመሆን | | | | | 1 | 1 | 5 | 3 |
| ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ | 3 | 4 | 1 | 1 | | 1 | | |
| ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛ ቋንቋን እንደ ጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበራከት | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | | | |
| የመምህራን ብቁ ሆኖ አለመገኘት | | | | | | 2 | 3 | 5 |
| ለአብዛኛዎቹ ክልሎች ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና ለራሳቸው ቋንቋ ቅድሚያ መስጠታቸው | | | 3 | 3 | 1 | 1 | | 1 |
| በብሔራዊ ፈተና የአማርኛ ውጤት አማራጭ ውስጥ መግባቱ | 1 | | 1 | 3 | 4 | | | 1 |
| በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚደረጉ ቅስቀሳዎች | 3 | 4 | 1 | 1 | | 1 | | |
| ወላጆች፣ ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆን | 2 | | 1 | | 2 | 3 | 2 | |

### 4.3.3. ልቅ ሆነው የየግል አስተያየቶች የተሰጡባቸው ጥያቄዎች

በልቅ መልክ ለመምህራን የቀረቡት ጥያቄዎች ሶስት ናቸው:: የመጀመሪያው ጥያቄ ተማሪዎች የቋንቋውን ትምህርት በከፍተኛ ንሺ. ወደሚመሩበት ደረጃ ለማሸጋገር ምን ምን እርምጃዎች ቢወሰዱ ይመረጣል? ሁለተኛው ጥያቄ የወቅቱን በተለይ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ጋር አያይዘው የሚሰነዘር አሉታዊ አባባልን የሚመለከት ነው:: የመጨረሻው ጥያቄ ቋንቋውን አስመልክቶ በተማሪው ላይ የሚንፀባረቀው አመለካከት በአፈፊት መሆን/አለመሆን መካከል ልዩነት ይኖረው ይሆን? የሚል ነው:: በእነዚህ ሶስት ጥያቄዎች ላይ ከመምህራን የተሰጡት አስተያየቶች ወይም መልሶች ተሰብስበውና ተጠናቅረው በሰንጠረዥ መልክ ቀርበዋል:: ስለዚህ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፣ አስራ ሰባትና አስራ ስምንት ላይ የቀረቡ ሃሳቦችን ይመልከቱ::

1/ ተማሪው ትምህርቱን እንደሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ለምሳሌ እንደ እንግሊዝኛ እና ሒሳብ በከፍተኛ ተነሳሽነት ወደሚማሩበት ደረጃ ለማሸጋገር ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ይላሉ?

ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት አስተያየቶች ከዚህ በታች በሰንጠረዥ አስራ ስድስት ላይ ቀርበዋል::

| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ ቢካተት፣ | 6 |
| 2 | ክፍለ ጊዜው ቢያንስ በሳምንት ሶስት ቢሆን፣ | 5 |
| 3 | እንደ የፌዴራል የሥራ ቋንቋነቱ በክፍለ ጊዜም ሆነ በመምህራን በኩል እንደ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ትኩረት ቢሰጥ፣ | 4 |
| 4 | ለመምህራን ስለቋንቋ ማስተማር አልፎ አልፎ ስልጠና ቢሰጥ፣ | 3 |
| 5 | በብሔራዊ ፈተና ላይ የአማርኛ ቋንቋ ውጤት በዋናነት ቢታይ፣ | 3 |
| 6 | በቋንቋው ላይ የሚንፀባረቁት አላስፈላጊ አመለካከቶች መለወጥ አለባቸው፣ | 2 |
| 7 | ክልሎች ቋንቋውን ባያጥላሉ፣ | 2 |
| 8 | በICT በሚተላለፈው ትምህርት ውስጥ አማርኛም ቢካተት፣ | 2 |
| 9 | ለቋንቋው መንግሥት ልዩ ትኩረት ማድረግ አለበት፣ | 2 |
| 10 | በቋንቋው ላይ የሚደረገውን ጥላቻ ማስወገድ | 2 |
| 11 | የማስተማሪያ መጽሐፍት ይዘቶች አዝናኝና አስተማሪ ቢሆኑ፣ | 2 |
| 12 | አሉታዊ አመለካከት የያዙ ወገኖች ይህን አመለካከታቸውን አስወግደው ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዲይዙ ጥረት ቢደረግ፣ | 2 |
| 13 | የቋንቋው ባለቤቶችም ቢሆኑ በባዶ ከመኩፈስ ይልቅ አክብሮ ለመማርና ለማወቅ ዝግጁ መሆን አለባቸው:: | 1 |
| 14 | በቋንቋው ችሎታ ያላቸውና ለሙያው ፍቅር ያላቸውን መምህራን በጥሩ ደመወዝ መቅጠር:: | 1 |

አጥኚው በምልከታው ወቅት ከፍተኛ የክፍለ ጊዜ እጥረት መኖሩ ብቻ ሳይሆን የክፍለ ጊዜዎቹ አመቺ አለመሆን ጭምር ችግር እንዳለ ተመልክቷል። ይኸውም አብዛኛው የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከ4-6 ሲሆን፣ ከስፖርት ሚዳ መልስ ነው።

2/ አንዳንድ ተቆርቋሪዎች ወይም አጥላዮች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያነት አለመስጠቱን አስታክከው አንድ የሚሉት አባባል አለ።

"እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" ይህን አባባል እንዴት ያዩታል?

ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት መልሶች ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ አሥራ ስባት ላይ ተዘርዝረዋል።

| ተ.ቁ | የተሰጡት መልሶች | የድግግሞሽ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ምሳሌያዊ አነጋገሩ በእርግጥ ለዚህ ሁኔታ ተገቢ ነው እላለሁ። ተማሪው ቀድሞውኑ ትኩረት ያልሰጠበትን ጉዳይ አሁን ደግሞ ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ሁኔታውን የሚያባብሰው መሆኑ እሙን ነው። | 1 |
| 2 | «አባቱን አያውቅ አያቱን ይናፍቅ» ይላሉ አበው። በመጀመሪያ ለራሳችን ቋንቋ ክብር ብንሰጥ፣ ብናዳብረው የተሻለ ነው፤ ቋንቋችን ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያነት ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ደረጃም እንዲነገር ማድረግ ይቻላል፤ የሰዋህሊ ቋንቋን ማየት ይቻላል። | 1 |
| 3 | ቋንቋ ከፖለቲካ ጋር ባይያያዝ ጥሩ ነው። የፌዴራሉ ቋንቋ እንደመሆኑ ቋንቋው ቢያድግ ጥሩ ነው፤ ተረቱን አልቀበለውም። | 1 |
| 4 | ይህ አባባል በቋንቋው ትምህርት ላይ የመገለል ወይም ተወት ተወት ማድረግን ይመለከታል። በዚህ አንፃር እውነት ሊሆን ይችላል። በእውነታዊ አንፃር ግን ቋንቋው አገልግሎት መስጠቱን ቅንጣትም የቀነሰው ነገር የለም። | 1 |
| 5 | ትክክል ነው። | 1 |
| 6 | እውነታቸውን ነው። ምክንያቱም የክፍለ ጊዜ ስርጭቱን እንኳ ከአራትና አምስት ወደ ሁለት ነው የወረደው። እንዲያውም በማታ ትምህርት በሳምንት አንድ ፔሬድ ብቻ (9ኛ ክፍል) ነው የሚሰጠው ቀስ በቀስ ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል የሚል ስጋት አለ። | 1 |
| 7 | ይህ አባባል ከመጥበብና ከቀኖናዊነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ የቋንቋውን የዕድገት ደረጃ አለመረዳት ነው። | 1 |
| 8 | በአጥላዮች ዘንድ ድሮውንም አልተወደደም። የማጥላያ ምክንያት ተገኘ ሲሉ ዱሮውንም የማይወዱት ደግሞ ተገላገልን እያሉ መሆኑን ለማመልከት ይመስላል። | 1 |
| 9 | ለነገሩ አማርኛ በብሔራዊ ደረጃ ያደገ ቋንቋ ነው። ለፈተና አለመቀረቡ በተማሪዎችና በወላጆች ዘንድ ለውጥ አምጥቶ እንደሆነ እንጂ በመምህራን ዘንድ ምንም ለውጥ አይታይበትም። | 1 |
| 10 | እውነታቸውን ነው። ቢቻላቸው ቋንቋው ከሀገሪቱ ቢጠፋላቸውም (አይቻላቸውም እንጂ) የሚመርጡም አይታጡም። እየተዳከመለት እንዲሄድ የሚፈልጉትን ለመውቀስ ፈልገው ነው። | 1 |

3/ በአዎንታዊ ጐኑም ሆነ በአሉታዊ ጐኑ ለቋንቋው አፈፌት በሆኑ ተማሪዎችና በኢአፈፌት በሆኑ ተማሪዎች መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለ ይመስልዎታል? ካለ ልዩነቱ እንዴት ይንፀባረቃል?

ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ አሥራ ስምንት ለዚህ ጥያቄ አሥሩም መምህራን የሰጡትን ምላሽ ዝርዝር ያሳየናል።

| ተ.ቁ | የተሰጡት አስተያየቶች | የድግግሞሽ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | እንዲያውም አፈፌት ከሆኑት ይልቅ ኢአፈፌት የሆኑት አማርኛን በጥንቃቄ ይማራሉ፣ ጥያቄ ይጠይቃሉ። አፈፌቶች ስለሚናገሩት ብቻ ቋንቋውን የሚያውቁት ይመስላቸዋል። | 2 |
| 2 | አዎን! አፈፌት የሆኑት ስለሚናገሩት የሚያውቁት እየመሰላቸው ብዙም ትኩረት አይሰጡም። ሌሎቹም (ኢአፈፌቶች) ግን ልክ እንደሌላው ቋንቋ ስለቋንቋው የማወቅ ጉጉት አላቸው። በክፍል ውጤታቸውም ኢአፈፌት የሆኑት የተሻሉ ናቸው። | 1 |
| 3 | የጎላ ልዩነት ያለ አይመስለኝም። | 1 |
| 4 | ብዙም ልዩነት የላቸውም። ኢአፈፌቶች የቋንቋ ችሎታቸው እየቀነሰ ስለመጣ ውጤታቸው እንዳይወርድ የጭንቀት ስሜት ይታይባቸዋል። | 1 |
| 5 | በአዲስ አበባ ይህ አይነቱ ችግር ሲከሰት አላስተዋልኩም። | 1 |
| 6 | ይህን የሚመለከት ጥናት ስላላካሄድኩ ለመግለጽ ያስቸግረኛል። ኢአፈፌት የሆኑት ተማሪዎች ይበልጥ ሲቆረቆሩ ከማየት በስተቀር። | 1 |
| 7 | አዎን! በአማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎች በቋንቋቸው ሲማሩ አማርኛን ያጥላሉታል፤ በቋንቋው ላይ ጥላቻ ስለሚያሳድሩ ለመከታተል ፍቃደኛ አይደሉም። | 1 |
| 8 | አፈፌት የሆኑ ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት የማይሰጡበት አንዱ ምክንያት «እናውቃለን» የሚል ባዶ ጉራ ሲሆን፣ ኢአፈፌት የሆኑት ቋንቋችን አይደለምና ምን ያስጨንቀናል የሚል አመለካከት ይታያል። | 1 |
| 9 | ቋንቋን በቋንቋነቱ ሳይሆን እንደ ዘር መለያ ስለሚቆጥሩት ከንቀት ማነስ የሚንፀባረቅ ነው። | 1 |

ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰነዘሩትን አስተያየቶች ወይም መልሶች ጠቅለል ባለ መልክ ስንመለከት የሚከተለውን ይመስላል።

ለአንደኛው ጥያቄ በሠንጠረዥ አሥራ ሥድስት ላይ ከቀረቡት አስተያየቶች መካከል አንዳንዶቹ ቀላልና ችግሮቹን ለመፍታት ያን ያህል ከባድ አይደሉም። ለምሳሌ ለመምህራን በየጊዜው የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መስጠትና ብቃታቸውን ከፍ ማድረግ ወይም የሚዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ለተማሪው በሚመች መልክ ማዘጋጀቱ ለጉዳዩ ትኩረት የመስጠት ነገር እንጂ ያን ያህል ችግሩን ለመቅረፍ ራስ ምታት የሚያስይዝ ነገር አይደለም። በሌላ ወገን የቀረቡት አስተያየቶች ግን ከመንግሥት ጀምሮ እስከ ታች የህብረተሰቡ ክፍል ድረስ የሚንፀባረቁ፣ በጣም ስር እየሰደዱ የመጡ የቋንቋው ነገር ከፖለቲካ ጋር እርስ በርስ የተተበተቡበት ጉዳይ ነው። ፖሊሲን የሚመለከቱ፣ የህብረተሰቡን አስተሳሰብ መለወጥ የሚሹ ወዘተ ጉዳዮችን ያካተተ ነው። በመሆኑም ዘላቂ መፍትሔ ላይ ለመድረስ የአንድ ወገን ሩጫ እልባት የሚሰጠው ሳይሆን መንግስት ከፖሊሲው ጋር፣ ከኅብረተሰቡ ጋር በመሆን ሊቀርፈው የሚችለው ጉዳይ ነው።

ለሁለተኛው ጥያቄ በሠንጠረዥ አሥራ ሰባት ላይ የተሰጡት መልሶች የመጀመሪያው ጥያቄ ነፀብራቅ ናቸው። ሃሳቡ የሚያጠነጥነው ቋንቋው በየጊዜው ችላ ችላ፣ ተወት ተወት፣

እየተደረገ መምጣቱን ነው መምህራን የሚገልጹት፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በትምህርት ቤት አስተዳደሮች አካባቢ በመጠኑም ቢሆን እንደሚንፀባረቅ በምልከታ ወቅት ለመከታተል ተችሏል፡፡ በተራ ቁጥር «1» ላይ የተሰነዘሩት አስተያየቶች መፍትሄ ካገኙ ይኸኛውም ይፈታል፡፡

በሶስተኛው ጥያቄ በተማሪዎች አስተያየት (ሠንጠረዥ አሥራ አራት ይመልከቱ) ሥር እንዳየነው አፈፃፀሞች ቋንቋውን እናውቀዋለን ብለው አንዳንዶቹ ለቋንቋው አጉል ንቀት እንደሚያሳዩ፣ ኢአፈፃፀሞች ግን በትኩረት እንደሚከታተሉ ነው፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ በቋንቋው ላይ ባላቸው አመለካከት ግን ልዩነት እንደሌላቸው ያሳየናል፡፡

## 4.4. በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተጠቀሰው አጥኚው ቃለ መጠይቅ ያካሄደው ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ወላጆች ጋር ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል እነዚህ ተጠያቂዎች ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የሰጡአቸውን ምላሾች አንድ ባንድ የምንመለከት ይሆናል፡፡

### 4.4.1. የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተማሪዎች ቁጥር አምስት ነው፡፡ ለእያንዳንዳቸው የቀረቡት ጥያቄዎች ሰባት ሲሆኑ፣ የተጠየቁትም ደግሞ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ነው፡፡ (አባሪ «ሐ»ን ይመልከቱ)፡፡

1/ የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ምን አይነት አመለካከት አላቸው?

ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በሁለት ይከፈላል፡፡ አራቱ ተጠያቂዎች እንደሚገኘውም ትምህርት የምናየው ቢሆንም፣ ያደግንበትና የምናውቀው ስለሆነ፣ በተለይ ለተቋም ለመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ከታወቀ ወዲህ ግን ከሌሎች አንጻር የቋንቋውን ትምህርት ትንሽ ዝቅ አድርገው እንደሚመለከቱ ገልጸዋል፡፡ አንደኛዋ ግን አመለካከታቸው በጣም ቆንጆ እንደሆነ ገልጻለች፡፡

2/ አማርኛ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱን በክፍሉ ውስጥ በሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል ብለህ/ሽ ትገምታለህ/ ትገምቻለሽ?

ለሁለተኛው ጥያቄ አምስቱም የሰጡት መልስ ተመሳሳይ ነው፡፡ «አዎ አሳድሯል» ነው፡፡ የሰጡትም ምክንያት ለምንፈተናቸው የትምህርት ዓይነቶች ነው ቅድሚያ የምንሰጠው፣ ለፈተና ስለማይመጣና ከመምህራኑም ጋር የምንገናኘው በሳምንት ለሁለት ክፍለ ጊዜያት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ትኩረት እንዳንሰጠው አድርጎናል፡፡

3/ አማርኛ ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱን ትደግፋለህ/ሽ? ለምን?

እንደ ሁለተኛው ሁሉ ለሶስተኛውም ጥያቄ ምላሻቸው ተመሳሳይ ነበር፤ «አልደግፈውም»:: የሰጡት ምክንያት ሁለት ናቸው:: ለቋንቋው ካላቸው ፍቅር እንጂ'ና ለፈተናው የሚመጣ ቢሆን ኖሮ የተሻለ ቋንቋውን እናውቀው ነበር መልሳቸው:: ከዚህ በተጨማሪ የጽሁፍ መጠይቅ ላይ ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ነበሩ:: አፈፊቶች በተ.ቁ «5.1» (አባሪ «ሀ»ን ይመልከቱ) «አማርኛ አፌን የፈታሁበት ቋንቋ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ቢሰጥ ደስ ይለኛል» ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተመዘገበው ውጤት 27.7% ሲቃወሙት፣ 58.8% ደግሞ ደግፈውታል:: እንዲሁም ለኢአፈፊት ተማሪዎች በተራ ቁጥር «5.3» ላይ «አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ አስደስቶኛል» ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተገኘው ውጤት 28.4% ሃሳቡን ሲደግፉት 52.6% ግን ተቃውመውታል:: እነዚህ ሁሉ መረጃዎች የሚያሳዩን የቋንቋው ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ቢሰጥ ተማሪዎቹ እንደሚደግፉ ነው::

4/ በክፍል ውስጥ የሚንፀባረቁት አዎንታዊ/አሉታዊ አመለካከት በቋንቋው አፈፊት ለሆኑትና አፈፊት ባልሆኑት መካከል ልዩነት ይታያል?

የአራተኛው ጥያቄ ምላሽ በሁለት መልክ ሊታይ የሚችል ነው:: ሁለቱ ምንም ልዩነት የለም ብለው ሲመልሱ ሶስቱ ደግሞ ኢአፈፊቶች ስለቋንቋው ለማወቅ ከአፈፊቶች የበለጠ እንደሚያጠኑና ትኩረት እንደሚሰጡት ነው የገለጹት::

5/ ተማሪው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ ያልሆነ ወይም አሉታዊ አመለካከት እንዲቀረጽባቸው ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ምን ምን ይመስልሃል? ይመስልሻል?

ለአምስተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች የሚከተሉት ናቸው::

- ስለቋንቋው ካላቸው የግንዛቤ ጉድለት ቋንቋውን በጥላቻ መልክ ማየት፣
- ኅብረተሰቡ ቋንቋውን «ወንዝ የማያሻግር» እያሉ ስለሚያጥላሉት፣
- ተማሪዎች ለፊልምና ቪዲዮ ካለቸው ፍቅር የተነሳ እንግሊዝኛ ስለሚስባቸው የሚሉት ናቸው::

6/ ለተማሪዎች በሙሉ ፍላጎትና ፍቅር የቋንቋውን ትምህርት እንዲከታተሉ ምን ቢደረግ ይሻላል?

ለዚህ ጥያቄ በተሰጠው ምላሽ አንድ ተማሪ በዚሁ ይቀጥል ሲል፣ የቀሩት ደግሞ ቲያትሮች፣ ምልልሶች፣ ትረካዎች፣ አባባሎች ወዘተ በብዛት ቢካተቱበት ተማሪውን ከመሳቡ ባሻገር ያሳትፋል በማለት መልሰዋል::

7/ «ብዙ ቋንቋ መቻል ከብዙ ኅብረተሰብ ክፍል ጋር ያግባባል» የሚለውን አባባል እንዴት ታይዋለሽ? ታየዋለህ?

ሰባተኛውን ጥያቄ ሁሉም በጣም እደግፋለሁ፣ በጣም ትክክል ነው በማለት ከመለሱ በኋላ ምክንያታቸውንም ገልጸዋል። የተለያዩ አካባቢዎች ለሥራ፣ ለጉብኝት ለተለየዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሲኬድ በቀላሉ ከኅብረተሰቡ ጋር ለመግባባት ያስችላል።

ተማሪዎቹ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽና ያስቀመጧቸው ምክንያቶች በአብዛኛው የሚደገፉና አሳማኝ ሃሳቦች ናቸው። አንዳንዶቹ ግን ለመቀበል ያስቸግራሉ። ታሪኩ (1988) ተማሪውም ሆነ ኅብረተሰቡ የራሱን ቋንቋ ንቆ በባዕድ ቋንቋ ማምለኩ አግባብ እንዳልሆነ የትችት ሃሳቡን አስፍሮ ነበር። አሁንም ይህ ሁኔታ በተማሪዎችና በኅብረተሰቡ እየተንፀባረቀ ሳይሆን አይቀርም። እራሳችንን ወደን ሌላውንም መውደድ፣ ማድነቅ የወግ ነው። ነገር ግን የራስን ወይም እራስን አስጠልቶ ሌላውን ማንቆለጳጳሱ እራስን እንደመካድ ይቆጠራል። ስለዚህ ስለአገርኛና የውጭ ቋንቋ ተማሪውም ሆነ ኅብረተሰቡ ያላቸው የተሳሳተና ቁንጽል እይታ እልባት ሊፈለግለት የሚገባው በሽታ ነው የሚል አስተያየት ያስነዝራል።

### 4.4.2. የመምህራን ቃለ መጠይቅ

በዳግማዊ ምኒልክ፣ በመድሐኒአለም፣ በቢሾፍቱና ሐዋስ የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ከአራቱ ጋር የቃለ መጠይቅ ምልልስ አጥኚው አካሂዶ ነበር። ለመምህራን የቀረቡት የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች (አባሪ «መ» ይመልከቱ) አምስት ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጡት መልሶች በመቀጠል የምንመለከት ይሆናል።

1/ የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

- የቋንቋውን ትምህርት የመማር ፍላጎት አላቸው ወይም ነበራቸው፤ ነገር ግን የቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተት ትምህርቱን በቸልታ እንዲከታተሉት አድርጎአቸዋል።

2/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ ከታወቀ ወዲህ በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪዎች ያመጡት የአመለካከት ለውጥ አለ?

ለውጥ አለ። ዋና ዋናውና ተጠቃሽ የሆነው፡-

- ትምህርቱን አለመከታተል፣
- የክፍልም ሆነ የቤት ሥራ ከልብ አለመስራት፣
- ወደሌሎች ትምህርቶች ማድላት

ይህ ሁኔታ ደግሞ የመምህራኑን ሞራል ይጎዳል፣ ስሜት ይነካል።

3/ ለቋንቋው ትምህርት ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ከክልል ክልል፣ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ሊለያዩ የሚችሉበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ። ለመሆኑ በእናንተ ት/ቤት ጉልህ የሆኑ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው? ከምንስ የመነጩ ናቸው?

- በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ፣
- ተማሪው እንግሊዝኛን የስልጣኔ መለኪያ አድርጎ መውሰዱ፣
- ከፊልም እና ቪዲዮ ጋር የተያያዘ ትልቅ የባህል ወረርሽኝ የገባ ይመስላል። ይህ ሁኔታ መንግስት መፍትሄ ካላፈላለገለት የሃገሪቷ ትልቅ የራስ ምታት እንደሚሆን ነው። እራስን አስጠልቶ ሌላውን የመናፈቅ አባዜ!

4/ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸውና በትምህርቱ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት ምን ቢደረግ የሚሻል ይመስሎታል?

- የመማሪያ መጻሕፍቱ አሰልቺነት፡- በተለይ የመልመጃዎቹ ድግግሞሽና ብዛት ስሜቱ እየቀዘቀዘ ከመጣው ተማሪ ጋር ተዳምሮ ትልቅ ችግር ነው። ስለዚህ እያዝናና የሚያስተምር፣ ያልተንዛዛ መማሪያ መጽሐፍት ቢዘጋጅ፣
- ከንባብ ይልቅ በንግግርና በጽሕፈት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ቢበራከቱ የሚሉ ናቸው።

5/ ይህ አዎንታዊ/አሉታዊ አመለካከት ከተማሪዎች የቋንቋው አፈፊት/ኢአፈፊት አንፃር ልዩነት ይታይበታል?

- ይህ ችግር በአዲስ አበባዎቹ ት/ቤቶች እንደ ችግር እንደማይንጸባረቅ፣
- የመጥላት አለመጥላት ሳይሆን፣ ኢአፈፊቶች እሳሳት ይሆን? በማለት በራስ ካለመተማመን የተነሳ አንደንዴ እራሳቸውን ከተሳትፎ የማግለል ሁኔታ ይታያል።

ከጥያቄዎቹ በኋላ አስተያየት ተጠይቀው መምህራኑ በአብዛኛው ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ከአስተያየቶቹ ዋና ዋናዎቹ፡-

- ለመምህራን በየጊዜው የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ቢሰጥ፣
- የማጣቀሻ መጻሕፍት በየትምህርት ቤቱ እንደልብ ቢገኙ ተማሪው ይገለገልበታል፣ ለመምህራኑም ሥራ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።
- ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተናነት ቢሰጥ፣ ቢያንስ ቢያንስ የአጠቃላይ ችሎታ ምዘና (Aptitude) ውስጥ 20 ጥያቄዎች ያህል እንኳን ቢካተቱ፣
- የመማሪያ መጻሕፍቱ በየጊዜው ቢሻሻል፣

ወዘተ የሚሉ ናቸው።

እንደተማሪዎቹ ሁሉ መምህራኑም ሃሳባቸውን የሰነዘሩት ከተቆርቋሪነት አንፃር በመሆኑ አብዛኛዎቹ ሃሳቦች ተገቢዎች ናቸው። በተለይ መምህራን ጥረው ተጣጥረው በሚያስተምሩበት ወቅት ሁኔታው «ያቀረቡለትን ካልበሉለት. . .» አይነት ሲሆንባቸው ስሜታቸው እንደሚነካ ግልጽ ነው። ሌላው መምህራኑ ያተኮሩበት ነጥብ በምንባቦቹ ወይም በየምዕራፉ ከምንባብ ነክ ጥያቄዎች ጀምሮ በየክሂሎች፣ እውቀቶች ተሸንሽነው የቀረቡት መልመጃዎች ሲደማመሩ በጣም እንደሚበዙና ተማሪዎቹ ገና ለገና እንዳዩት የመስራት

ስሚታቸው እንደሚዳፈን ነው የጠቆሙት። የመማሪያ መጻሕፍትን አስመልክቶ «በየጊዜው ቢሻሻል» የሚል አስተያየት አንድ መምህር ሰንዝረዋል። በእርግጥ መጻሕፍቱ ከወቅቱ ጋር እንዲሄድ ወይም እንዲራመድ መሻሻል እንደሚገባቸው ይታመናል። ይህ ማለት ግን መጻሕፍቱ የተወሰኑ አመታት ሥራ ላይ ውለው ካልተገመገሙ ጠንካራና ደካማ ጐናቸው ሳይፈተሽ መሻሻል የሚለው ላይሰራ ይችላል። ለምሳሌ እነዚህ የመሰናዶ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ሥራ ላይ መዋል የጀመሩት የ11ኛ ክፍሉ በ1994፣ የ12ኛ ክፍሉ ደግሞ ዘንድሮ ገና ሁለተኛ ዓመቱን መያዙ ነው። ስለዚህ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ማድረግ የሚቻለው ነገር በመጽሐፍቱ ላይ አስተያየቶችን ማንሳት እንጂ ለማሻሻል ዘግይታችኋል የሚለው ስሜት አያስኬድም።

## 4.4.3. የተማሪ ወላጅ ቃለ መጠይቅ

ከምስራቅ ሸዋ ዞን ሁለት፣ ከአዲስ አበባ አንድ በድምሩ ከሶስት የተማሪ ወላጆች ጋር ቃለ መጠይቅ ተካሂዷል። ለእያንዳንዱ ወላጅ የቀረቡ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ በቁጥር ደግሞ አራት ናቸው (አባሪ «ሠ»ን ይመልከቱ)። ከዚህ በመቀጠል ወላጆች ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡትን ምላሽና አስተያየት እንመለከታለን።

1/ በመሰናዶ ደረጃ ልጅዎ አማርኛ መማሩን ምን ያህል ይደግፉታል?

ለመጀመሪያው ጥያቄ የሶስቱም መልስ ተመሳሳይ ነው። «እደግፋለሁ» የሚል ነው። እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን ያለበት ነገር አለ። ይኸውም የአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎች አማርኛን የሚማሩት ያለአማራጭ ሲሆን፣ የምስራቅ ሸዋዎቹ ግን ከኦሮምኛ እና ከአማርኛ አንዱን መርጠው ነው። ሁለቱም የምስራቅ ሸዋ ዞን ተጠያቂ ወላጆች ኦሮሞ ሲሆኑ፣ በልጆቻቸው አማርኛን መርጦ መማር ቅሬታ እንደሌላቸውና እንዲያውም እንደሚደግፉት ነው የገለፁት።

2/ «ብዙ ቋንቋ መቻል ከብዙ ኅብረተሰብ ክፍል ጋር ለመግባባት ያስችላል» የሚለውን አባባል እንዴት ያዩታል?

እንደመጀመሪያው ጥያቄ ሁሉ ለሁለተኛውም ጥያቄ ተመሳሳይ መልስ ነው የሰጡት። በጣም ተቀባይነት ያለው አባባል እንደሆነ እነርሱ እራሳቸው ዕድሉን ቢያገኙት የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቋንቋ መማር ፍላጎታቸው እንደሆነ ገልፀዋል።

3/ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና እንደ እንግሊዝኛ እና ሒሳብ የአማርኛ ቋንቋ ቢሰጥ ይደግፋሉ? ለምን?

የሶስተኛውንም ጥያቄ ሁሉም በተመሳሳይ መልኩ ይደግፋሉ። ምክንያታቸው ደግሞ፦

- የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ፣

- በቋንቋው ለመቀጠል ለሚፈልግ ትምህርቱን በጥልቀት እንዲማር ስለሚያደርገው የሚሉት ናቸው፡፡

4/ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት እንዳይኖር የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እርስዎ ካልዎት ልምድ አንዳንዶቹን ቢጠቅሱልኝ፡፡

ለአራተኛው ጥያቄ የተሰጡት መልሶች እንደሌሎች በአንድ ቃል ወይም አባባል አልተጠቃለሉም፡፡

- ቋንቋውን ከመደብ ወይም ከዘር ጋር የማያያዝ ሁኔታ የሚለው ከተሰጡት ምላሾች አንዱ ነው፡፡ ከአገላለጻቸው ለመረዳት እንደተቻለው ገዢ መደብ አማራ ወይም ትግሬ ቢሆን፣ አማርኛን ከአማራ ገዢ ጋር አያይዘው የመጥላት፣ ትግርኛን ከትግሬ ገዢ ጋር አያይዘው የመጥላት ሁኔታ እንዳለ፣
- በመርህ ደረጃ አንድ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ አይበልጥም/አያንስም፡፡ ይህንን እውነታ ወደ ጐን በመተው የአንዳንድ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አጉል መኩራስ፣ በእነርሱ አይን ቋንቋውን የመጥላት ሁኔታ ይንፀባረቃል፡፡

በመጨረሻም በአንድ ተማሪ ወላጅ የተሰጠው አስተያየት አማርኛ ለወደፊቱ እንደ አንድ ወሳኝ ትምህርት ቢያዝ እንደሚደግፉት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## 4.5. በቃለ መጠይቅ ከተማሪዎች፣ ከመምህራንና ከተማሪ ወላጆች የተገኙት መረጃዎች ንጽጽር፡፡

ለማነጻጸሪያነት ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

4.5.1. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

4.5.2. ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱን ከመደገፍ/ ከመቃወም አንፃር፣

4.5.3. የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ በክፍሉ ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ አለ ወይ?

በእነዚህ ነጥቦች ላይ ተጠያቂዎቹ ምን ብለው ነበር? ቀጥለን የምንመለከተው ጉዳይ ነው፡፡

### 4.5.1. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

ይህ ነጥብ ከተማሪ ወላጅ ይልቅ መምህራንና ተማሪዎችን የሚመለከት በመሆኑ የሁለቱን ምላሽ እናነፃጽራለን። ተማሪዎቹ «የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ምን አይነት አመለካከት አላቸው?» (አባሪ «ሐ»ን ይመልከቱ) ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አዎንታዊ ቢሆንም በተለይ ለተቋም የመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ከታወቀ ወዲህ ግን ያ ሁኔታ እየተለወጠ መምጣቱን ነው የገለጹት። መምህራንም በበኩላቸው «የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል» (አባሪ «መ»ን ይመልከቱ) ተብሎ የቀረበላቸው ተመሳሳይ ጥያቄ «የቋንቋውን ትምህርት የመማር ፍላጎት አላቸው ወይም ነበራቸው፣ ነገር ግን የቋንቋው ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተት ትምህርቱን በቸልታ እንዲከታተሉት አድርጎአቸዋል» የሚል ነበር። በተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን የተሰጡት መልሶች ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው፣ ነገር ግን ቋንቋው ከፈተና ውጭ በመሆኑ ምክንያት የተማሪውን አመለካከት እያስለወጠ እንደመጣ ነው።

### 4.5.2. ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱን ከመደገፍ/ ከመቃወም አንፃር፣

ሁለተኛው የማነፃፀሪያ ነጥብ ወላጆችንም የሚያካትት ነው። ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ ለቀረበላቸው ጥያቄ (አባሪ «ሐ»ን ፣ «መ» እና «ሠ»ን ይመልከቱ) መልሳቸው ቋንቋው በተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ ባለመካተቱ ቅር መሰኘታቸውንና ለወደፊቱ የመሰጠት ዕድሉን ቢያገኝ በጣም እንደሚደግፉት ነው ያረጋገጡት።

4.5.3. የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት ባለመሰጠቱ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ አለ ወይ?

ይኸኛውም ነጥብ ተማሪዎችንና መምህራንን ብቻ የሚመለከት ነው። በዚህ ነጥብ ላይ ሁሉም ተማሪዎች የሰጡት መልስ «አዎ አሳድሯል» የሚል ነው። መምህራኑም «በተማሪዎቹ ላይ ለውጥ አለ» ነው ያሉት። በምልከታ ወቅት ለውጥ መኖሩን የሚያሳዩ ሁኔታዎችን ለመታዘብ ተችሏል። ጥቂቶቹን መጥቀስ ካስፈለገ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለትምህርቱ የሚሰጡት ከበሬታ ያን ያህል ስለሆነ መጽሐፍ፣ ደብተር ወዘተ በአግባቡ ይዞ በመምጣት መምህሩን በጉጉት የመጠባበቅ ሁኔታ የጎላ አለመሆን፣ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በወጉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ከመፈለግ ይልቅ ወዲህም ወዲያም ተብሎ ክፍለ ጊዜው እንዲባክን መፈለግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ስለዚህ ቋንቋው ከተቋም የመግቢያ ፈተናነት መቅረት በመማር ማስተማሩ ላይ መጥፎ ጥላ እንደጣለበት ሁለቱም ወገን ተስማምተውበታል።

# ምዕራፍ አምስት

## አጠቃላይ ግኝትና የመፍትሄ ሃሳብ

በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዋና አላማ አመለካከት በመማር ማስተማር ሂደትና ውጤት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖችን ማሳየትና በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ተውላጦችን ማመልከት ነው፡፡ ይህንን አጠቃላይ የሆነ አላማ ከግብ ሊያደርሱና ለመሠረታዊ ጥያቄዎቹ ምላሽ ሊያስገኙ ይችላሉ ተብለው የተነደፉት ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመሰናዶ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ተቋሞች ለመግቢያ በሚሰጠው ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ተማሪው ለቋንቋው ባለው አመለካከት ላይ ለውጥ አስከትሎ እንደሆነ ማረጋገጥ፣
2. ይህ በተ.ቁ. "1" ላይ የተጠቀሰው ሃሳብ ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊትና ኢአፈፊት በሆኑት ተማሪዎች መካከል ልዩነት ያሳይ እንደሆነ ማረጋገጥ፣
3. የቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋሞች የመግቢያ ፈተና ላይ አለመሰጠቱ የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ላይ ያሳደረው አሉታዊ ስሜት ካለ ማረጋገጥ፣
4. ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ተላውጦችን ለይቶ ማሳየት ናቸው፡፡

እነዚህ የተተለሙትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ አራት አብይ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ሀ/ በቋንቋና በቋንቋ ትምህርት አመለካከት ዙሪያ የተሰሩ የውጭና የአገር ውስጥ ጥናቶች ተከልሰዋል፡፡

ለ/ መሠረታዊ ጥያቄዎቹን ሊያስመልሱ የሚችሉ የጽሁፍ መጠይቆች ተዘጋጅተው፡-

- ለቋንቋው አፈፊት እና ኢአፈፊት በሆኑት ተማሪዎች፣
- ለቋንቋው አፈፊት እና ኢአፈፊት የሆኑትን ተማሪዎች በሚያስተምሩ መምህራን እንዲሞሉ ተደርገዋል፡፡

ሐ/ ለቋንቋው አፈፊት እና ኢአፈፊት ለሆኑት የመሰናዶ ተማሪዎች፣ ለመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ለመሰናዶ ተማሪዎች ወላጆች ቃለ መጠይቅ ተደርጎ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

መ/ «ማየት ማመን ነው» ከሚለው አባባል በመነሳት ከጽሁፍና ከቃለመጠይቁ ባሻገር በየክፍሎቹ በመገኘት ያለውን ሂደት ለማጤን ተሞክሯል፡፡

እነዚህ በልዩ ልዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተጠናቀሩ፣ ከተተነተኑ፣ ከተብራሩና ከተለኩ በኋላ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

## 5.1. ግኝት

5.1.1. በአዲስ አበባና በምስራቅ ሸዋ ዞን ስር ከሚገኙት የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ ቋንቋው ለከፍተኛ ተቋሞች የመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ በጣም ቅር አሰኝቶአቸዋል፡፡ ይኸውም እየወደዱት ችላ እንዲያደርጉ ያደረገ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ስሜት ደግሞ በአፈፈቱም ሆነ በኢአፈፈቱ መካከል ልዩነት አያሳይም፤ ተመሳሳይ ስሜት ይንፀባረቃል፡፡

5.1.2. በሁለቱ መስተዳድር ስር፣ የመሰናዶ ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ቋንቋው በከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በጣም አሳዝኖአቸዋል፤ ውጤት የሌለው ሥራ እንደሚሰሩ፣ በአጠቃላይ ሁኔታው ሙያዊ ሞራላቸውን ሳይነካ አልቀረም፡፡

5.1.3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ፣ በአዲስ አበባ እና በምስራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ የሚገኙትን አብዛኛዎቹን የመሰናዶ ተማሪዎች (አፈፈቱም ሆነ ኢአፈፈቱን) የቋንቋውን ትምህርት ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱት ያደረጋቸው ይመስላል፡፡

5.1.4. በአዲስ አበባ እና በምስራቅ ሸዋ ዞን ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን አይጠሉም፤ ትምህርቱን መማር ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን የቋንቋው በከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና አለመሰጠት፣ በቋንቋው ላይ ያላቸውን አዎንታዊ አመለካከት እየሸረሸረባቸው እንደመጣ ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.1.5. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ቢሰጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሰመረና ውጤታማ እንደሚያደርገው መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ይጠቁማሉ፡፡

5.1.6. ከአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ግማሽ ያህሉ አማርኛን ከየትኛውም ቋንቋ አስበልጠው የሚወዱ ሲሆን፣ የተቀሩትን ግን እንግሊዝኛን እንደሚወዱ ነው፡፡

5.1.7. ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፈት በሆኑት የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ከአማርኛ አስበልጠው እንደሚወዱ ነው፤ ሆኖም

ግን ብዙሃን ባይሆኑም አማርኛን ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አስበልጠው የሚወዱም አሉ።

5.1.8. አብዛኛዎቹ ለቋንቋው አፈፊት የሆኑትም ሆነ ኢአፈፊቶች የአማርኛ ተናጋሪንም ሆነ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚጠሉ አይደሉም።

5.1.9. ለአብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች (አፈፊቶቹም ሆኑ ኢአፈፊቶች) የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደማይከብዳቸው ነው።

5.1.10. ለአማርኛ ቋንቋ አፈፊት ከሆኑት የአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል ለወደፊት በአማርኛ ቋንቋ መሰልጠን የሚፈልጉት ግማሾቹ ብቻ ሲሆኑ፣ የተቀሩት የቋንቋው ትምህርት የወደፊት ምርጫቸው አድርገው ስለማይቆጥሩት ትምህርቱን በደንብ አይከታተሉም።

5.1.11. ለአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት ከሆኑት የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ የቋንቋው ትምህርት የወደፊት ምርጫቸው በመሆኑ ትምህርቱን በትኩረት ይከታተላሉ።

5.1.12. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ እና የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች ለቋንቋዎች እኩል አክብሮት ቢኖራቸውም ጥቂት ተማሪዎች ግን በቋንቋዎች እኩልነት አያምኑም።

5.1.13. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ እና የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ስነጽሁፎችን ማንበብ፣ ጭውውቶችንና ድራማዎችን መከታተል በጣም እንደሚያስደስታቸው ይገልፃሉ።

5.1.14. አብዛኛዎቹ የአዲስ አበባ የመሰናዶ ተማሪዎች ለወደፊት ጋዜጠኛ፣ ደራሲ ... የመሆን ፍላጎታቸው አነስተኛ ነው። በአንፃሩ አብዛኛዎቹ የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች ለወደፊት ጋዜጠኛ፣ ደራሲ ... የመሆን ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው።

5.1.15. በሁለቱም መስተዳድር ውስጥ የሚገኙት የመሰናዶ ተማሪዎች ወላጆች ልጆቻቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በወጉ እንዲከታተሉ የሚያበረታቱ እንዳሉ ሁሉ ከጉዳይም የማይቆጥሩ ወላጆች አሉ።

5.1.16. የአማርኛ ቋንቋ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን ትምህርት ሚኒስቴር መስጠት የሚገባውን ያህል ትኩረት ለቋንቋው አልሰጠውም የሚለው የብዙዎች እምነት ነው።

5.1.17. በመሰናዶ ደረጃ ለቋንቋው ማስተማሪያ እየዋሉ ያሉት የመማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት አላቸው።

5.1.18. በተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በአኩዮች፣ በህብረተሰብ እና በመገናኛ ብዙሃን አካባቢ በማወቅም ይሆን ባለማወቅ ስለቋንቋው የተሳሳተ ግንዛቤ አልፎ አልፎ ይንፀባረቃል።

5.1.19. አማርኛ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ፣ በሁሉቱም መስተዳድር ሥር ያሉት አብዛኛዎቹ የመሰናዶ ተማሪዎች ቋንቋው በመሰናዶ ክፍሎች ያለ አማራጭ ቢሰጥ ይደግፋሉ።

5.1.20. አንዳንድ ብሔር ብሔረሰብ እንዲሁም ክልሎች በአማርኛ ቋንቋ ላይ በጐ አመለካከት የላቸውም።

5.1.21. በየቤተ መፃሕፍቱ በቂና ወቅታዊ የመርጃ መጻሕፍት የሉም።

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳብ

በክለሳ ድርሳን ስር በተዛማጅ ሥራዎች ውስጥ ለማየት እንደተሞከረው በዚህ ርዕስ ዙሪያ በተሰሩት ሥራዎች ብርሃኑ (1976)፣ ታሪኩ (1988)፣ አበበ (1990) እና ዳንኤል (1992) ውስጥ በርካታ የመፍትሔ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል። ከተሰነዘሩት የመፍትሄ ሃሳቦች መካከል በሚመለከታቸው ክፍሎች ትኩረት አግኝቶ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም መፍትሄ የተፈለገለት የመማሪያ መፃህፍትን ይዘትና አቀራረብ አስመልክተው የተሰጡት አስተያየቶች ናቸው። ቢቻል ቢቻል በጥናት ተደግፈው የሚቀርቡት አስተያየቶች፣ የመፍትሄ ሃሳቦች ወዘተ የሚመለከታቸው ክፍሎች ዘንድ ትኩረት አግኝተው እልባት ቢፈለግላቸው በየጥናቶቹ ባልተነሱ ነበር። ይህ ባለመሆኑ ምክንያት ቀደም ባሉት ሥራዎች የተሰነዘሩ ሥራዎች በዚህ ሥራም ላይ አስተያየት የተሰጠባቸው ነጥቦች አሉ።

5.2.1. የአማርኛ ቋንቋ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ብዙ ታሪካዊ ፋይዳዎችም አሉት። አብዛኛዎቹ የአገራችን ታሪካዊ ድርሳናት የተፃፉት በአማርኛ ቋንቋ ነው፤ ባለ ብዙ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች ባለቤት ለሆነችው አገራችን የመግባቢያ ድልድይ ነው፤ ዘመናዊ ትምህርት በአገራችን መሰጠት ከተጀመረበት ከ1901 ዓ.ም አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሲሰጥ የቆየ ብቸኛ ሃገር በቀል ቋንቋ ነው፤ በአገራችን ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በቋንቋው እስከ ማስተርስ ዲግሪ እየተሰጠበት ያለ ወዘተ የትምህርት ክፍል ነው። በእርግጥ ከአለም አቀፍ እውቅናና ከቴክኖሎጂ ቋንቋነት አንፃር ከእንግሊዝኛ ጋር ሊወዳደር አይችልም። ያም ሆኖ ግን ቋንቋው ከቋንቋነቱ ባሻገር የአገሪቷ ቅርስ ነው፤ የታሪክ አሻራ ነው። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ግን አሁን ያለው የገሸሸ ገሸሽ ሁኔታ አግባብነት ያለው አይመስልም። በመሆኑም ከተማሪዎች ሆነ ከመምህራን እንደተሠነዘረው መንግስት፣ ትምህርት ሚኒስቴርና ሕብረተሰቡ ስለቋንቋው አልፎ አልፎ የሚንፀባረቁትን የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ወደ ትክክለኛው የቋንቋ ሳይንስ የሚሸጋገርበትን ስልት መቀየስ ይኖርባቸዋል።

5.2.2. ለአማርኛ ቋንቋ አፈፋት የሆኑትም ሆነ ኢአፈፋቶች የአዲስ አበባ እና የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ለቋንቋው የነበራቸው አዎንታዊ አመለካከት እንደለወጠባቸው፣ ለቋንቋው ይሰጡት የነበረውን ደረጃ እንደቀነሰባቸው፣ ትምህርቱን በወጉ እንዳይከታተሉ እንዳደረጋቸው ወዘተ እንደዋነኛ መንስኤ ጠቅሰዋል:: መምህራንም በበኩላቸው የሥራ ሞራላቸውን እንደገደለ በምሬት ገልፀዋል፤ ህብረተሰቡም በውጭ ቋንቋ ማምለኩን አጠንክሮ እንዲገፋበት ሰበብ ሆኗል:: ስለዚህ ለዚህ ሁሉ አሉታዊ አዝማሚያዎች መንስኤ ከሚሆን፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ያለውን ወይም እየተፈጠረ ያለውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የአማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ ቢያካትት::

5.2.3. የአማርኛ ቋንቋ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ከመሆኑም ባሻገር፣ በአገሪቷ ውስጥ በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው:: ስለሆነም ቋንቋው በመሰናዶ ክፍሎች በክልሎች አካባቢ እንደ አማራጭ ከሚቀርብ እንደ እንግሊዝኛ ሁሉ ለሁሉም የመሰናዶ ተማሪዎች በዋና ትምህርትነት ቢሰጥ::

5.2.4. መምህራንን ከወቅታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ፣ ለአዳዲስ ጽንስ ሐሳቦችና ግንዛቤዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ለማድረግ፣ በአጠቃላይ የማስተማር ሞራላቸውን ለማነቃቃት በየጊዜው የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ቢሰጡ::

5.2.5. አሁን በሥራ ላይ ያለው የመሰናዶ ክፍሎች የመማሪያ መፃህፍት በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት አለው:: ነገር ግን ቋንቋውን ከተለያየ አቅጣጫ ከሚፈታተኑት ሁኔታዎች ለማዳን በየጊዜው ከተማሪዎች ከሚሰነዘሩት ገንቢ አስተያየቶች አንፃር መፃህፍቱን ማሻሻል የግድ ሆኗል:: በዚህ መሠረት መጽሐፍቱ ከይዘት አኳያ ወደ ስነጽሁፍ ያዘነበለ ሆኖ፣ ምልልሶችን፣ ጭውውቶችን፣ አጫጭር ድራማዎችን፣ ትረካዎችን፣ ድርሰት ማዛፍን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ ቅኔዎችን ወዘተ በብዛት ያቀፈ ሆኖ ቢሻሻል፤ በተጨማሪም መልመጃዎቹ አሰልቺ እንዳይሆኑ ተመጥነው ቢቀርቡ:: እንዲሁም ከአቀራረብ አኳያ የተማሪውን ስሜት ቆንጥጦ የመያዝ ሃይል እንዲኖረው በማድረግና ተማሪውን ለተሳትፎ በሚጋብዝ ስልት ቢዘጋጅ::

5.2.6. ከመምህራንና ከአንዳንድ ተማሪዎች በተገኘው ጥቆማ መሠረት አዳዲስና ወቅታዊ መርጃ መፃህፍት ለየትምህርት ቤቶቹ አይገዙም:: ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት አንደኛ፣ ቋንቋው ለተቋም የመግቢያ ፈተና ስለማይሰጥ ፈተና ላይ ለሚመጡት የትምህርት አይነቶች ትኩረት ስለሚደረግ:: ሌላው እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው (በተለይ በክልሎች አካባቢ) ቋንቋው ቀደም ሲል የዳበረና ብዙ መርጃ

መጻሕፍት አለው በማለት ለአፍ መፍቻ ቋንቋ በይበልጥ ትኩረት እንደሚሰጡ ነው፡፡ የመርጃ መፃሕፍት እንደ ልብ በቤተመፃህፍት ውስጥ መኖር ተማሪውን ይበልጥ እንዲያነብ፣ እንዲያገናዝብ፣ ለትምህርቱ ፍቅር እንዲኖረው ወዘተ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ማጣቀሻ መፃሕፍት እንደልብ ካሉ የቤት ሥራ፣ የቡድን ሥራ ወዘተ በአግባቡ ለማሠራት ሁኔታዎች ይመቻቹላቸዋል፡፡ ስለዚህ ለቋንቋ ትምህርት ማጣቀሻ የሚሆኑ መርጃ መፃሕፍት በየቤተመፃህፍቱ ቢኖሩ፡፡

5.2.7. በየትምህርት ቤቱ ያሉት የስነጽሁፍ፣ የድራማ፣ የክርክር ወዘተ ክበቦች በተጠናከረ መልኩ ቢደራጁ ለቋንቋው ትምህርት መወደድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚል እምነት አለ፡፡ ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና ትምህርት ቤቶች ክበባት በተጠናከረ መንገድ ተደራጅተው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማነት አጋዥ ሚናቸውን እንዲወጡ ሁኔታዎች ቢመቻቹ፡፡

እነዚህ ከላይ ከ1-7 የሰፈሩት የመፍትሄ ሃሳቦች በጥናቱ ውጤት ላይ ለታዩት ዋና ዋና ችግሮች የመቅረፊያ ስልቶች ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ የእነዚህ ዋና ዋና ችግሮች እልባት ማግኘት ደግሞ የተቀሩት አሉታዊ ጐኖች እንዳያንሰራሩ ከማድረጉ ባሻገር አዎንታዊ ጐኖች እንዲጎለብቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እምነት በመኖሩ፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ሁሉ በትኩረት ቢያጤነው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሃይሉ ተሰማ (1994) «አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አዘገጃጀት ሂደት»፣ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማሪያ የተዘጋጁትን መርሃ ትምህርቶች ለማሻሻል በተካሄደው አወደ ጥናት መነሻ የቀረበ ጽሁፍ። አዲስ አበባ፣ ስ.ት.ገ.ጥ.ም.ኢ.፣ ያልታተመ።

ሙሉ እመቤት ዘነበ (1989) «ስነ ጽሁፍ በቅድመ 1966 በአማርኛ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የነበረው ድርሻና አሁን ሊኖረው የሚገባው ሚና»፣ ለአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት (ከ9ኛ -12ኛ ክፍሎች) ዐውደ ጥናት የቀረበ የጥናት ጽሑፍ። አዲስ አበባ፣ ስ.ት.ገ.ጥ.ም.ኢ.፣ ያልታተመ።

ብርሃኑ ገብረማርያም (1976) «ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት (Attitude) በስድስት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።» ያልታተመ፣ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ታሪኩ ፋንታዬ (1988) «ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት»። ያልታተመ፣ የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ትምህርት ሚኒስቴር (1981) «የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ፖሊሲ ጥናት።» ጥራዝ አንድ፣ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ።

አለም እሸቱ (1992) <u>መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ</u>። አዲስ አበባ፣ የቅድስተ ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋኩሊቲ ሕትመት።

አበበ ሽፈራው (1990) «አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት በሰበታ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት።» ያልታተመ፣ ለኢዱኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ።

<u>አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት</u>። (1986) አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

<u>የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና አተገባበር</u> (1994) አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

<u>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት</u> (1987) አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት።

ዳንኤል መኮንን (1992) «በሀዲይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ በሆሳዕና ከተማ የሚገኙ የሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸው አመለካከት።» ያልታተመ፣ ለኢዲኬሽን ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ።

ፍቃደ አዘዘ (1982) «አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ አላማዎች፣ ስለ ሥርአተ ትምህርቶች፣ ስለመማሪያ መፃህፍት እና ስለስነጽሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት /1940-1982/»፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ሲምፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ። ስ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ.፣ ያልታተመ።

Aggarwal, J. C. (1998) Essentials of Educational Psychology. Reprinted.New Delhi: Vikas Publishing House Put Ltd.

Allport, G. W (1967) "Attitudes" in Fishbein, M. (Ed) Reading in Attitude Theory and Measurement. New York: John Willey and Sons, Inc. (3-13).

Anastasi, A. (1976) Psychological Testing. 4th ed. New York: Macmillan Publishing Inc.

Atkinson, J. et al (1987) Dictionary of Psychology. 4th Revised ed. New Delhi: Batra Art Printers.

Best, J. W and J.V. Kahn (1998) Research in Education. New Delhi: Prentice-Hall of India Private Limited.

Celce-Murcia, M (Ed) (1991) Teaching English: as a Second or Foreign Language. 2nd ed. Boston: Heinle and Hinle Publishers.

Chauhan, SS. (1996). Advanced Educational Psychology. 6th Revised ed. New Delhi: Vikas Publishing House Pvt. Ltd.

Colle, J. and Stephen, S. (1987) Literature in the Language Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Cronbach, L.L. (1963) Educational Psychology. 2nd ed, London: Harcourt, Brace and World Inc.

Cunningsworth, A. (1984) Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: Heine, Mann.

Cushman, D. R and R.D. Mcphee (Ed) (1980). Message-Attitude-Behavior Relationship. New York: Academic Press.

Day, R. R. and Jullan. B. (1998). Extensive Reading in Second Language Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Dubin, F. and Elite, Olshtain (1986) Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Fernald, L. D and Peter, S. F. (1999) Introduction to Psychology. 5th ed. Delhi: A.I.T.B.S Publishers and Distributors.

Fishbein, M. (ED) (1967) Reading in Attitude Theory and Measurement. New York: John Wiley and Sons, Inc.

Gagne, R.M. (1977). The Conditions of Learning. 3rd Edition, New York: Holt, Rinehart and Winston.

Gardner, R. C (1968) "Attitudes and Motivation: Their Role in Second-language Acquisition." In TESOL Quarterly 2.141-50.

_______ (1975) "Attitudes and Motivation: Their Role in Second Language Acquisition." In Oller, Jr and Richards J.C (Ed). Focus on the Learner: Pragmatic Perspectives for the Language Teacher. Massachusetts: New Bury House Publishers, Inc. ( 235-45).

Harmer, J. (1983) The Practice of English Language Teaching. New York: Longman.

Hurlock, E.B. (1996) Developmental Psychology: A Life-Span-Approach. 8th Reprinted. New Delhi: McGraw-Hill Publishing Company Ltd.

Jahoda, M. and Neil, Warren (1966) Attitudes. England: Ponguim Books Inc.

Kerlinger, F.N. (1988) Foundation of Behavioral Research. 3rd edition. Hong Kong: Holt, Rinehart and Winston Inc.

Kiesier, et al (1969) Attitude Change. New York: Jon Wileys and Sons, Inc.

Kundu, C. L and D.N Tutoo (1988) Educational Psychology. New Delhi: Sterling Publishers Private Limited.

Kuppuswamy, B. (ed) (1984) Advanced Educational Psychology. New Delhi: Sterling Publishers, Private Ltd.

Lambert, W.W. and Wallace, E.L (1964) Social Psychology. New Jersey: Prentice-Hall, Inc.

Lewy, A. (Ed) (1977) Curriculum Evaluation. New York: Longman, Inc.

Littlewood, W. (1992) Foreign and Second Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Malim, T. and Ann, Birch (1998) Introductory Psychology. London: Macmillan Press Ltd.

Medhaine Habtegiorgis (1986) "The Attitude of Eleventh Grade Students Towards the Learning of English as a Foreign Language." Unpublished M.A. Thesis. Addis Ababa University.

Morgan, C.T. (1961) Introduction to Psychology. 2nd ed, New York; McGraw-Hill Book Company, Inc.

Morgan, C. et al (1986). Introduction to Psychology. 7th ed, New York: McGraw-Hill Book Company.

Neale, et al (1970) "Relationship Between Attitudes Towards School Subjects and School Achievement." Journal of Education Research, Vol. 63; No. 5, 232-37.

Punkhurst, R. (1976) "Historical Background of Education in Ethiopia" in Bender, M.L. and et.al. Language in Ethiopia. Oxford: Oxford University Press. (305-323)

Roger, D. and Peter, H. (1995) Mastering Psychology. 2nd ed, London: Macmillan press.

Rokeach, M. (1968) "In Sills, D.L. (ED) International Encyclopedia of the Social Science. Vol.1, New York: the Macmillan Company and the Free Press. (449-457).

Russell, I. L (1989) "Development of Attitudes, Interests, and Values" In Skinner, C.E. (Ed) Educational Psychology. 4th ed. New Delhi: Prentice-Hall of India. (325-53).

Sherif, et al (1965) Attitude and Attitude Change. Philadelphia: W.B. Saunders, Company.

Sills, D.L. (1968) International Encyclopedia of Social Science. Vol. 1 and 2. New York: The Macmillan Company and Free Press.

Skinker, C. E. (Ed) (1989) Educational Psychology. 4th ed, New Delhi: Prentice-Hall of India.

Smith, M. B. (1968) "Attitude Change" in Sills, D.L. (Ed) International Encyclopedia of the Social Science. Vol 1 and 2, New York: The Macmillan Company and the Free Press. (458-66).

Spolsky, B. (1969) "Attitudinal Aspects of Second Language Learning" in Language Learning. Vol. XIX, Nos. 3 and 4. ( 271-83).

__________ (1990) Conditions for Second Language Learning. 2nd ed, Oxford: Oxford University Press.

Stewart, W.A. (1968) "National Development and Language Diversity" in Fishman, J.A. (ed). Reading in Sociology of Language. Paris: Moutons and Co, Printers, (214-216).

The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia (1996) Results for Oromiya Region. Vol. I, Part I, Addis Ababa: Certoral Statistics Authority.

Thurnstone, L. L (1967) "Attitudes Can BE Measured" in Fishbein, M. (Ed) Reading in Attitude Theory and Measurement. New York: John Willey and Sons, Inc. PP. 77-89.

Vargas, S.J. (1972) Writing Worthwhile Behavioral Objectives. New York: Harber and Row. Publishers.

## አባሪ "ሀ"

I. በአዲስ አበባ መስተዳድር እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን ስር በሚገኙት የመሰናዶ (Preparatory) ተማሪዎች የሚሞላ የመጠይቅ ቅፅ፡፡

### ውድ ተማሪ

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመሰናዶ ደረጃ እንደ አንድ የትምህርት አይነት እየተሰጠ እያለ ወደ ከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ከቋንቋው ትምህርት አኳያ ያሳደረውን አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ አመለካከት ላይ አስተያየት ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከተፈለገው ግብ ደርሶ ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው ትክክለኛ መረጃዎችን ሰብስቦ ማጠናቀር ሲቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለውን በአንተ/በአንቺ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበህ/አንብበሽ ትክክለኛውን አስተያየት (መረጃ) ስትሰጥ/ስትሰጪ ብቻ ነው፡፡ የምትሰጠው/የምትሰጪው ምላሽ ሆነ አስተያየት በምስጢር የሚያዝ ስለሆነ ውስጣዊ ስሜትህን/ስሜትሽን በትክክል የሚወክለውን መልስ እንድታሰፍር/እንድታሰፍሪ በትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ የሆነ የትምህርት ጊዜህን/ጊዜሽን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበርከኝ/ስለተባበርሽን በቅድሚያ ምስጋናዬ ይድረስህ/ይድረስሽ!

<u>ማሳሰቢያ</u>

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

*አጥኚው*
*የካቲት/1996 ዓ.ም*
*አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

### አጠቃላይ መረጃ

### ሀ/ ስለራሳችሁ የሚፈለግ መረጃ

ሀ.1. የምትማሩበት ት/ቤት ስም ----------------------------------------------

ሀ.2. ት/ቤታችሁ የሚገኝበት፡- ክልል ------------------------------------፣ ዞን ወይም ክፍለ ከተማ ------------------ ወረዳ ----------------------------፡፡

ሀ.3. ፆታ -----------------------፣ ት/ደረጃ -----------------፣ ዕድሜ -----------------፡፡

ሀ.4. የትውልድ ቦታ ---------------------፣ አፍ መፍቻ ቋንቋ ------------------- አሁን የምትናገራቸው/የምትናገሪያቸው ቋንቋዎች በችሎታ ቅደም ተከተል --------------------- ----------------------------------------------------------------------------

ሀ.5. የመረጥከው/ሽው የትምህርት ዘርፍ

ሳይንስ ☐ ፣ አርት ☐

## ለ/ ስለቤተሰባችሁ የሚፈለግ መረጃ

ለ.1. የአባት የመጀመሪያ ቋንቋ --------------------፣ የእናት የመጀመሪያ ቋንቋ ------------------

ለ.2. የአባት የት/ደረጃ -----------------------------፣ የእናት የት/ደረጃ --------------------------

ለ.3. የአባት የሥራ መስክ ------------------------፣ የእናት የሥራ መስክ ----------------------

ለ.4. የአባት የሥራ ቋንቋ -------------------------፣ የእናት የሥራ ቋንቋ ---------------------

ለ.5. ቤተሰብ ቤት ውስጥ በብዛት የሚገለገሉበት ቋንቋ ---------------------------------------------

### <u>መመሪያ አንድ</u>

የተሰነዘረውን ሐሳብ ረጋ ብላችሁ ካነበባችሁ በኋላ፡-

ሀ. በሐሳቡ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የምትስማሙ ከሆነ "በጣም እስማማለሁ" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን "X" አድርጉ።

ለ. ከፍ ባለ ደረጃ ባይሆንም በሐሳቡ የምትስማሙ ከሆነ "እስማማለሁ" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ።

ሐ. ስለተሰነዘረው ሐሳብ ለመስማማትም ሆነ ላለመስማማት ከተጠራጠራችሁ "መወሰን ያስቸግረኛል" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ።

መ. የተሰነዘረውን ሐሳብ የማትቀበሉ ከሆነና የተቃውሞአችሁ ደረጃ መለስተኛ ከሆነ "አልስማማም" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ።

ሠ. የተሰነዘረውን ሐሳብ በጭራሽ የማትቀበሉ ወይም አጥብቃችሁ የምትቃወሙ ከሆነ "ፍጹም አልስማማም" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ።

የሚከተለውን ምሳሌ ተመልከቱ።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ያስቸግረኛል | አልስማማም | ፍጹም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ብዙ ቋንቋ ማወቅ ያረካኛል | X | | | | |
| 2 | ከአገሬ ቋንቋ ይልቅ የውጭ ቋንቋ ያስደስተኛል | | | | X | |

ሐ/ ይህ መጠይቅ በውስጡ ሰባት የተለያዩ ጉዳዮችን ይዳስሳል። እነሱም

1. ወደከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ አለመካተቱ የሚያሳድረው ተፅዕኖ
2. የተማሪው ግላዊ አመለካከት።
3. የአማርኛ ቋንቋን መማር ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንፃር።
4. የወላጅ፣ የእኩዮች፣ የኅብረተሰብና የመገናኛ ብዙሃን አመለካከት።
5. የቋንቋው አፈፌትና ኢአፈፌት መሆን የሚያሳድረው ተፅዕኖ።
6. የመማሪያ መጻሕፍቱ ይዘትና አቀራረብ።
7. ለአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከተሰጠው ዝቅተኛ ደረጃ አንፃር።

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ 5 | እስማማለሁ 4 | ለመወሰን ያስቸግረኛል 3 | አልስማማም 2 | ፍፁም አልስማማም 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ ለቋንቋው እስጥ የነበረውን ቦታ ቀንሶብኛል። | | | | | |
| 1.2 | የአማርኛ ቋንቋ ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ በቋንቋው ላይ ያለኝን አመለካከት አልለወጠም። | | | | | |
| 1.3 | ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ አማርኛን ባልማረው ደስታውን አልችልም። | | | | | |
| 1.4 | ቋንቋው ለተቋም መግቢያ ፈተናነት ቢሰጥ የትምህርት አቀባበሉን አዎንታዊ የማድረግ ሃይል አለው። | | | | | |
| 2.1 | የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪን ስለምጠላ የአማርኛንም ትምህርት አልወድም። α | | | | | |
| 2.2 | ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ ለአማርኛም ሆነ ለሌሎች ቋንቋዎች ጥሩ አመለካከት አለኝ። | | | | | |
| 2.3 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስለሚከብደኝ አልወደውም። | | | | | |
| 2.4 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የወደፊት ምርጫዬ ባለመሆኑ በትኩረት አልከታተልም። | | | | | |
| 2.5 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሙሉ ልብ እከታተላለሁ። | | | | | |
| 2.6 | አማርኛ ጨቋኝ ቋንቋ በመሆኑ በእርሱ ላይ ጥሩ አመለካከት የለኝም። | | | | | |
| 2.7 | ለቋንቋዎች እኩል አክብሮት አለኝ። | | | | | |
| 2.8 | የአማርኛ ስነጽሑፎችን ማንበብ፣ ጭውውቶችንና ድራማዎችን መከታተል በጣም ያስደስተኛል። | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ 5 | እስማማለሁ 4 | ለመወሰን ያስቸግረኛል 3 | አልስማማም 2 | ፈጽሞ አልስማማም 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 | በአማርኛ ትምህርት ገፍቼ ጋዜጠኛ፣ደራሲ ... መሆን እፈልጋለሁ:: | | | | | |
| 3.2 | የአማርኛ ቋንቋ በመማሬ ስለቋንቋና የቋንቋ ባህሪያት እንዲሁም ስለስነጽሑፍ ጥሩ ግንዛቤ ለመጨበጥ ችያለሁ:: | | | | | |
| 3.4 | በመሰናዶ ደረጃ የሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለከፍተኛ ተቋማት መሠረት በመሆናቸው ውድጀአቸዋለሁ:: | | | | | |
| 3.5 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሥነ-ጽሑፍና ድራማ ክበብ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንድሆን ረድቶኛል | | | | | |
| 4.1 | ቤተሰቦቼ የአማርኛን ትምህርት በወጉ እንድከታተል ያበረታቱኛል:: | | | | | |
| 4.2 | ቤተሰቦቼ የአማርኛ ቋንቋ ከፖለቲካ ጋር እያይዘው ስለሚመለከቱ በኔ አማርኛ መማር ላይ በጎ አመለካከት የላቸውም:: | | | | | |
| 4.3 | በኔ አማርኛ መማር ጓደኞቼ ይሳለቁብኛል:: | | | | | |
| 4.4 | የአካባቢዬ ሰዎች አማርኛን "ወንዝ የማያሻግር" እያሉ እንደትምህርት አይቆጥሩትም:: | | | | | |
| 4.5 | አንዳንዴ በመገናኛ ብዙሃን አማርኛን ከነፍጠኛ ጋር እያይዘው የሚያቀርቡት ዝግጅቶች በአማርኛ ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዳይኖረኝ አድርጎኛል:: | | | | | |
| 4.6 | በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ለማዳበር የመምህሩ ሁኔታ ትልቅ ድርሻ አለው:: | | | | | |
| 5.1 | አማርኛ አፌን የፈታሁበት ቋንቋ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና ቢሰጥ ደስ ይለኛል:: | | | | | |
| 5.2 | ከአማርኛ የበለጠ የምወደው ቋንቋ አለኝ:: | | | | | |
| 5.3 | አማርኛ 2ኛ ቋንቋዬ በመሆኑ ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተና አለመሰጠቱ አስደስቶኛል:: | | | | | |
| 5.4 | የአማርኛ ቋንቋ ከየትኞቹም ቋንቋዎች አስበልጨ እወደዋለሁ:: | | | | | |
| 6.1 | የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ ቋንቋውን ተወዳጅ ያደርገዋል:: | | | | | |
| 6.2 | በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል ውስጥ የተካተቱት ይዘቶችና አቀራረባቸው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንድጠላ አድርጎኛል:: | | | | | |
| 7.1 | አማርኛ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ በመሰናዶ ክፍሎች (Preparatory classes) ያለአማራጭ ቢሰጥ ደስ ይለኛል:: | | | | | |
| 7.2 | የአማርኛ ውጤት ቦታ ስለሌለው ዋጋ እንዳለው ትምህርት አልቆጥረውም:: | | | | | |

መ/ አሁን የምትማሯቸውን የትምህርት አይነቶች በጣም ከምትወዱት

በመጀመር 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ. . . እያላችሁ ሁሉንም በደረጃ አስቀምጡ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | ---------------------------- | 5ኛ | ---------------------------- |
| 2ኛ | ---------------------------- | 6ኛ | ---------------------------- |
| 3ኛ | ---------------------------- | 7ኛ | ---------------------------- |
| 4ኛ | ---------------------------- | 8ኛ | ---------------------------- |

ሠ. ተማሪው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት (Negative Attitude) እንዲይዝ ከፍተኛ ሚና አላቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች ወይም ተላውጦች (Variables) 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ...8ኛ እያላችሁ በደረጃ አስቀምጡአቸው::

--------- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ ሳቢ አለመሆን::

--------- ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ::

--------- ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛን ቋንቋ እንደጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበርከት::

--------- የመምህራን ብቁ ሆነው አለመገኘት::

--------- ለአብዛኛዎቹ ክልሎች ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና ለራሳቸው ቋንቋ ቅድሚያ መስጠታቸው::

--------- በብሔራዊ ፈተና የአማርኛ ውጤት አማራጭ ውስጥ መግባቱ::

--------- በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚደረጉ ቅስቀሳዎች::

--------- ወላጆች፣ ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆን::

<u>መመሪያ ሁለት</u>:- ከዚህ ቀጥለው ላሉት ሁለት ጥያቄዎች ያለሽን/ያለህን አስተያየት ባዶ ቦታ ላይ ፃፊ/ፃፍ::

ረ. ሀ. የአማርኛ ቋንቋን መማር በጣም የሚያስደስትሽ/የሚያስደስትህ ከሆነ ምን ምን ነገሮች እንዲሻሻል ትጠቁሚያለሽ/ትጠቁማለህ? ------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------

ረ.ለ. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ከሌለሽ/ከሌለህ ቋንቋውን እንድትጠሉ ያደረጉአችሁን ነጥቦች አስፍሩ ------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------

*"በድጋሚ ስለትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ"*

*አጥኚው*

# አባሪ "ለ"

## II. በአዲስ አበባ መስተዳድር እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የምስራቅ ሸዋ ዞን የመሰናዶ ተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ መምህራን የሚሞላ የመጠይቅ ቅፅ፡፡

## የተከበራችሁ ውድ መምህራን

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመሰናዶ ደረጃ እንደ አንድ የትምህርት አይነት እየተሰጠ እያለ ወደ ከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ ከቋንቋው ትምህርት አኳያ ያሳደረውን አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ አመለካከት ላይ አስተያየት ለመሰብሰብ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከተፈለገው ግብ ሊደርስ የሚችለው ትክክለኛ መረጃዎችን ተሰብስቦ ሲጠናቀር ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለውን በእርስዎ ጥያቄዎች በጥሞና አንብቦ ትክክለኛውን መረጃ መስጠት ብቻ ነው፡፡ በአጥኚው በኩል የእርስዎ ምላሽ ሆነ አስተያየት በምስጢር የሚያዝ ስለሆነ ትክክለኛውን መረጃ እንዲያሰፍሩልኝ በትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

ውድ የሆነ ጊዜዎትን በመሰዋት ይህንን መጠይቅ በመሙላት ስለተባበሩኝ በቅድሚያ ምስጋናዬ ይድረስዎት!

<u>ማሳሰቢያ</u>

በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

*አጥኚው*
*የካቲት/1996 ዓ.ም*
*አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

## ስለራሳችሁ የሚፈለግ መረጃ

1. ፆታ -----------------------፣ የት/ደረጃ ----------------፣ የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት -----------------፣ የአገልግሎት ዘመን ------------------------------፡፡
2. የትውልድ ቦታ -------------------፣ክልል ------------፣ ዞን/ክፍለ ከተማ -----------
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ----------------------------------፣ አሁን የሚናገሩአቸው ቋንቋዎች በችሎታ ቅደም ተከተል ------------------------------------------------------------
4. በአማርኛ ቋንቋ ስልጥነው ከሆነ የራስዎት ምርጫ ነበር? አዎን ☐ አይደለም ☐
5. አሁንስ እያስተማሩ ያሉት፡-
   ሀ/ በራስዎት ፍላጎት ተመድበው ነው
   ለ/ በቋንቋው ስለሰለጠኑ ተገድደው ነው

## ሀ/ አማራጭ መልሶቹን ረጋ ብላችሁ ካነበባችሁ በኋላ፡-

ሀ/ በሐሳቡ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የምትስማሙ ከሆነ "በጣም እስማማለሁ" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን "X" አድርጉ፡፡

ለ/ ከፍ ባለ ደረጃ ባይሆንም በሐሳቡ የምትስማሙ ከሆነ "እስማማለሁ" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ፡፡

ሐ/ ስለተሰነዘረው ሐሳብ ለመስማማትም ሆነ ላለመስማማት ከተጠራጠራችሁ "መወሰን ያስቸግረኛል" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ፡፡

መ/ የተሰነዘረውን ሐሳብ የማትቀበሉ ከሆነና የተቃውሞአችሁ ደረጃ መለስተኛ ከሆነ "አልስማማም" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ፡፡

ሠ/ የተሰነዘረውን ሐሳብ በጭራሽ የማትቀበሉ ወይም አጥብቃችሁ የምትቃወሙ ከሆነ "ፍጹም አልስማማም" በሚለው አማራጭ ሥር ባለው ሣጥን ውስጥ "X" አድርጉ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ 5 | እስማማለሁ 4 | ለመወሰን ያስቸግረኛል 3 | አልስማማም 2 | ፍፁም አልስማማም 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ ከመታወቁ በፊትና ከታወቀ በኋላ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የአመለካከት ለውጥ ተከስቷል፡፡ | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተናነት መሰጠት አለመሰጠቱ በተማሪዎቹ አመለካከት ላይ ያመጣው ለውጥ የለም፡፡ | | | | | |
| 3 | በመሰናዶ ደረጃ የተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ አመለካከት የሚያሳድሩ አይደሉም፡፡ | | | | | |
| 4 | ቋንቋውን በማስተማሬ ብዙ የስነጽሑፍ፣ የስነልሳን ወዘተ ባለሙያዎችን እንዳፈራ ስለሚያስችለኝ እረካበታለሁ፡፡ | | | | | |
| 5 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና ላይ ቢሰጥ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉት ያደርጋቸዋል፡፡ | | | | | |
| 6 | ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ትኩረት ስለማይሰጡና ጥሩም አመለካከት ስለሌላቸው ሌላ ትምህርት ባስተምር ደስ ይለኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | አማርኛ የፌደራሉ የሥራ ቋንቋ በመሆኑ በመሰናዶ ደረጃ አማራጭ ውስጥ ባይገባ ይመረጣል፡፡ | | | | | |
| 8 | የአማርኛ ቋንቋ አፌ.ፈትም ሆኑ ኢአፌ.ፈት ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት ላይ ባላቸው አመለካከት ተመሳሳይ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 9 | በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በቋንቋው ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት አላቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ | | | | | |
| 10 | ትምህርቱን ለማሻሻል ዕድል ቢሰጠኝ በአማርኛ ማስተማር መቀጠል አልፈልግም፡፡ | | | | | |

## ለ/ በደረጃ የሚቀመጡ ጥያቄዎች

ተማሪው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት (Negative Attitude) እንዲይዝ ከፍተኛ ሚና አላቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ተላውጦች (Variables)1ኛ፣2ኛ፣3ኛ፣...8ኛ እያላችሁ በደረጃ አስቀምጡአቸው::

------- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት መጻሕፍት ይዘትና አቀራረብ ሳቢ አለመሆን::

------- ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና ውስጥ አለመካተቱ::

------- ከግንዛቤ ጉድለት የአማርኛ ቋንቋን እንደጨቋኝ ቋንቋ የሚመለከቱ ክፍሎች መበርከት::

------- የመምህራን ብቁ ሆኖ አለመገኘት::

------- ለአብዛኛዎቹ ክልሎች ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑና ለራሳቸው ቋንቋ ቅድሚያ መስጠታቸው::

------- በብሔራዊ ፈተና የአማርኛ ውጤት አማራጭ ውስጥ መግባቱ::

------- በተዘዋዋሪ የአማርኛ ቋንቋ ቦታ እንዳይኖረው የሚያደርጉ ቅስቀሳዎች::

------- ወላጆች ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ለቋንቋው ትምህርት የሚሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆን::

## ሐ/ ቀጥሎ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የየግል አስተያየት በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ፃፉ::

1. ተማሪው ትምህርቱን እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች ለምሳሌ እንደ እንግሊዝኛና ሂሳብ በከፍተኛ ተነሳሽነት ወደሚማሩበት ደረጃ ለማሸጋገር ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ይላሉ?------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

2. አንዳንድ ተቆርቋሪዎች ወይም አንዳንድ አጥላዮች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት መግቢያነት አለመሰጠቱን አስታክከው አንድ የሚሉት አባባል አለ:: "እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" ይህንን አባባል እንዴት ያዩታል?

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

3. በአዎንታዊ ጐኑም ሆነ በአሉታዊ ጐኑ ለቋንቋው አፈፊት በሆኑ ተማሪዎችና ኢአፈፊት በሆኑ ተማሪዎች መካከል የአመለካከት ልዩነት ያለ ይመስሎታል? ካለ ልዩነቱ እንዴት ይንፀባረቃል?------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

*በድጋሚ ስለትብብርዎ ከልብ አመሰግናለሁ::*

*አጥኚው*

# አባሪ "ሐ"

## በቃለ መጠይቅ መልክ ለመሰናዶ ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የመሰናዶ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?
2. አማርኛ ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል ብለህ/ብለሽ ትገምታለህ/ትገምቻለሽ?
3. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋም የመግቢያ ፈተና አለመሰጠቱን ትደግፋለህ/ትደግፊያለሽ? ለምን?
4. በክፍል ውስጥ የሚንፀባረቁት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አመለካከት ለቋንቋው አፈፌት በሆኑትና ኢአፈፌት በሆኑ ተማሪዎች መካከል ልዩነት ይታያል?
5. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ ያልሆነ/ አሉታዊ አመለካከት እንዲቀርጽባቸው ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ምን ምን ይመስልሃል/ይመስልሻል?
6. ተማሪዎች በሙሉ ፍላጎትና ፍቅር የቋንቋውን ትምህርት እንዲከታተሉ ምን ቢደረግ ይሻላል?
7. «ብዙ ቋንቋ መቻል ከብዙ የሕብረተሰብ ክፍል ጋር ያግባባል» የሚለው አባባል እንዴት ታያለህ/ታያለሽ?

# አባሪ "መ"

## ለመምህራን በቃለ መጠይቅ መልክ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች

1. የመሰናዶ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተናነት አለመሰጠቱ ከታወቀ ወዲህ በቋንቋው ትምህርት ላይ ተማሪዎች ያመጡት የአመለካከት ለውጥ አለ?
3. ለቋንቋው ትምህርት ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ከክልል ክልል ወይም ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ሊለያዩ የሚችሉበት አጋጣሚም ይኖራል። ለመሆኑ በእናንተ ትምህርት ቤት ጉልህ የሆኑ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው? ከምንስ የመነጩ?
4. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸውና በትምህርቱ ተማርከው ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ምን ቢደረግ የሚሻል ይመስሎታል?
5. ይህ አሉታዊ ሆነ አዎንታዊ አመለካከት ከተማሪዎች ለቋንቋው አፈፃት/ ኢአፈፃት ከመሆን አንፃር ልዩነት ይታይባቸዋል?

# አባሪ "ሠ"

ለተማሪ ወላጆች በቃለ መጠይቅ መልክ የቀረቡላቸው ጥያቄዎች

1. በመሰናዶ (Preparatory) ደረጃ ልጅዎ አማርኛ መማሩን ምን ያህል ይደግፉታል?
2. «ብዙ ቋንቋ መቻል ከብዙ ብሔረሰብ ክፍል ጋር ለመግባባት ያስችላል» የሚለውን አባባል እንዴት ያዩታል?
3. ለከፍተኛ ተቋማት የመግቢያ ፈተና አማርኛም እንደ እንግሊዘኛ እና የሒሳብ ትምህርት ቢሰጥ ይደግፋሉ? ለምን?
4. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት እንዲኖር የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል፤ እርስዎ ካለዎት ልምድ/ገጠመኝ አንዳንዶቹን ቢጠቅሱልኝ?

## አባሪ “ረ”

1. «ወደ ከፍተኛ ተቋም መግቢያ ፈተና ውስጥ አማርኛ አለመካተቱ የሚያሳድረው ተፅዕኖ» በሚለው ተላውጦ ስር የተመዘገበ ዝርዝር ውጤት

መፍቻ:- *→ አሉታዊ ዐረፍተ ነገር

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 | ለ | 58 | 30 | 54 | 27.8 | 20 | 10.3 | 30 | 15.4 | 32 | 16.5 | 3.4 |
| | ሊ | 67 | 35 | 44 | 22.9 | 25 | 13 | 35 | 18.2 | 21 | 10.9 | 3.5 |
| | ድ | 125 | 32.4 | 98 | 25.4 | 45 | 11.7 | 65 | 16.8 | 53 | 13.7 | 3.5 |
| *1.2 | ለ | 34 | 17 | 29 | 14.5 | 12 | 6 | 71 | 35.5 | 54 | 27 | 3.4 |
| | ሊ | 15 | 7.6 | 47 | 23.9 | 25 | 12.7 | 83 | 42.1 | 27 | 13.7 | 3.3 |
| | ድ | 49 | 12.3 | 76 | 19.1 | 37 | 9.4 | 154 | 38.8 | 81 | 20.4 | 3.4 |
| *1.3 | ለ | 15 | 7.5 | 9 | 4.5 | 22 | 11.1 | 48 | 24.1 | 105 | 52.8 | 4.1 |
| | ሊ | 13 | 6.6 | 16 | 8.0 | 15 | 7.5 | 38 | 19.1 | 117 | 58.8 | 4.2 |
| | ድ | 28 | 7.0 | 25 | 6.3 | 37 | 9.3 | 86 | 21.6 | 222 | 55.8 | 4.1 |
| 1.4 | ለ | 76 | 38.2 | 46 | 23.1 | 35 | 17.6 | 20 | 10 | 22 | 11.1 | 3.7 |
| | ሊ | 63 | 31.9 | 47 | 23.9 | 40 | 20.3 | 26 | 13.2 | 21 | 10.7 | 3.5 |
| | ድ | 139 | 35.1 | 93 | 23.6 | 75 | 18.9 | 46 | 11.6 | 43 | 10.9 | 3.6 |

# አባሪ "ሰ"

2. «የተማሪው ግላዊ አመለካከት» በሚለው ተላውጦ ስር ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገቡ ውጤቶች

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *2.1 | ከ | 7 | 3.5 | 0 | 0 | 4 | 2 | 22 | 11.1 | 166 | 83.4 | 4.7 |
| | ኪ | 4 | 2 | 17 | 8.6 | 10 | 5.1 | 18 | 9.1 | 149 | 75.2 | 4.5 |
| | ድ | 11 | 2.8 | 17 | 4.3 | 14 | 3 | 40 | 10.1 | 115 | 79.1 | 4.6 |
| 2.2 | ከ | 137 | 68.9 | 54 | 27.1 | 3 | 1.5 | 3 | 1.5 | 2 | 1 | 4.6 |
| | ኪ | 142 | 71.4 | 31 | 15.6 | 10 | 5 | 11 | 5.5 | 5 | 2.5 | 4.5 |
| | ድ | 279 | 7.0 | 85 | 21.4 | 13 | 3.3 | 14 | 3.5 | 7 | 1.8 | 4.5 |
| *2.3 | ከ | 8 | 4.2 | 9 | 4.6 | 8 | 9.2 | 87 | 44.6 | 73 | 37.4 | 4.1 |
| | ኪ | 17 | 8.9 | 13 | 6.8 | 16 | 8.3 | 49 | 25.5 | 97 | 50.5 | 4.0 |
| | ድ | 25 | 6.5 | 22 | 5.7 | 34 | 8.8 | 136 | 35.1 | 170 | 43.9 | 4.0 |
| *2.4 | ከ | 33 | 16.8 | 42 | 21.4 | 35 | 17.9 | 56 | 28.6 | 30 | 15.3 | 3.0 |
| | ኪ | 25 | 12.6 | 22 | 11.1 | 40 | 20 | 49 | 24.6 | 63 | 31.7 | 3.5 |
| | ድ | 58 | 14.7 | 64 | 16.2 | 75 | 19 | 105 | 26.6 | 93 | 23.6 | 3.3 |
| 2.5 | ከ | 51 | 25.9 | 74 | 37.6 | 31 | 15.7 | 29 | 14.7 | 12 | 6.1 | 3.6 |
| | ኪ | 77 | 38.9 | 72 | 36.3 | 19 | 9.6 | 13 | 6.6 | 17 | 8.6 | 3.9 |
| | ድ | 128 | 32.4 | 146 | 37 | 50 | 12.7 | 42 | 10.6 | 29 | 7.3 | 3.8 |
| *2.6 | ከ | 7 | 3.5 | 4 | 2 | 9 | 4.5 | 31 | 15.6 | 148 | 74.4 | 4.6 |
| | ኪ | 18 | 9.4 | 14 | 7.3 | 15 | 7.8 | 6 | 13.5 | 119 | 62 | 4.1 |
| | ድ | 25 | 6.4 | 18 | 4.6 | 24 | 6.1 | 56 | 14.6 | 267 | 68.3 | 4.3 |
| 2.7 | ከ | 134 | 69.8 | 31 | 16.2 | 11 | 5.7 | 11 | 5.7 | 5 | 2.6 | 4.5 |
| | ኪ | 124 | 63.9 | 41 | 21.1 | 9 | 4.6 | 9 | 4.6 | 10 | 5.2 | 4.3 |
| | ድ | 258 | 66.8 | 72 | 18.7 | 20 | 5.2 | 20 | 5.2 | 15 | 3.9 | 4.4 |
| 2.8 | ከ | 139 | 69.9 | 50 | 25.1 | 5 | 2.5 | 1 | 0.5 | 4 | 2 | 4.6 |
| | ኪ | 145 | 72.5 | 39 | 19.5 | 8 | 4 | 5 | 2.5 | 3 | 1.5 | 4.6 |
| | ድ | 284 | 71.2 | 89 | 22.3 | 13 | 3.3 | 6 | 1.5 | 7 | 1.7 | 4.6 |

# አባሪ "ሸ"

3. «የአማርኛ ቋንቋን መማር ከሚያስገኘው ጠቀሜታ አንፃር» በሚለው ተላውጦ ስር ለተጠየቁት አራት ጥያቄዎች የተመዘገበው ውጤት ዝርዝር

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1 | ሰ | 30 | 15 | 23 | 11.6 | 65 | 32.7 | 43 | 21.6 | 38 | 19.1 | 2.8 |
| | ሴ. | 65 | 32.7 | 42 | 21.1 | 43 | 21.6 | 32 | 16.1 | 17 | 8.5 | 3.5 |
| | ድ | 95 | 24 | 65 | 16.3 | 108 | 27.1 | 75 | 18.8 | 55 | 13.8 | 2.3 |
| 3.2 | ሰ | 64 | 32.2 | 95 | 47.7 | 26 | 13.1 | 9 | 4.5 | 5 | 2.5 | 4.0 |
| | ሴ. | 72 | 36.5 | 79 | 40.1 | 30 | 15.2 | 9 | 4.6 | 7 | 3.6 | 4.0 |
| | ድ | 136 | 34.3 | 174 | 44 | 56 | 14.1 | 18 | 4.6 | 12 | 3 | 4.0 |
| 3.4 | ሰ | 43 | 21.9 | 76 | 38.8 | 44 | 22.5 | 23 | 11.7 | 10 | 5.1 | 3.6 |
| | ሴ. | 68 | 34.9 | 79 | 40.5 | 28 | 14.4 | 12 | 6.1 | 8 | 4.1 | 4.0 |
| | ድ | 111 | 28.4 | 155 | 39.6 | 72 | 18.4 | 35 | 9 | 18 | 4.6 | 3.8 |
| 3.5 | ሰ | 18 | 9.1 | 33 | 16.8 | 45 | 22.8 | 67 | 34 | 34 | 17.3 | 2.7 |
| | ሴ. | 30 | 15.3 | 55 | 28 | 49 | 25 | 45 | 23 | 17 | 8.7 | 3.2 |
| | ድ | 48 | 12.2 | 88 | 22.4 | 94 | 23.9 | 112 | 28.5 | 51 | 13 | 2.9 |

## አባሪ “ቀ”

4. «ወላጆች፣ እኩዮች፣ ሕብረተሰብና የመገናኛ ብዙሃን አመለካከት» በሚለው ተላውጦ ስር ለቀረቡት 6 ጥያቄዎች የተመዘገበውን ዝርዝር ውጤት ያሳያል::

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.1 | ለ | 28 | 14.5 | 53 | 27.5 | 45 | 23.3 | 36 | 18.7 | 31 | 16 | 3.1 |
| | ሊ | 41 | 21.1 | 51 | 26.6 | 54 | 27.8 | 33 | 17 | 15 | 7.7 | 3.4 |
| | ድ: | 69 | 17.8 | 104 | 26.9 | 99 | 25.6 | 69 | 17.8 | 46 | 11.7 | 3.2 |
| *4.2 | ለ | 3 | 1.5 | 2 | 1 | 9 | 4.6 | 40 | 20.3 | 143 | 72.6 | 4.63 |
| | ሊ | 13 | 6.6 | 12 | 6.1 | 16 | 8 | 45 | 22.7 | 112 | 56.6 | 4.2 |
| | ድ: | 16 | 4.1 | 14 | 3.5 | 25 | 6.3 | 85 | 21.5 | 255 | 64.6 | 4.4 |
| *4.3 | ለ | 5 | 2.6 | 10 | 5.1 | 3 | 1.5 | 34 | 17.5 | 143 | 73.3 | 4.5 |
| | ሊ | 10 | 5.2 | 8 | 4.2 | 13 | 6.8 | 34 | 17.7 | 127 | 66.1 | 4.4 |
| | ድ: | 15 | 3.9 | 18 | 4.6 | 16 | 4.1 | 68 | 17.6 | 270 | 69.8 | 4.5 |
| 4.4 | ለ | 22 | 11.2 | 38 | 119.3 | 27 | 13.7 | 41 | 20.8 | 69 | 35 | 3.5 |
| | ሊ | 28 | 14.7 | 29 | 14.7 | 22 | 11.2 | 43 | 21.8 | 75 | 38.1 | 3.6 |
| | ድ: | 50 | 12.7 | 67 | 17 | 49 | 12.4 | 84 | 21.3 | 144 | 36.6 | 3.5 |
| *4.5 | ለ | 12 | 6.1 | 29 | 14.7 | 26 | 13.2 | 49 | 24.9 | 81 | 41.1 | 3.8 |
| | ሊ | 33 | 16.7 | 29 | 14.6 | 34 | 17.2 | 44 | 22.2 | 58 | 29.3 | 3.3 |
| | ድ: | 45 | 11.4 | 58 | 14.7 | 60 | 15.2 | 93 | 23.5 | 139 | 35.2 | 3.6 |
| 4.6 | ለ | 140 | 70.7 | 46 | 23.2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 6 | 3 | 4.6 |
| | ሊ | 110 | 55.6 | 53 | 26.8 | 15 | 7.6 | 10 | 5 | 10 | 5 | 4.2 |
| | ድ: | 250 | 63.1 | 99 | 25 | 17 | 43 | 14 | 3.5 | 16 | 4 | 4.4 |

## አባሪ “በ”

5 «ለአማርኛ ቋንቋ አፈፌት/አ.አፈፌት ከመሆን አንፃር» ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተገኙት ዝርዝር መልሶች::

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1 | አ | 75 | 37.7 | 42 | 21.1 | 27 | 13.6 | 22 | 11.1 | 33 | 16.6 | 3.5 |
| | ኢ. | | | | | | | | | | | |
| | ድ | | | | | | | | | | | |
| *5.2 | አ | 34 | 17.5 | 35 | 18 | 49 | 25.3 | 33 | 17 | 43 | 22.2 | 3.1 |
| | ኢ. | 47 | 24.2 | 40 | 21.1 | 36 | 18.6 | 37 | 19.1 | 33 | 17 | 2.8 |
| | ድ | 81 | 20.9 | 75 | 19.6 | 85 | 22 | 70 | 18 | 76 | 19.6 | 3.0 |
| *5.3 | አ | | | | | | | | | | | |
| | ኢ. | 27 | 14 | 28 | 14.4 | 37 | 19 | 33 | 17 | 69 | 35.6 | 2.5 |
| | ድ | | | | | | | | | | | |
| 5.4 | አ | 33 | 16.9 | 48 | 24.6 | 45 | 23.1 | 40 | 20.5 | 29 | 14.9 | 3.1 |
| | ኢ. | 27 | 14.1 | 47 | 24.6 | 50 | 26.2 | 36 | 18.9 | 31 | 16.2 | 3.0 |
| | ድ | 60 | 15.5 | 95 | 24.6 | 95 | 24.6 | 76 | 19.7 | 60 | 15.5 | 3.0 |

# አባሪ "ተ"

6. «የመማሪያ መጽሐፍት ይዘትና አቀራረብ» በሚለው ተላውጦ ስር ለተጠየቁት ጥያቄዎች የተመዘገቡ ውጤቶች::

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 | ሀ | 42 | 21.4 | 62 | 13.6 | 55 | 28.1 | 22 | 11.2 | 15 | 7.7 | 3.5 |
| | ለ. | 56 | 28.4 | 68 | 34.5 | 43 | 21.8 | 20 | 10.2 | 10 | 5.1 | 3.7 |
| | ድ. | 98 | 24.9 | 130 | 33.1 | 98 | 24.9 | 42 | 10.7 | 25 | 6.4 | 3.6 |
| *6.2 | ሀ | 8 | 4 | 6 | 3 | 31 | 15.7 | 61 | 30.8 | 92 | 46.5 | 4.1 |
| | ለ. | 13 | 6.6 | 20 | 10.2 | 32 | 16.3 | 43 | 22 | 88 | 44.9 | 3.9 |
| | ድ. | 21 | 5.3 | 29 | 6.6 | 63 | 16 | 104 | 26.4 | 180 | 45.7 | 4.0 |

## አባሪ «ቸ»

7. «ለአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከተሰጠው ዝቅተኛ ደረጃ አንፃር» ከሚለው ተላውጦ ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች የተመዘገቡት ውጤቶች::

| የጥያቄዎች መለያ ቁጥር | የመላሾች አይነት | በጣም እስማማለሁ | % | እስማማለሁ | % | ለመወሰን ያስቸግረኛል | % | አልስማማም | % | ፍፁም አልስማማም | % | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7.1 | ሰ | 47 | 23.5 | 71 | 35.5 | 41 | 20.5 | 25 | 12.5 | 16 | 8 | 3.54 |
| | ሴ. | 47 | 23.6 | 45 | 22.6 | 42 | 21.1 | 27 | 13.6 | 38 | 19.1 | 3.18 |
| | ድ: | 94 | 23.6 | 116 | 29.1 | 83 | 20.8 | 52 | 13.1 | 54 | 13.5 | 3.36 |
| *7.2 | ሰ | 11 | 5.5 | 24 | 12.1 | 19 | 9.6 | 50 | 25.1 | 95 | 47.7 | 4.0 |
| | ሴ. | 25 | 12.7 | 21 | 10.6 | 23 | 11.6 | 37 | 18.6 | 94 | 47.2 | 3.8 |
| | ድ: | 36 | 9 | 45 | 11.3 | 42 | 10.6 | 87 | 21.9 | 189 | 47.4 | 3.9 |

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬን ያስቀመጥኩኝ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ዕሁፎች ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ድንቂሳ ደሬሳ

ፊርማ ______________

አድራሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ቀን 14/10/1996 ዓ.ም